# ምዕራፍ ስድስት

በሕሊና ህይወት የተከሰተው ታላቁ ማዕበል ካለፈ ሳምንታት ተቆጠሩ ። ለህሰን የግንኙነት መደምደሚያ ለመስፍን ደግሞ ለደብዳቤው መልስ ፃፈች ። ለህሰን በፃፈችው ደብዳቤ ምንም ማብራሪያ አልጨመረችም ። ቀዘቀዝ ባለ መልኩ ሀሰን እርሷን ማየት፣ ስልክ መደወል ወይም ደብዳቤ መፃፍ እንዲያቆም ጠየቀች ። በት/ቤት በኩል ሁለት ጊዜ ስልክ ቢደውልም ማንነቱን ካረጋገጠች በኃላ ለማነጋገር ፈቃደኛ እንዳልሆነች ገልፃ ስልኩ ተዘጋ ።

ለመስፍን በአጠቃላይ መልኩ ጋባዥ የሆነ ደብዳቤ ስትፅፍ ፣ በመልስ የደረሳት ደብዳቤ ግን ዝርዝር የያዘ ፣ ስለመስፍን ፍላጎት የሚያስረዳ ሆኖ ጥያቄ አዘል ነበር ። የሕሊናን ትኩረት በከፍተኛ ደረጃ የሳበው ግን በመስፍን ደብዳቤ ላይ የተሰነዘሩት በሁለት ዐረፍተ ነገሮች የቀረበው መልዕክት ነበር ።

« ሕሊና ለትምህርት በጣም ጉጉት እንዳለሽ ባለፈው ጊዜ ስንወያይ ገልፀሽልኛል ። ይኸውልሽ ቁምነገር አልረሳም ። እዚህ እኛ ጋ አንድ ኮሌጅ አለ ብዙ የውጪ ሀገር ተማሪዎችን እየተቀበለ ያስተናግዳል ። የምትፈልጊ ከሆነ የመግቢያ ማመልከቻ ቅፅ በሚቀጥለው ጊዜ እልክልሻለሁ ። ሞልተሽ ላኪና እኔ እዚህ እከታተልልሻለሁ ። »

ሕሊና በዚህ አጭር ጊዜ ትውውቅ መስፍን ይህን ዓይነት ውለታ ለእርሷ ለማድረግ የፈለገበትን ምክንያት ብትጠራጠርም ከነበረችበት ሁኔታ በአሸናፊነት ለመወጣትና የትምህርት ጥሟን ለማርካት የሚያስችል ብቸኛ ዕድል በመሆኑ ፣ ያለአንዳች ቅሬታ ግብዣውን ተቀበለች ። ለደብዳቤውም መልስ ሳይውል ሳያድር ፃፈች። ሕሊና በምታደርገው ሁሉ ደስተኛ ሆነች ። አካባቢዋ አብረዋት የሚውሉ የሥራና የግል ጓደኞቿ የሕሊናን የባህሪ ለውጥ



በቀላሉ ተገነዘቡ ። ለለውጡ ምክንያት ምን እንደሆነ የተመራመሩት ግን ጥቂቶች ብቻ ነበሩ ። የቅርብ ጓደኛዋ ከበቡሽ በሕሊና ለውጥ ተደሰተች ።

« ሕሊና እስካሁን የጋን መብራት ሆኖ የቆየው ውበትሽና የጨዋታ ስልትሽ ሊወጣ እንዴት እንዳደመቀሽ አታውቂም ? ምነው እንቺን ባደረገኝ ። ያየሽ ሁሉ ይመኝሻል » በማለት ከበቡሽ ሕሊናን አሞገሰቻት ።

አበራ የወንድሙና የሕሊና ግንኙነት ደረጃው ከፍ ባለ ቁጥር እየከፋው መጣ ። አልፎ አልፎም ይህን ስሜቱን ግልፅ በማድረግ ሕሊናን « እስቲ አትቸኩይ ! ቀስ በይ ! » በማለት የሚሰጠው ምክር ከማበረታታት የተቆጠበና የቀዘቀዘ ሆነ ። ከሁሉም ለሕሊና ዕንቅቅልሽ የሆነባት ግን በጣም የሚቀርቧት ሁለቱ የመስፍን ታናናሽ እህቶቹ ናቸው ። ወዳጅነታቸው የደራ ከመሆኑም ባሻገር በዕድሜ እኩያሞች በመሆናቸው ከሥራ ውጪ በሚደረገው ማህበራዊ ተሳትፎ በየጊዜው ስለሚያገናኛቸው ቅርርባቸው የሰፋ ነበር ። ከወንድማቸው ጋር ያላት ግንኙነት እየጠነከረ ሲመጣ እህትማማቾቹ ሕሊናን እየራቁና ብሎም በግልፅ እየተፃረሩ መጡ ።

ሕሊና ለአድራጎታቸው ካላት ልምድና ከምታገኘው ምክር እንፃር ልማዳዊ የእህትነት ስሜት ነው በማለት ለማቀዝቀዝ ሞከረች። ሆኖም ይህ እሉታዊ ስሜት በጥቂት የቤተሰቡ አባላት ሳይወሰን ጠቅላላውን ቤተሰብ በመበከሉ ሕሊና በዝምታ ልታልፈው አልቻለችም ።

« ከበቡሽ የአበራ ቤተሰቦች ለምንድነው እንዲህ የጠሉኝ » በማለት ሕሊና በአንድ አጋጣሚ ከበቡሽን ጠየቀቻት ።

« እባክሽ ተያቸው እነርሱ ዓመላቸው ናቸው ። አንቺን ብቻ አይምሰልሽ እኔንም ያንገበግቡኛል ። እንዳላወቀ መዝጋት ነው » አለች ከበቡሽ ለጉዳዩ ብዙም ክብደት ባለመስጠት ።

« አበራንም ጭምር እኮ ነው የምልሽ እሱን ደግሞ ምን እንዳደረኩት አልገባኝም ? » አለቻት ::

« አይገባሽም እንዴ ? ጉዳዩ አንቺ ከመስፍን ጋር በመጣፍሽ የመላውን ቤተሰብ ዕቅድ ነው ያበላሸሽው :: » አለች ከበቡሽ ::

« እንዴ ! ምን ማለትሽ ነው የቤተሰቡን ዕቅድ አበላሸሽ ስትይ? እኔ ምን አድርጌ አበላሻለሁ ? »

« ሕሊና ሞኝ ነሽ ልበል ? መስፍን ለአንቺ ዝም ብሉ የሚፅፍ ይመስልሻል ? እስቲ ንገሪኝ በሣምንት አንድ ጊዜ ደብዳቤ ፤ በወር አንድ ጊዜ ስጦታ የሚልክልሽ ? ንገሪኝ ! እስቲ አንቺ እንደሚገባሽ የመጣፍ በሽታ አለበት ብለሽ ታምኛለሽ ? ስለወደደሽ ነው ! ከአንቺ ጋር ለመኖር ስለሚያስብ ነው :: ሌላ ምንም ምክንያት የለውም :: ሕሊና ይግባሽ » አለች ድምጿን ከፍ አድርጋ ::

« እሺ ገባኝ ልበል :: ታዲያ ወንድማቸው እኔን ቢወድ እነርሱ ምናቸው ተነካ ? እነስኩበት ? በዛሁበት ? እኔ እኮ ግራ ገባኝ» አለች እራሷን እያወዛወዘች ::

« አንቺን ወደደ ማለት ሁለንተናው ወደ አንቺ ዞረ ማለት ነው :: ቀድሞ ለእህቶቹ የሚጽፈው ደብዳቤና ስጦታ አሁን ለአንቺ ሆነ :: ከሁሉም ከባዱ ግን እማከለች ወደ አሜሪካ የሚቀጥለው ዓመት ለመሄድ ተዘጋጅታ ነበር :: ይወስዳት የነበረ ወንድሟ መስፍን፤ አሁን የሚወስደው ማንን እንደሆነ አይታወቅም :: ቤተሰቡ የሚጠረጥረው አንቺን ነው :: » ከበቡሽ ወደ ሕሊና እየቸና ቆመች ::

« ሕሊና ስሚ መቼም አንቺ የዋህ ሴት ነሽ :: ሁሉም ወዳጅሽ ነው :: ያለውን ሁኔታ ስነግርሽ እንዳትደነግጪ በጣም ተጠንቀቂ :: ከመስፍን ቤተሰቦች ራቅ በይ :: ሊጎዱሽ ይችላሉ » በማለት ጥቂት አሰበች :: « አበራ ጓደኛዬ ነው እወደዋለሁ :: እርሱንም ቢሆን አንድ የተረጋገጠ ነገር እስከሚኖር ድረስ ተጠንቀቂው :: » በማለት የሕሊናን እጅ በእጆቿ በደግ አመስካከት



ዳሰሰች :: ሕሊና በፀጥታ ከማዳመጥ በስተቀር መልስ ለመስጠት አልቻከለችም :: የሰማችውን ማብሰልሰል መረጠች ::

« ይገርማል አንቺ የምትይው ሁሉ አይቀርም ከአንዱ ወጣሁ ስል ደግሞ ወደዚህ ተሸጋገርኩ :: ከእሳት ወደ ረመጥ ይሉሻል ይሄ ነው :: ህሰንን ተገላገልኩ ስል የመስፍን ዘመዶች ደግሞ ሰፈሩብኝ :: እኔስ ምን ይሻለኛል :: ዕድሌ ይሆን ? » በማለት ራሷን ጠየቀች ::

« ዕድልሽማ ቆንጆ ዕድል ነው :: ሰዎች ግን የአንቺን ዕድል ለመቀማት ይሯሯጣሉ :: እግዚአብሄር በጣም ይወድሻል ልታምኚበትና ልትፀልይ ይገባሻል » አለች ከበቡሽ የተማረረችውን ሕሊናን በማፅናናት ::

« ተጠንቀቂ ስልሽ በጣም አትቅረቢያቸው ፤ ከቀረብሽ ደግሞ ቅርበትሽ በጥንቃቄ ይሁን ማለቴ ነው :: አይዞሽ እንግዲህ በመንግስት ህገር ምን ማድረግ ይችላሉ :: መስፍን መጣብሽ እንጂ አንቺ የሙጥኝ ብለሽ አልሄድሽበት ምን አስጨነቀሽ አለቻት :: »

« የእርሱ መፃፍ ቢቀርብኝስ ? የእርሱ ስጦታ መጥቶ የትኛ ውን ግንብ ሊገነባልኝ ነው ? ቀርቶስ የትኛውን ግንብ እንዳያፈርስብኝ? ዛሬውኑ አቋርጥ ፤ ገንዘብህን ለእኔ ከምታባክነው ዘመዶችህን እርዳበት ብዬ እፅፍለታለሁ » አለች ሕሊና የተናገረችውን ራሷን ለማሳመን በመሞከር ::

« እኔ አንቺን ብሆን ያልሽውን አላደርግም :: እንደዚያ ብትይ ነገሩን ማባባስ ነው :: መስፍን ይሄን ሲሰማ ዘመዶቹን ከእነጭራሹ ነው የሚዘጋው :: ይልቁንስ የአንቺ መፃፍ አልፎ አልፎ ጣል ጣል የሚያደርገውን ደብዳቤ እንዲቀጥል ይረዳል :: እነርሱም ለጊዜው ነው እንደዚህ የሚሆኑት :: ቁርጡን ሲያውቁ ይለይላቸዋል :: ይልቁንስ ከአንቺ ጋር መስማማቱ ሳያዋጣቸው ይቀራል ብለሽ ነው::» በማለት ከበቡሽ ጥቂት እንደተራመዱ ቆም አለች ::

« መጀመሪያ ከአበራ ጋር ስሆን ዘመዶቹ ያላወሩት ነገር አልነበረም ። ቤት ተከራይቶ ከእህቶቹ ቤት ሲወጣ እዬዬ ብለው አለቀሱ ። በእናትና በአባታቸው አፅም አስገዘቱት ። እኔ ደግሞ ድርቅ አልኩ ። የራስህ ቤት ከሌለህ ለው ቤት እየመጣህ አልውልም፣ አላርፍም ፣ ገረድ አይደለሁም ግልምጫና ስድብ የሚደርስብኝ አልኩት ። እርግጥ ለእርሱ ከባድ ምርጫ ነበር ፤ አውቃለሁ ። ለእኔም እንደዚሁ ። ያኔ ይህንን እርምጃ ባልወስድ እስካሁን አብረን አንቆይም ነበር ። ቤት ተከራይቶ ከወጣ ወዲህ የጥል መነሻው ሁሉ ተወገደ ። የምንከራከርበት ጉዳይ የለም ። በእርግጥ የአበራና የመስፍን ጉዳይ እንኳ የተለያየ ነው ። » ብላ ዝም አለች ከዚህ በላይ ለመቀጠል አልፈለገችም ነበር ።

« እንዴት ነው የተለየ ነው ስትይ ? » አለቻት ሕሊና ።

« አበራን እህቶቹ በእውነት ይወዱታል ። አብረው በመኖራቸው ፣ ክፉውንና ደጉን አብረው በማሳለፋቸው እንዲለያቸው አይፈልጉም ። አበራ ለቤተሰቡ የአባትን ያህል መንፈሳዊ ድጋፍ የሚሰጥ አውራ ነው ። በእርግጥ መስፍን ወንድማቸው ቢሆንም ያበራን ያህል ጣዕሙን አያውቁትም ። ለችግራቸው ደራሽ ነው ። የቤተሰቡን የገንዘብ ፍላጎት ከወንድሙ ከሙሉጌታ ጋር በመሆን ለማሟላት ጥረዋል ። ሁለቱም ወንድሞቻቸው ናቸው ፤ እንዳየደረጃቸውና እንደየቅርበታቸው ይወዷቸዋል ። » አለች ከበቡሽ ንግግሯን በመደምደም ። በመሀከላቸው ፀጥታ ሰፈነ ። በየቤታቸው እስከሚደርሱ ሁለቱም በፍጥነት ተራመዱ ። ሕሊና ቤቷ ገባች ። እረፍ ብላ ከበቡሽ ስለነገረቻት አባባል ጠልቃ አሰበች ።

« አበራ እንዴት እንደዚህ ያስባል ? የመሰሰኝና የገመትኩት ለእኔ እንደሚቆረቆርልኝ ነበር ። ምን ነካው ? የሌሎቹ ሁሉ ማደም ከበቡሽ እንዳለችው ከሆነ ይገባኛል ። ሌላ ምክንያት እንዳይኖራቸው



እንጂ ። አይ አበራ ! . . . እንዴት ያናድዳል ? » አለችና መልሳ ጥቂት አሰብ አደረገች ። የሆነ ሀሳብ ብልጭ አለባት ።

« ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው ። ለምን ራሴ አልጠይቀውም ። እንዲያውም አባባሉ ለሚቀጥለው እርምጃ ያዘጋጀኛል ። » በማለት አበራን ጠርታ ለማነጋገር ወሰነች ። ከትምህርት ቤት መልስ ከሥራ በኋላ ተቀጣጥረው ሕሊና ቤቷ ቁጭ ብላ ስትጠብቅ የመጣው አበራ አልነበረም ። በምትኩ ከበቡሽን ነበር የላከው ። ከበቡሽ አንኳኩታ ስትገባ ሕሊና ደነገጠች ።

« ምን ሆነ አበራ ? » ብላ ከበቡሽን ጠየቀቻት ። ከበቡሽ ወዲያውኑ ለጥያቄዋ መልስ አልሰጠችም ። ተመቻችታ ወንበር ላይ ተቀመጠች ።

« ምንም አልሆነም ። ሆኖም መምጣት አልቻለም ። ስለዚህ እኔን ላከኝ ። ይቅርታ አስቸኳይ ነገር አጋጥሞኝ እህቴ ጋ ሄጃለሁ ። የዛሬውን ቀጠሮ ወደ ሌላ ቀን እንድታስተላልፊው ብሎሻል » በማለት መልዕክቱን ለሕሊና ከነገረቻት በኋላ « አበራ ምንም ማድረግ አይችልም ። አንቺ ቤት ሲወጣና ሲገባ ቢያዩት እህቶቹ ጥምድ አድርገው ነው የሚይዙት ። ዛሬ ልነግርሽ አልችልም ። ምን ያህል እንደተጨነቀ ። አበራ ክፉ ነገር ባያስብም በአንቺ ምክንያት ከእህቶቹ ጋር መቀያየም አይፈልግም ። » በማለት የራሷን አስተያየት ከመልዕክቱ በስተጀርባ አከለችበት ።

« ከበቡሽ በጣም አመሰግንሻለሁ ። በመምጣትሽ ቅርም አይለኝ ። ለማንኛውም ቢሆን የቦታ ምርጫ ነው እንጂ ትምህርት ቤትም ቢሆን ላነጋግረው እችላለሁ ። ምርጫ ከሌለኝ የማደርገው በአለችኝ የምሳ ሠዓት ብቸኛ ቦታ ፈልጎ ማነጋገር ነው ። እስከመቼ ድረስ ሆድና ጀርባ እንሆናለን ። » አለች ሕሊና ቁጣ ስሜቷን እየገለፀች ።

ከዚያ ወንድም ፣ እህት ፣ ከዚያ የተረፈ ትርፍ ነው » በሚል መርህ ላይ የተመሠረተ ነው ። አሁን የምታይን ታዲያ የዚያ ርዝራዥ ነን።

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የራሱን ህይወት መኖር አልጀመረም ። የቤተሰብ የጋራ ኑሮ አሁንም በእኛ ዘንድ እንደቀጠለ ነው ። በቤተሰባችን ለቤተሰብ አባላት እኛ የሚሰው ቃል ተግባራዊ በመሆኑ ግንኙነቶች ከውጪ ሰው ወደ ቤተሰቡ ሲስነዘሩ የሚቆጠረው እንደሰርጎ ገብና ተቀናቃኝ ነው ። ቤተሰቡ ባለው አቅምና ችሎታ በአንድነት ይህን ሰርጎ ገብ ይቋቋማል ። ሒሊና ይኸውልሽ ታዲያ ከአራት ወንድማማቾች አንድ ብቻዬን ከስድስት እህቶቼ ጋር በዚህ ፍልሚያ መካከል አለሁ ። » . . . አበራ ራሱን ነቀነቀ ። ተስፋ በመቁረጥ መልክ ዓይኖቹን ወደ መሬት ተክሎ « ይህን ሁሉ እንዳስተናግድ አደራው በእኔ ትከሻ ላይ ነው የወደቀው ። »

« ታዲያ መስፍን እዚህ ውስጥ ምን አገባው ? »

« መስፍን የቤተሰቡ አባል ነው ። ቀደም ሲል የገባው ቃል ነበር ። ቃሉን አልፈፀመም ። ለመስፍን ይህ አዲስ ነገር አይደለም ። እርሱ የመሰለውን ነው የሚያደርገው ። ስለዚህ ቤተሰቡ በገባው ቃል መሠረት መስፍንን ለማስገደድ ባለመቻላቸው ሀሳቡን መቃወምና ማፍረስ ላይ አተኮሩ ። »

« ታዲያ ይሄ ከእኔ ጋር ምን ግንኙነት አለው ? »

« ሒሊና ባለፈው ጊዜ ስለመስፍን ደብዳቤ ስንነጋገር የነገርኩሽ መሰለኝ ። መስፍን ስለአንቺ ያለው ስሜት ዘለዓለማዊ ነው። በመፃፍ ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም ።

« ለቤተሰቡ በፃፈው ደብዳቤ ስለ ሠርግና ስለመሳሰለው አውስቷል ። ቤተሰቡ ትኩረቱን ወደ ሌላ ለመለወጥ የተለያዩ ደብዳቤዎችን ቢያዥጎደጉዱም መስፍን ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ የሚፅፈው ስለ ትዳር እና ስለወደፊት ኑሮው ነው ። ማለትም



መስፍን ሁልጊዜ በደብዳቤው ስለአንቺ ነው የሚያወሳው ። ቤተሰቡ ይህ አሳስቦታል ። »

« ያልከው በሙሉ ትክክል ነው እንበል ፤ ግን የአንተንና የእኔን ግንኙነት ምን አሻከረው ? »

« በአንቺ ምክንያት ነው መስፍን የተለወጠው ። ለእኔ አትንገሪኝ አውቃለሁ ። ሒሊና አንቺን እንደ ራሴ ነው የማውቅሽ ። መስፍንን ጥሩ ያልሆነ ነገር መከረሽ እንደማትለውጪው አውቃለሁ። ሆኖም ቤተሰቡ እንደእኔ አይገባውም ። የእኔ ከአንቺ ጋር መቀራረብ ቤተሰቡን መበታተን ማለት ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ በያዙት መጥፎ አስተሳሰብ እንዲቀጥሉ መገፋፋት ነው ። ግን አሁን ባለው ሁኔታ ሳንዘጋጋ ሀሳባችንን ልናስታርቅና ጤናማ ግንኙነት እንዲመሠረት ለማድረግ እንችላለን ። ካንቺ ጋር እንደድሮው የነበረን ግንኙነት መቀጠሉን ካወቁ ለኔም እንደአንቺው በሩን ይዘጋሉ ። ይህ ለሁሉም አይበጅም ። »

ስለዚህ ከእኔ ጋር መነጋገሩን ያቆምከው የቤተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ ስትል ነው ? »

« አዎን የቤተሰቡንም የአንቺንም ደህንነት ለመጠበቅ ነው ።» አበራ ወደ ሒሊና በእርግጠኝነት ተመለከተ ።

« አልገባኝም ። »

« ለማንኛውም በደፈናው ለጥቂት ጊዜያት ሁኔታዎች እስከሚረጋጉ የእኔና የአንቺ ግንኙነት የቀዘቀዘ ይሆናል ። አንቺን በመጥላቴ ወይንም ቤተሰቤን በመደገፌ ሳይሆን ለሁላችንም ደህንነትና ሁኔታዎችን በጤናማ መልክ ለማረጋጋት የግንኙነታችን መቀዝቀዝ አስፈላጊ ነው ። »

« ቀዘቀዘ ማለት ከእነ ጭራሹ መነጋገር አንችልም ? »

« ትምህርት ቤት »

« ትምህርት ቤት መነጋገር ከተቻለ እርሱም ተስፋ ነው ። »

« በጥቂቱ »

« ከከበቡሽ ጋርም መነጋገር ክልክል ነው እንዳትለኝ » አለች ሕሊና ፈገግ ብላ በማሾፍ መልክ ::

« ከበቡሽን ማን ያግዳታል :: በፍቃዷ የምትኖር . . . ተይ ቢሏትም በጆ አትል :: . . .» ጥቂት አመነታ :: « እኔና አንቺ ዓላማ አለን :: »

« ምን ማለት ነው ? ዓላማ ስትል ? ነገሩ ጠጠረብኝ »

« ቤተሰቡ የአንቺና የመስፍን ግንኙነት የግላችሁ መሆኑን እንዲረዱትና እንዲቀበሉት ማድረግ ማለቴ ነው :: »

« እኔ የቤተሰቡን አስተሳሰብ እንዴት አድርጌ ነው የምለውጠው ? »

« እርሱን እንገዲህ ጊዜው ሲደርስ እናያለን :: ለጊዜው የምጠይቅሽ ግን ሁኔታውን አጢነሽ እንድታይውና በተቻለ መጠን ለመስፍን ስትፅፊ ጉዳዩን ላለማንሳት ሞክሪ :: እርሱ ከሰማ ነገር ተበላሸ ማለት ነው :: »



* * *

በመስፍንና በሕሊና መሀከል የሚካሄደው የደብደቤ ግንኙነት ቀጠለ :: የግንኙነታቸው ደረጃና ዓይነት ከፍ እያለና እየጠበቀ በመምጣቱ በአካባቢያቸው ያሉ ቤተሰብና ዘመድ አዝማድ ወገን ለይተው የግንኙነቱ ደጋፊና ነቃፊ በመሆን ከሕሊና ጋር ያላቸውን ቅርበት አስተካከሉ :: የሕሊናና የሀሰንም ግንኙነት እንደዚሁ በቀላሉ ሊሸነገል አልቻለም :: ሕሊና በቆራጥነት ግንኙነቱን ለማቋረጥ ብትጥርም የሀሰን ፍላጎት ግን ቀኑ እየገፋ በሄደ ቁጥር ሕሊናን መልሶ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ የነበረው ቆራጥነት እየናረና እየጎለበተ መጣ ::

ሀሰን ወደ አሰላ በመመላለስ ከሕሊና ጋር ቅርበት አላቸው ብሎ ያሰባቸውን ሰዎች ፊትለፊት በማነጋገር ለማስረዳት ሞከረ :: በሀሰን መመዘኛ የሕሊና የቅርብ ጓደኛ አበራ ነው :: ቢያማክረው ችግሩ እንደሚቀረፍ አሰበ :: የሀሰን እንደገና ማንሰራራትና በአካባቢው ማንጃበብ ጤና የነሳው ሕሊናን ብቻ አልነበረም :: የመስፍንና የሕሊናን ግንኙነት ለሚደግፍ ሁሉ እንደመጥፎ ክስተትና በራሳቸው ላይ እንደተሰነዘረ ጥቃት አድርገው ቆጠሩ :: ለአበራ ሕሊና የቅርብ ጓደኛ ብቻ አይደለችም :: መስፍን በሁሉም ነገር ሕሊናን ለአበራ አደራ ሰጥቶታል :: እርሱም የተሰጠውን አደራ በቀላሉ አላየውም :: ማንኛውም በሕሊና ላይ የሚሰነዘር ጥቃት በቀጥታ ስለሚመለከተው በተቻለው ሁሉ ጥቃቷን የማስወገድ ወይንም የመከላከል ኃላፊነት እሱ ላይ ሆነ ::

ሕሊናና የመስፍን ቤተሰቦች በመሀከላቸው ያለውን ቅራኔ በከፊል በማስወገድ ለመነጋገር ያላቸውን ፍላጎት አሰፉ :: ሕሊና ለአበራ ከሀሰን ጋር የነበራትን ግንኙነትና ግጭት በመግለፅ ቀደም

ሲል እንዲያውቅ ያደረገች በመሆኑ ሀሰንን ለመቋቋም በምታደርገው ትግል ሁሉ በሙሉ ልብ ተባባሪዋ በመሆን ከሀሰን ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ ስለሁኔታው ለማስረዳት ሞከረ ፡፡

« ሀሰን ለግንኙነታችሁ መቀጠል የበኩሉን ጥሬ ነበር ፡፡ ሆኖም ሕሊና ግንኙነቱ እንዲቀጥል አትፈልግም » በማለት ወደ ቤቷ መምጣቱን እንዲያቆም ሀሰንን መከረው ፡፡ ሀሰን ግን « እወዳታለሁ ፡፡ ከእርሷ ጋር ለመሆን ፍላጎት አለኝ ፡፡ ስለ አጠፋሁት ሁሉ ይቅርታ እጠይቃታለሁ » ሲል ተከራከረ ፡፡ ሆኖም ሕሊናን አግኝቶ ስለሁኔታው ሊያነጋግራት አልቻለም ፡፡

ፀሀይዋ በመጥለቅ ላይ ነበረች ፡፡ ቀኑ አልፎ ወደ ጨለማው እያዘገመ ነው ፡፡ ሰዎች የቀን ሥራቸውን ፈፅመው ወደየቤታቸው በመግባት ላይ ናቸው ፡፡ ሕሊና ከትምህርት ቤት ተመልሳ ፣ ልብስ ቀይራ ወደ ማጀት ለመግባት እየተዘጋጀች ነበር ፡፡ ገርበብ ባለው የቤቷ በር የሚገባ ሰው አየች ፡፡ ከሩቁ ለመለየት ባለመቻሏ « ማን ነው ? » በማለት እየተጣራች ወደ በሩ ቀረበች ፡፡ ያየችውን ጥላ በመሸሽ መልክ ወደ በሩ በፍጥነት አመራች ፡፡ « ሕሊና አትደንግጪ፤ ሀሰን ነኝ ላነጋግርሽ ስለፈለኩ ነው » በማለት በበሩ መሀከል ቆሞ የምትሸሸውን ሕሊናን ለማስቆም ሞከረ ፡፡

« ላነጋግርህ አልፈልግም ፡፡ ለምን እዚህ ትመጣለህ ? » ስትል ጮኸችበት ፡፡

« ቆይ እንጂ ፣ ለምን እንደዚህ ትሆኛለሽ ? » በማለት እጇን በሁለት እጆቹ ጠበቅ አድርጎ ይዞ በመለማመጥ መልክ ጠየቀ ፡፡

« አትያዘኝ ፤ ልቀቀኝ ፤ ከቤቴ ውጣለኝ ነው የምልህ ! ላነጋግርህ አልፈልግም ብዬሃለሁ ፤ እጄን ጎዳኸኝ » ጉዳቷን ለማሳየት ፊቷን አጨማደደች ፡፡

« ኧረ ጎረቤት ምን ይልሻል ? አትጩሂ ፤ ቀስ ብለሽ አትናገሪም ? »



« ምንም ቀስ ማለት የለም ፡፡ ውጣልኝ ብዬሃለሁ ሌላ ነገር ሳይመጣ ! » እርዳታ በመፈለግ ሕሊና ድምጿን ከፍ አድርጋ በመጮህ ተናገረች ፡፡

« የአንቺ ጩኸት ምንም ነገር አይፈጥርም ፡፡ ይልቁንስ የምለውን አዳምጪ ፡፡ እዚህ የመቆየት ሀሳብ የለኝም ፡፡ »

« አልፈልግም ፡፡ አላዳምጥህም ብዬሃለሁ ፡፡ አንተ ሰውዬ ልቀቀኝ ፡፡ »

በበሩ በኩል ሁለት ሰዎች ተሯሩጠው ገቡ ፡፡ ግርግሩ ብዙም አልቆየም ፡፡ ሀሰን ቤቱን ለቆ ወጣ ፡፡ በገላጋይነት የመጡት ወደ የቤታቸው ተመለሱ ፡፡ ይህ የሀሰን ድርጊት ለሕሊና አዲስ ክስተት ነበር ፡፡ ሀሰን ከዚህ በፊት በጉልበቱ ለመጠቀም ሞክሮ አያውቅም ነበር ፡፡ « ሰዎቹ ባይደርሱ ኖሮ ምን ሊያደርግ ነበር ፡፡ ላነጋግርሽ ፣ ምን ያነጋግረኛል ? አልፈልግም ማለት አይገባውም ! » ሕሊና የሀሰን ድርጊት ቢቀጥል ወዴት እንደሚያመራ አላወቀችም ፡፡ ፍርሃቷን ውጣ ፣ ሀፍረቷን ሸፍና ለማሳለፍ ወሰነች ፡፡

እንቅልፍ አልወሰዳትም ፡፡ በሯ የተንኳኳ መሰላት ፡፡ ወደ በሩ ጠጋ ብላ አዳመጠች ፡፡ ሆኖም ምንም ድምጽ ለመስማት አልቻለችም፡፡ ወደ መኝታዋ ተመልሳ ለመተኛት ሞከረች ፡፡ በመስኮት በኩል የመንኳኳት ድምፅ የሰማች ስለመሰላት ወደ መስኮቱ ጠጋ ብላ ለማዳመጥ ሞከረች ፡፡ ሆኖም የሰማችውን ደግማ መስማት አልቻለችም ፡፡ ተመልሳ አልጋዋ ላይ ተኛች ፡፡ ለሦስተኛ ግዜ የሰማችው ድምፅ ግን በጣም አስደንጋጭ ነበር ፡፡ በመኝታ ቤቷ አቅራቢያ የነበረው መስኮት በድንጋይ እሩምታ ተደበደበ ፡፡ ሕሊና ለመደበቅ ወደ አልጋዋ ስር ቶሎ ብላ ገባች ፡፡ ከሁለት ተከታታይ የድንጋይ ናዳ በኋላ አካባቢው ፀጥ አለ ፡፡

ሕሊና ሰውነቷ ዛለ ተንቀጠቀጠች ፡፡ የምትይዘውና የምትጨብጠው ጠፋት ፡፡ ሀሳቧ ርቆ ሄደ ፡፡ በህይወቷ የሰማችውን

አሰቃቂ የግድያ ወንጀል አስታወሰች ። የራሷን ሁኔታ ከዚህ አሰቃቂ ወንጀል ጋር በማመሳሰል ፍርሀቷን አናረች ። ቶሎ ቶሎ እየተነፈሰች አልጋዋ ሥር ያለ አንዳች ነገር ፈለገች ። እጆቿን ወዲያና ወዲህ እያወራጨች ዳሰሰች ። እንደድንገት እጇ ራቅ ብሎ በተቀመጠ ቋጠሮ ላይ አረፈ ። ፍርሃቱ ለቋት ሠላም ሰፈነ ። የነካችውን ከረጢት ወደራሷ አቀረበችና አቀፈችው ። ወዙን አሽተተች ። ከአልጋው ስር ወጣ ብላ ከረጢቱን ለመክፈት ሞከረች ። አጠገቧ ያለውን መብራት አብርታ ከከረጢቱ ውስጥ ያወጣችውን የአባቷን መጥረቢያ ወደ ራሷ አቅርባ አልጋው ላይ ተቀመጠች ። አካባቢዋን ትታ በሀሳብ ማዕበል እርቃ ሄደች ።

«አባዬ እባክህን እርዳኝ ፤ ከዚህ ሁሉ መዓት አውጣኝ » በማለት በእጇ የያዘችውን መጥረቢያ እንደቅርብ ሰው አቅፋ ማልቀስ ጀመረች ። ድንገት የሕሊና በር ተንኳኳ ። ከውጪ ከሚጠራው ድምፅ ለእርሷ ዕርዳታ የመጡ መሆናቸውን አበሰራት ።

በሩን በጉጉት ስትከፍት መምህር ዲሪባ ከሌሎች የሠፈሩ ሰዎች ጋር በመሆን « ደህና ነሽ ! ደህና ነሽ ! » በማለት ጠየቋት ። በተደናገጠ መልክ ቀርበው ሕሊናን ተመለከቱ ። ሕሊና ደህንነቷን ገልፃ እንዲቀመጡ ጋበዘች ። ከመሀከላቸው አንደኛው ቀደም ሲል በሀሰንና በሕሊና መሀከል ለተፈጠረው ግጭት በገላጋይነት የቀረበ ነበር ።

« ይህ ሰው ሌላ ነገር ሊያደርግ ስለሚችል አሁኑኑ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄደሽ ለምን ክስ አትመሰርችም ? » በማለት ጠየቀ ። ጎረቤቱ የሕሊና መነካት ብቻ ሳይሆን የሰፈሩ ፀጥታ መነሳት ጉዳይ እንዳሳሰበው ገለፀ ።

« በይ ልብስሽን ቀይሪና እኔና ድሪባ እንሸኝሻለን » በማለት ለጊዜው ወደየቤታቸው ተመለሱ ። ሕሊና በአድራጎቷ ቅር እያላት ሁለቱን ሰዎች ተከትላ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተያይዘው ሄዱ ። ሕሊና



ፖሊስ ላቀረበላት ጥያቄ አጠቃላይ መልስ በመስጠት በዕለት ሁኔታ ላይ ስፍሮ እንዲቀመጥ ጠየቀች ።

ፖሊስ « የሚጠረጥሩት ሰው አለ ? » ብሎ ለጠየቃት ጥያቄ ምንም መልስ አልሰጠችም ።

« ለህይወቴ እፈራለሁ ሲሉ ጉዳት ሊያደርስብኝ ይችላል የሚሉትን ወገን ካልጠቆሙን በምን ዓይነት ዘዴ ልንረዳዎት እንችላለን ? » በማለት ከመፃፍ ተገትቶ በመገረም ሕሊናን ተመለከተ። በሀሰንና በሕሊና መሀከል በተፈጠረው ግጭት በገላጋይነት ከነበሩት ሰዎች ውስጥ አንድ አዛውንት ብድግ ብለው ፤

« ለምን ትደብቂያለሽ ? ምን ያለችው ነች እያ ? ተናገሪ እንጂ ! » አሉ በሕሊና ዝምታ በመናደድ ቆጣ ብለው ።

« ምኑን ነው የምናገረው ? ማን ብዬ ? » እጇን ዘርግታ ግራ በተጋባ መልክ ወደ አዛውንቱ ሰው ተመለከተች ።

« ንሳማ ፖሊስ ነገሩ ወዲህ ነው ። ቀደም ሲል እዚህ ቤት አምባጓሮ ተፈጥሮ ነበር » በማለት ለማስረዳት ሲሞክሩ ፖሊሱ አቋረጣቸው ።

« ቃሉ ከተበዳይ መምጣት አለበት ። የእርስዎ ምስክርነት እዚህ ላይ ሊሰፍር አይችልም ። ነገረ ፈጅ ነኝ የሚሉ ከሆነ በህጋዊ ፍርድ ቤት ውክልናዎ ሲረጋገጥ እንነጋገራለን ። መምህርት በደረሰብዎ በደል ተጠያቂ የሚሆን ወይንም የሚጠረጥሩት ግለሰብ የለም ነው የሚሉት ? » ሲል ፊቱን ወደ ሕሊና አዞረ ።

ሕሊና ጥቂት አሰብ አድርጋ « በአሁኑ ወቅት በእርግጠኝነት የማውቀው ሰው የለም ። ጥርጣሬዬ ግን ሊሆንም ላይሆንም ስለሚችል ቃሌን ለመስጠት በጣም እቸገራለሁ ። »

« በዕለት ሁኔታ ላይ የሰጡት ቃል ሰፍሯል ፤ ያንብቡት ።» በማለት ፖሊሱ በቅጹ ላይ የተሞላውን ወደ ሕሊና አሳለፈ ። ሕሊና አንብባ መጨረሷን እንዳረጋገጠ

« ይህ ቃልዎ ነው ። ፊርማዎን እዚህ ላይ ያስፍሩ ። በአካባቢው ላሉት ሮንዶች በዓይነ ቁራኛ እንዲጠብቁ አስፈላጊው ትዕዛዝ ይሰጣል ። »

* * *

ሕሊና በሀሳብ ተውጣ በፖሊስ ጣቢያው ውስጥ ስለተነሱት ጥያቄዎች አብሰለሰለች ። « ሀሰን ምን ብሎ ድንጋይ ይወረውራል ? ይህን መሰል ፀባይ ከዚህ ቀደም ሰምቼም አይቼም አላውቅም ። እኔን ለመጉዳት ቢፈልግ እንደያዘኝ ለምን አልደበደበኝም ነበር ? ። . . . ፈፅሞ ሀሰን ምንም ያህል ቢናደድ የዚህ ዓይነት ነገር በእኔ ላይ አይፈፅምም ። » በማለት ሀሰን በትግሉ ወቅት የያዛትን የእጇን ክፍል ዳሰሰች ።

« ሀሰን እንደዚህ ጨክኖ በጉልበት ይዞኝ አያውቅም ነበር ፤ ምን ነካው ? ለምን እንደዚህ ያደርጋል ? » አበራ የሕሊናን አቤቱታ በፀጥታ አዳመጠ ።

« እንዳልሽው ሀሰን ይኼን የሚያደርግ አይመስለኝም ። » አለ ሕሊና ያለችውን በማረጋገጥ « እርግጠኛ ነሽ ከሌላ ሰው ጋር ምንም ግጭት የለሽም ? » በማለት ጠየቀ ። ሕሊና ሀሳቧን በማንበብ ዓይነት ጥቂት ተከዘች ። እራሷን በአሉታ ነቀነቀች ።

« ከሀሰን ሌላ እኔ የማውቀው ወይም የማስታውሰው ምንም ጥል የለኝም » አለች በእርግጠኝነት ።

« ከሀሰን ሌላ ይህን ሁኔታ የሚፈታ ከሌለ ብጠይቀው ፈቃደኛ ነሽ ? » በማለት አበራ ጠየቃት ።

« ለምን አንተወውም ። አንተን እዚህ ውጣ ውረድ ውስጥ ማስገባት አልፈልግም:: »

« ስለ እኔ አታስቢ ። ሀሰንና እኔ እኮ በቀላሉ መወያየት



የምንችል መሰለኝ . . . » አላት ። ዝም አለችው ። አበራ ቀጠለ « ምን ዝም ትያለሽ ? ይኼ እኮ በዝምታ የሚታለፍ ቀላል ነገር አይደለም ። ጠላትሽን ማወቅና መለየት አለብሽ ። አለበለዚያ ነገ የሚፈፀምብሽን ወንጀል በምን ልታውቂ ትችያለሽ ። ደግሞ አይዞሽ ። እኔ ምንም አልሆንም ። »

« አበራ በእኔ ሀጢያት አንተን ልማግድህ አልፈልግም . . . » አለች እያመነታች ። አበራ ጊዜ አላጠፋም ከሕሊና ተሰናብቶ ሀሰን አለበት ብሎ ወደአመነበት ሆቴል አመራ ። ከሀሰን ጋር በሠላም ጨረሱ ።

« ሕሊና ልክ ነሽ ፤ ሀሰን አይደለም ። ጠየኩት ። አንቺ ጋ የመጣው ስለአጠፋው ጥፋት ይቅርታ ሊጠይቅሽ ነው እንጂ ለሌላ ጉዳይ አልነበረም ። እስላ የቆየውም አንቺን በግል አግኝቶ ይቅርታ እስከሚጠይቅሽ ነበር ። ጉዳዩን ስነግረው በጣም ነው ያዘነው ። የእኔ እዚህ መሆን የሚያስፈራት ከሆነ ዛሬውኑ ለቅቄ እሄዳለሁ ብሏል ። በእኔ ግምት ወርዋሪው ሀሰን አይደለም ። ሕሊና ጉዳዩን እስከምናጣራ ለምን ከእኛ ጋር አትሆኚም ? ቤቱ እንደሆነ ለሁላችንም ይበቃል ። »

ሕሊና መልስ ከመስጠት ተቆጠበች ። መልስ ለመስጠት የተቸገረችበት አንዳች ነገር እንዳለ ተረዳ « ለምን አትናገሪም ! »

« እምቢ ማለት አልፈልግም ፤ እንዳላስቀይምህ ። አበራ እዚህ ብሆን ምንም አይነካኝም ። አሁን በርትቻለሁ ። ሌላው ደግሞ ይህን የሚያደርጉ ሰዎችን በዓይኔ ማየት እፈልጋለሁ ። ከዚህ ከሄድኩ ማየት አልችልም » ስትል ተሟገተችው ።

« ብቻ ምን ጊዜም ለመምጣት ከፈለግሽ በሩ ክፍት ነው » አላት በሀሳቧ መፅናቷን ከተረዳ በኋላ ።

«አበራ ስለሰጠኸኝ ድጋፍ በጣም ነው የማመሰግንህ ፡፡ በጣም ነው ያኮራኸኝ ፡፡ ሌላም ነገር ብሆን አጠገቤ ተቆርቋሪ ሰው እንዳለ ተማመንኩ ፡፡ እግዝአብሔር ውለታህን ይክፈልህ ፡፡ »

« ምስጋናው በዛብኝ ፡፡ በጣም ሞቀኝ ፡፡ » አለ አበራ የሰራውን አጋና እንደትልቅ በመቁጠሯ ፡፡ « ሒሊና ለእንቺ መቼም ብርጭቆ ቢያቀብሉሽ እንደ ትልቅ ድጋፍ ነው የምትቆጥሪው፡፡ እንቺና እኔ እኮ ከእንግዲህ ሥጋና ደም ነን ፡፡ በነገራችን ላይ መስፍን የጠየቀው ጥያቄ እንዴት ሆነ ? »

« እርሱ የማይጠይቀው ነገር የለም ፡፡ ስለየትኛው ጥያቄ ነው የምታወራው ? »

« ከሁሉም ስለሚበልጠው ጥያቄ ! አትሽኮርመሚ ፡፡ ስለምን እንደማወራ ታውቂያለሽ ፡፡ »

« ምን ብዬ እመልስለታለሁ ፡፡ እኔ እኮ አበራ ሁሉ ነገር ተፋጠነብኝ ፡፡ ነገሮች ሁሉ በአንድ ጊዜ ሊመጡ የማስበው ሁሉ ተምታታብኝ ፡፡ »

« እሺ ወይም እምቢ ማለት ይህን ያህል ጊዜ እያስፈልገውም፡፡ ይልቁንም ስመምጣት እያቀደ ስለሆነ ቶሎ ዓፊለትና አስፈላጊውን ነገር ቶሎ ቶሎ ፈፅመን ተያይዛችሁ ወደ እዚያው ብትሄዱ ጥሩ ነው ፡፡ እኛም የግል ህይወታችንን እንኑርበት ፡፡ »

ሒሊና በሀሳብ ተውጣ ከአበራ ራቀች ፡፡ የእባቷ ማስታወሻ ከሆነው መጥረቢያ መለየት አትፈልግም ፡፡ ሌላው ደግሞ እማማ በላይነሽ ከያሬድ ጋር ለጊዜው ይኑሩ እንጂ ኃላፊነቱ የራሷ እንደሆነ አሰላሰለች፡፡ ከያሬድ ጋር ያላትን ግንኙነት መቋጫ ሳታደርግለት እንደዚሁ እንደተንጠለጠለ መተው ለያሬድም ለራሷም እንደማይበጅ አመነች ፡፡ የእክስቷ የእማሆይ አባይነሽ ጉዳይም በጥቂቱ አሳሰባት ፡፡ ከሁሉ በላይ ግን አጥብቆ ያሳሰባት ከማታውቀው ሰው ጋር ተያይዛ ወደማታውቀው ሀገር ተጠቃላ የመሄዱ ጉዳይ ነበር ፡፡



መስፍንን በመልክ ያየችው ለሁለት ቀናት ነው ፡፡ አብዛኛው ትውውቃቸው በመፃፃፍ ላይ የተመሠረተ ነው ፡፡ እንደ ወንድሙ አባባል መስፍን ከቤተሰቡ ሁሉ ለየት ያለና የራሱ የኑሮ ዘይቤን የሚከተል ሰው ነው ፡፡ ባደረጉት የፅሁፍ መለዋወጥ ምንም ያህል የናረ ግጭት ባይኖራቸውም በአስተሳሰብ ርቀት እንዳላቸው ለሒሊና ግልፅ ነበር ፡፡ ለማንኛውም መስፍን ሃሳቧን እንድትቋጭና መልሱን በቶሎ እንድትፅፍለት ስለአሳሰባት ጉዳዩን ለብዙ ጊዜ ማዘግየት እንደማትችል አሰበች ፡፡ ነገሮች የተበታተኑ ቢሆንም ይህ ዕድል የትምህርት ጥማቷን ለማርካት እና ለወደፊቱ የኑሮዋ ማማር ወሳኝነት እንዳለው ገመተች ፡፡ ስለ ጉዳዩ ያወቁ የቅርብ ጓደኞቿ « ዕድለኛ ነሽ ምነው እንችን ባደረገኝ » በማለት ለመሄድ ያላትን ጉጉት አሰፉላት ፡፡

« ሁሉንም ጥሎ መሄድ ከኃላፊነት መሸሽ አይደለም ፡፡ ለምን እንደዚህ እንደማስብ አላውቅም ፡፡ በሄድኩበት ሁሉ የቅርብ ሰዎች ሀሳብ አብሮኝ ይጓዛል ፡፡ ከዚህ ሄድኩ ማለት ራቅኳቸው እንጂ በሀሳብ እርግፍ አድርጌ ከአልተውኳቸውም እዚህ ሆኜ የምረዳቸውን ያህል እዛም ሆኜ ማድረግ አልችልም ? » ስትል አሰበች ፡፡ ወደ ኋላም መለስ ብላ ያሬድ ወደ ጀርመን ለትምህርት በሄደበት ጊዜ እንዴት በወኪል እርሷንና ወ/ሮ በላይነሽን ሲረዳ እንደነበረ አስታወሰች ፡፡ ዘዴውን መጠቀም ይቻላል ፡፡ ማን አለ የሚታመን ፣ የእኔን ዘመዶች በውክልና ሊረዳ ፈቃደኛ የሚሆን ? » የመጀመሪያው ሰው በኃላፊነቱ ብቁ ነው ብላ ያቀረበችው አበራን ነበር ፡፡ « ግን እርሱ ደግሞ ብዙ ውክልናና ኃላፊነት ያለበት ሰው ነው ፡፡ በእርግጥ ብጠይቀው እሺ ብሎ ይቀበላል ፡፡ ሆኖም በእኔ በኩል ትክክል አይሆንም » ብላ ሀሳቧን ሰረዘች ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ያሰበችው ሰው ከበቡሽን ነበር ፡፡ « ከበቡሽ ሴተላጤ ነች ፡፡ ለመሰላት ግን ቁም ነገረኛ ነች ፡፡ እንዲያውም

ስሜቱ አሸንፎት በጉንጮቹ ላይ እንባው መውረድ ጀመረ ። በአድራጎቱ የተደናገጠው አበራ ወንድሙን በማፅናናት ከዳሱ ይዞት በፍጥነት ወጣ ። ወደ መኖሪያ ቤት ገቡ ። መስፍን ለቅሶውን ሊገታ አልቻለም ።

« አባቴ ፣ እናቴ . . . ምነው የዛሬዋን ቀን አብራችሁኝ ሆናችሁ ደስታዬን በተካፈላችሁ ። » በማለት ሥማቸውን በመጥራት አለቀሰ ። አጠገቡ የነበሩት አበራና ሕሊና ራሳቸውን በማጠናከር ሊያፅናኑት ሞከሩ ። ሕሊና በማፅናናቱ ብዙም አልገፋችም ። የመስፍን እባባል ብሶቷን አንሮት እንባዋ መርገፍ ጀመረ ። በቤቱ ውስጥ ሕሊናንና መስፍንን ተከትለው የገቡት ሰዎች በአፅናኝና ተፅናኝ ተከፈሉ ። በማጀት አካባቢም ምግብና መጠጥ በማቀበል ላይ የነበሩት የመስፍን እህቶች ተደናግጠው ወደ ሳሎን ተሯሯጡ ። የወንድሞቻቸውን ለቅሶ እንደሰሙ ሁሉም ተቃቅፈው ሀዘናቸውን ገለጹ ። የታላቅ ወንድማቸው የሙሉጌታ ድምፅ ነበር ለቅሶውን ያቆመው ።

« ዋት ኢዝ ጎይንግ ኦን ? ምን ነካችሁ ? ሼም ኦን ዩ » ሙሉጌታ ድምፁን ከፍ አድርጐ ተናገረ ። ወደ መስፍን ፊጥኖ በመሄድ « ዜይ ዲዘርቭ ቤተር ! ምን ሆንክ ብለህ ነው የምታለቅሰው? እነርሱን በዚህ ወቅት በፀሎት ማስታወስ ነው እንጂ መልሰህ ልታመጣቸው ነው ? ምን ዓይነቱ ነህ ? » ሙሉጌታ በመናደድ መስፍንን በእጆቹ ይዞ ነቀነቀው ።

« አይ ካን ኖት ኸሪቴንድ ። እራሴን ለማባበል ብሞክርም አልቻልኩም ። ውስጤ ነደደ ። አባዬና እማዬ ቢኖሩ ኖሮ የዛሬው ደስታዬ እጥፍ ይሆን ነበር ። የእነርሱ አለመኖር ደስታዬን ግማሽ አድርጎት ። ቁጭቱ አልወጣልህ አለኝ » አለ መስፍን ዓይኑን እየጠራረገ ።



« አንተን የሚሰማህ ስሜት እኔን አይሰማኝ መሰለህ ? የእነርሱ ያለመኖር ሁላችንንም ይቆጨናል ። ሆኖም መፅናናት ያለበህ እነርሱ የሚፈልጉትን ከግብ ለማድረስ በመቻልህ መንፈሳቸውን ደስ እንዳሰኘህ መቁጠር አለብህ ። የአንተ ለቅሶ ለራስህ አዝነህ ሌላውንም ማሳዘን ነው ። ከአሜሪካን ሀገር እዚህ ድረስ የመጣነው መላው ቤተሰቡ የደስታህ ተካፋይ እንዲሆን ነው እንጂ ሙሾ እንድታወርድ አይደለም ። ስማ መስፍን ! ቤተሰቡ ከዘመናት ሀዘን በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘው ደስታ ነው ። ለእነርሱ ይህ አዲስ ምዕራፍ ነው ። ለወደፊቱ በዚህ እንዲገፋ አግዛቸው ። በል ውጣ ወደ ዳሱ ሰው እየጠበቀህ ነው ። »

ሙሉጌታ ወደ ሕሊና ዞር አለ ። እርሷም ብትሆን ፊቷ ቀልቶ ፣ ዓይኖቿ ዕንባ አዝለው ፣ አፍንጫዋ ተዘግቶ ሳግ ይተናነቃት ነበር ። ወደ ሙሉጌታ እያየች « ይቅርታ እራሴን መቆጣጠር ስላልቻልኩ ነው » አለችው ።

« አንቺ ደግሞ ተው ብለሽ እንደማፅናናት ነገር ታባብሻለሽ ? ። » በታላቅ ወንድሙ ግሳፄ ሁሉም በየፊናቸው ሲበታተኑ ሕሊናና መስፍንም ተያይዘው ወደ ተጣለው ድንኳን ገቡ ።

የድንኳኑ ግብር ቀደም ሲል በተከሰተው ለቅሶ አልተረበሸም ። አዲስ ገቢው በምግብና በመጠጥ ሲስተናገድ የነሸጠው ደግሞ መሀል በከበባ ወደ ደመቀው ዙፈን ተቀላቀለ ። የቀሰበቱ ድግስ ጉድ እየተባለ ከሚነሱት ከመንደሩ ወሬዎች አንዱ ሆነ ። በሽርሽሩ ወደ ሃያ ሦስት መኪና የተሳተፉበት ፣ የአሰላ ከተማ ዳር እስከ ዳር የተጠራበት ፣ በሥም ቀሰበት ተባለ እንጂ ለመስፍንና ለሕሊና ሌላ ድግስ እንደማይኖር ግልፅ ነበር ።

ሕሊናን ወደ አሜሪካን ለመውሰድ መስፍን ህጋዊ የጋብቻ ወረቀት ከማመልከቻ ጋር ማስገባት አለበት ። ዋናውን የጋብቻ ወረቀት ከአራት ቀናት በኋላ ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ተቀበሉ ።

« በቃ አለቀ ማለት ነው ? » አለች ሕሊና የጉዳዮ መፋጠን አስገርሟት አብረዋት የነበሩትን አበራና መስፍንን አፈራርቃ እያየች::

« ሌላ ምን ትጠብቂያለሽ ፤ ዋናው ይህ ነበር :: በቀላሉ አለቀልን » አለ መስፍን ::

« ይህስ አለቀ የሚቀጥለው ደግሞ ምንድን ነው ? » ሲል አበራ መስፍንን ጠየቀው ::

« ከዚህ በኋላ በኤምባሲው በኩል ፕሮሰስ ማድረግ ነው :: ኤምባሲ ከመግባቱ በፊት ግን እኔ ማመልከቻውን በመኖሪያ ቦታዬ ሆኜ ማስገባት አለበኝ :: » ከባድ ይመስላል አይደል ? የእኛን ሀገር ውጣ ውረድ ካለፍን ሌላው እንኳ እስከዚህ አይከብድም » አለ መስፍን ::

« ስንት ጊዜ ይፈጃል ከዚህ በኋላ ? » ሕሊና መስፍንን ጠየቀችው ::

« ከሦስት እስከ ስድስት ወር ከዚያ እንግዲህ ጓዝሽን ጠቅልለሽ መምጣት ነው :: » አለ መስፍን ፈገግ ብሎ ::

« እኔ አላምንም ስድስት ወር ብቻ ! » ሕሊና አፏን ከፍታ በመገረም ዓይነት አበራን አየችው ::

« ምነው ለመሄድ ቸኮልሽ እንዴ ? » አላት አበራ ::

« ችኩላ አይደለም :: በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መፈፀም ያለብኝን ነገሮች ሳስብ . . .ጊዜው እንዴት እንደሚበቃኝ አላውቅም! »

« ሀሳብ አታጨሺም ደግሞ ምን ቀረ ? ሥራ ብዙ ነሽ » አለ አበራ፤ ሕሊና ያሰበችውን እንድትናገር በመገፋፋት ::

« እማማ በላይነሽ ፤ የእክስቴ የድሮው ቤት መታደስ አለበት፤ እዚህ በጅምር የቀሩትን ነገሮች ቦታ ቦታ ማስያዝ አለብኝ :: » በማለት ሀሳቧን በጥቅሉ አካፈለችው ::



« ታዲያ ይህን ለማድረግ አንቺ እዚህ መኖር አለብሽ ? በወኪል ሊሰራ የሚችል ነገር እኮ ነው » አለ አበራ አነጋገሩ መስፍንንም ጉዳዩ እንደሚመለከተው አድርጎ ::

« ሕሊና መቼም ስለቤተሰቦችሽ የነገርሽኝ ነገር በጣም የሚያሳዝን ነው :: ሆኖም ይህ ችግር በአንድ ቀን የሚቀረፍ ጉዳይ አይደለም :: አብሮን የሚኖር ጉዳይ ነው :: ስለዚህ አሜሪካ እሄዳለሁ ብለሽ ካሰብሽ ሆድሽን ሠፋ ማደረግ አለብሽ :: ብዙ ነገሮችን በአንድ ጊዜ ለማስተካከል ባትችዪ እንኳን ቀስ በቀስ የሚሆን ይመስለኛል ::»

« መስፍን እዚህ ላይ ልክ ነህ :: ስለ ቤቱ ተነጋግረናል :: ዝርዝሩን ከበቡሽ ባለችበት እንነጋገራለን :: ብዙ የሚያሳስብሽ ነገር የለም :: አሜሪካን ሄድሽ ማለት ሠማይ ቤት ገባሽ ማለት አይደለም:: በየጊዜው ብቅ  ማለት ትችያለሽ » ብሎ ወደ መስፍን ተመለከተ ፤ ከእርሷ የበለጠ ጉዳዩ የመስፍን እንደሆነ ለማረጋገጥ ::

* * *

መስፍን ጉዳዩን ፈፅሞ ወደ አሜሪካ ከተመለሰ በኋላ ሕሊና ኑሮዋን ለመለወጥ ከመስፍን ቤተሰቦች ጋር ተቀላቀለች :: ኑሮዋ ያበበ፣ የፈካና በቤተሰቡም ተደማጭና ተወዳጅ ሆነች :: ቤተሰቡ በእርሷ እርሷም በቤተሰቡ ችግር ላይ መወያየትና ድጋፍ መስጠት ልማዳዊ የቀን ተቀን ህይወቷ ሆነ :: የመስፍን ደብዳቤ ፣ ሌላም ለቤተሰቡ መከፋፈል ያለበት ገንዘብ የሚላከው በሕሊና ሥም ሆነ :: አማከለች ሕሊና ወደ አሜሪካ ስትሄድ አብራ ለመሄድ ተስፋ በማድረግ ከሕሊና ጋር ያላት ቅርበት ከምንጊዜውም የበለጠ ተጠናከረ::

« አንድ ትልቅ ምስጢር ብነግርሽ ለማንም አትናገሪም ? » አለች አማከለች አጠገቧ ተቀምጣ ለነበረችው ሕሊና ::

« ምንድነው ምስጢሩ ፤ የፈራሁት ነገር እንዳይሆን » አለች ሒሊና ዓይኖቿን አፍጥጣ አፏን ከፍታ ::

« ስለ እኔ አይደለም ፤ ስለ አንቺ ፤ ስለ ራስሽ ነው :: ከብዙ ጊዜ በፊት የተፈፀመና ያለፈ ነው :: »

« አሁን በዚህ ጨዋታ መሀከል ለምን አመጣሽው ? የምናወራው ስለ አንቺ ቦይ ፍሬንዶች ነው » አለች ሒሊና የነገሩን አለመገጣጠም በመጠራጠር ::

« እሱን ልነግርሽ ነው :: ስለ መሬሳና እኔ ጥል ስነግርሽ ሁሉን ነገር አልነገርኩሽም :: የተጣላነው ከእርሱ ጋር አልሆንም ስለአልኩ አይደለም :: እርሱ ነው የመጀመሪያ እውነተኛው ቦይፍሬንዴ :: »

« አረገዝሽ እንዴ ? » ስትል ሒሊና ጠየቀች :: አማከለች ራሷን በእሉታ ነቀነቀች ::

« ስለእሱ አይደለም የማወራልሽ :: እንዴት ብዬ ልጀምርልሽ ? » አለች አማከለች እጆቿን እያፍተለተለች ::

« ምን አስጨነቀሽ ? ተናገሪውና ይውጣልሽ » ሒሊና አማከለች እንድትናገር ገፋፋቻት ::

« እንዳትናደጂ ፤ እንዳትቆጪ ቃል ግቢልኝ »

« እባክሽ አትጨነቂ እኔ ለማንም አላወራም »

« ያኔ ድንጋይ የተወረወረብሽ ጊዜ ታስታውሻለሽ » አማከለች መሬት መሬት ተመለከተች « እነ መሬሳ ነበሩ ያኔ የወረወሩብሽ »

« ምን ! ለምን ? »

« መሬሳ እኔ አሜሪካ ስሄድ እኔን ተከትሎ የመውጣት ሀሳብ ነበረው :: በመሀል የአንቺ መምጣት ጋሼ መስፍን እኔን ለመውሰድ የገባውን ቃል አጨለመው :: ታዲያ መሬሳና ጓደኞቹ ይህንን ሲሰሙ ቆይ እንሰራላታለን ብለው ሲፎክሩ ነበር :: ሒሊና እመኚኝ እኔ እዚህ



ውስጥ አልነበርኩበትም :: በወቅቱ መሬሳ ሲነግረኝ በጣም ነው ያናደደኝ :: »

« የመስፍንን እና የእኔን ግንኙነት እንዴት ሊያውቅ ቻለ ? » አማከለች ጥያቄውን መመለስ አልፈለገችም :: ዓይኖቿን ሰበረች :: የሒሊና ጥያቄ አሳፈራት ::

« እንዴት እንደዚህ ያደርጋል ? እኔ መሬሳ በጣም ጥሩ ልጅ ነው እያልኩ ሁልጊዜ ከአበራ ጋር እጣላለሁ :: አሁንም አበራ ፈፅሞ አያውቅም ፤ ይጠራጠራል እንጂ :: ሒሊና አደራ አበራ እንዳያውቅ:: መሬሳ እንደሆነ ብዙ ዱርዬ ጓደኞች አሉት ከነገርሽው ይገዳደላሉ :: »

« ምን ብዬ እነግረዋለሁ ? »

« ምናልባት ሳታውቂ በጨዋታ መሀል ለአበራ እንዳትነግሪው ብዬ ነው :: አየሽ በጊዜው ይህ ነበር ያጣላን :: ከዚያን ቀን በኋላ ከእርሱ ጋር መውጣቱን አቆምኩ :: እገድልሻለሁ ብሎ መሄጃ መቀመጫ ሲያሳጣኝ ከእነ ሳምሶን ጋር መሆን ጀመርኩ :: የእነ መሬሳ ግሩፕ የእነ ሳምሶምን ግሩፕ በጣም ስለሚፈሯቸው ሳምሶን አነጋግሮት ነው መሬሳ አፉን የዘጋው እንጂ ሊደበድበኝ ፈልጎ ነበር::»

« እኔንስ ይበለኝ :: ግን አንድ የዋህ ሰው በመሀል ቢጎዳ ኖሮ ያሳዝን ነበር » አለች በድፍኑ ::

« እነ ሳምሶን ዋጋቸውን ለጥተዋቸዋል »

« ምን ማለትሽ ነው ? »

« አንድ ወቅት ላይ ት/ቤት ለሁለት ወራት በተከታታይ የቀረ ጊዜ እኮ ተደብድቦ ነው ሆስፒታል ተኝቶ የወጣው :: እነ ሳምሶን ለሦስት ቀን ታስረው በሽማግሌ ነው የታረቁት :: »

« በእኔ ምክንያት እንዳይሆን ? »

« እ . . . እ . . ርሱ ብቻ አይደለም :: እኔንም መንገድ ላይ እየጠበቁ በድንጋይ ሲያሯሩጡኝ ነበር :: »

« ለአበራ አትነግሪውም ነበር ? »

ፖሊስ ወደ አሳያት አቅጣጫ ተራመደች ። የምታውቀውን እየራቀች ወደማታውቀው ቀረበች ። አዲሱን መስክ እያሰሰች በማረፊያ ቤቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ቃኘች ። ወጣት ፣ ሽማግሌ ፣ ደካማ ፣ ጎበዝ፣ አንዱ ሌላውን እያገዘ ወደ ፊት ተጓዘ ። የፍተሻውን ቦታ አልፈው የመጨረሻ ማረፊያ ቦታ ደረሱ ። አጠገቧ የነበሩ አዛውንት ሴት ነበሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተሳፋሪዎች ውስጥ ያነጋገሯት ።

« አይዞሽ ልጄ አይዞሽ ! እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ ስሄድ ሆዴ ባብቶ ጨለማ ነበር የመሰለኝ ። አሁን ይኸው የውጋ መንገድ አድርጌው በየዓመቱ እመላለሳለሁ ። »

ሕሊና እኚህን አዛውንት ቀደም ብላ በግርግሩ ወቅት በመሸኘት ላይ እንዳሉ አስታወሰች ።

« አይ እማማ ከባድ ነው ። የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው ። . . . እርስዎ ወዴት ነው የሚሄዱት » ስትል ጠየቀች ።

« ወደ ልጄ ነው ። ልጄ አሜሪካ ሀገር ነው የሚኖረው ። »

«ታዲያ ብቻዎትን ? » ሕሊና መገረሟን መደበቅ አልቻለችም።

« ምን አለ ብለሽ ነው ሁሉም ነገር የተዘጋጀ ነው ። ግራ የሚገባ ነገር የለም » አሉ ።

« ጎበዝ ነዎት ። »

« አንቺም አንድ ጊዜ ካየሺው ትለምጂዋለሽ ። »

የአይሮፕላኑ አስተናጋጅ የመተላለፊያ በር ከፍታ ተሳፋሪዎች ቦርዲንግ ፓስ እንዲያዘጋጁ ጠየቀች ። ሁሉም ተሰልፈው የቁጥጥሩን በር እያለፉ ወደ አይሮፕላኑ በሚያደርሳቸው አውቶቢስ መሳፈር ጀመሩ ። ሕሊና ሥሟን ከሩቅ የሚጣራ ድምፅ ሰማች ። ድምፅ ከወደመጣበት አቅጣጫ ተመለከተች ። ሆኖም ምንጩን ማግኘት አልቻለችም ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጥሪው ቀጠለ ።



ሕሊና ወደ አቅጣጫው በማየት ላይ እንዳለች አጠገቧ የነበረው አንድ ወጣት የድምፁን ምንጭ ጠቆማት ። ሕሊና ጥቂት አመነታች ። ሰገነቱ ላይ በርቀት የቆመውን ሰው በቅጡ ልትለየው አልቻለችም ። እጇን ከዓይኖቿ በላይ ጥላ ለማነጣጠር ሞከረች ።

« ያሬድ ነኝ ! ያሬድ ነኝ ! »

ሕሊና የሰማችውን አላመነችም ። እጆቿን አወራጭታ ። ወደ ልቧ ሰበሰበች ። አፏን በመዳፏ ሸፍና ባግራሞት ፈዛ ቀረች ። እንባ እየተናነቃት በአድራጎቷ በከፊል የውስጥ ስሜቷን ለመግለፅ ሞከረች ። እጆቿን ወደ ሠማይ ዘርግታ ሰላምታ በመስጠት ዓይነት አውለበለበች ።

« ጋሼ ያሬድ ! ጋሼ ያሬድ ! » ብላ ደጋግማ ተጣራች ። ዓይኖቿን ያሬድ ላይ ተክላ በድን ሰውነቷን እየጎተተች አውቶቡሱ ውስጥ ገባች ።

ሕሊና የራሄል አድራጎት እየገረማት ወደ ሻወር ገባች ። ይሆናል ስትል ለማሰብ ሞከረች ። የራሄል ቀልጣፋነትና ግልፅነት ለኢትዮጵያውያን አዲስ እንደሆነ ስታስብ ከበቡሽ ታወሰቻት ። ከበቡሽ በትምህርት ቤት አካባቢ በነበረችበት ወቅት ከራሄል ጋር በብዙ ነገራቸው እንደሚመሳሰሉ ገመተች ። ሕሊና ከሻወር እንደወጣች ልብሷን ለብሳ ፀጉሯን ስታበጥር ራሄል የሕሊናን ልብስ ቁም ሳጥን ውስጥ በማደራጀት ላይ ነበረች ።

« ይሄ በጣም የሚያምር ልብስ ነው መቼም ውድ መሆን አለበት » አለቻት ራሄል አንድ የሀበሻ ጥበብ ቀሚስ በእጆቿ ይዛ አገላብጣ እየተመለከተች ።

« ያምራል አይደል ? ግን የሚገርምሽ በጣምም ውድ አይደለም ። ወደ ሦስት መቶ የኢትዮጵያ ብር ነው የከፈልኩት » አለች ሕሊና ፊቷን ከመስታወቱ ሳታዞር ፀጉሯን እያበጠረች ።

« አ - ያ - ሦስት መቶ ብር ብቻ » አለች ራሄል በመገረም።

« አዎ ሦስት መቶ ብር ብቻ ነው ። ከወደድሽው ልትወስጂው ትችያለሽ እኔ ሌላ አለኝ » አለቻት ።

« ኦ ኖ ምን ማለትሽ ነው ? ለምን ትሰጭኛለሽ ። አሜሪካን ሀገር በነፃ መስጠት የለም ። ባይሆን ትርፍ ከለሽ እገዛሻለሁ ። »

ሕሊና ግማሽ ልብሷን በማውለቅ ላይ እንዳለች የመኝታ ቤቱ በር ተንኳኳ ።



*   *   *

መስፍን መታጠቢያ ክፍል እንደገባ ሕሊና ሰውነቷን ለማሳረፍ ሶፋ ላይ ተጋድማ ከራሷ ጋር ሀሳብ ውስጥ ገባች ። አሜሪካ ሀገር መኖሯ ህልም እየሆነባት በተራመደች ቁጥር የምታያቸው አዳዲስ ነገሮች ሀሳቧን በመሻማት ስለ ግል ኑሮዋና ከመስፍን ጋር ስለአላት ግንኙነት በቅጡ እንዳታጤን አደረጓት ። ከመጣች ሦስት ሣምንታት ሆኗታል ። በዚህን ጊዜ ውስጥ ከመስፍን ጋር ጠዋት ከቤት የወጡ የሚመለሱት ሲመሽ ነበር ። አልፎ አልፎም በመስፍን ጓደኞች በሚደረግ የመልስ ጥሪ በመገኘት ለጓደኞቻቸው ያላቸውን አክብሮት በመግለፅ አሳለፉ ።

ሕሊና ለአሜሪካን ኑሮ ካላት ታላቅ አድናቆት ባሻገር የተፈታተናት የአሜሪካን ሀገር ምግቡ ነበር ። ዶሮው ፣ ሥጋው ፣ እንቁላሉ በአጠቃላይ ጣፋጭነት የበዛው ምግብ ከለመደችው ኮስተር፣ ጠንከር ካለው የሀገር ቤት ምግብ ጋር ሊመሳሰልላት አልቻለችም ። በተፈጥሮ የተገኘ ለመሆኑ ተጠራጠረች ። መስፍን ታጥቦ የቤት ልብሱን ለውጦ ወደ ሳሎን ሲገባ ሕሊና በፈገግታ ተቀበለችው ።

« ጺምህን ለምን ተላጨኸው ? በጣም ነበር የሚያምርብህ » አለች የቀድሞ ፊቱ መለወጡን አይታ ።

« ለለውጥ ያህል ብዬ ነው » በማለት የተላጨ ፊቱን በእጁ እያሻሸ ፈገግታውን ለገሳት ።

« ራትህን ላቅርብልህ ? » ሕሊና ከተጋደመችበት ተነስታ ወደ ኩሽና ስትሄድ ፣

« አንቺስ አትበይም ? »

« እኔ ቀን የበላሁት እስካሁን አልጎደለም ። »

« ቀን መቼ በላን ? ጠዋት ቁርስ ያደረግነውን ነው ? » መስፍን ለማረጋገጥ ወደ ሕሊና ተመለከተ ::

« የዚህ ሀገር ቁርስ የእኛ ሀገር ምሳ ነው :: »

« ሃኒ እዚህ ሀገር ምግብ ካልበላሽ ጥሩ አይደለም :: አሁን እንኳ በጋ ነው በክረምቱ ወቅት መንቃነቅ አትችይም :: ከአሁኑ መልመድ አለብሽ » አላት ::

« ምግቡ በጣም አስጠልቶኛል :: ከዳቦ በስተቀር ሌላው ነገር ሁሉ አልዋጥልሽ እያለ አስቸገረኝ :: ቢሆንም ለመልመድ እየሞከርኩኝ ነው :: »

« አይዞሽ ትለምጂያለሽ :: አብዛኛው ሰው አዲስ እንደመጣ ይህ ችግር አለበት » አለ መስፍን ጭንቀቷን ከፊቷ ላይ እያነበበ ::

ሕሊና ኩሽና ውስጥ ጉድ ጉድ ብላ የተቻላትን አብስላ እራት አቀረበች :: መስፍን እያደነቀና እያጣጣመ ተመገበ ::

« መቼም ዕድለኛ ነኝ ሃኒ :: ይህን የመሰለ ምግብ መብላት ከተመኘሁ ቆየሁ :: አሁን እውን ሆኖ በራስ ሰው ሲዘጋጅና ሲቀርብ እንዴት ደስ ይላል በማለት ሕሊናን ሳማት ::

« አይ ላብ ዩ » በማለት እጁን ለመታጠብ ወደ ውስጥ ገባ :: ሕሊና ገበታውን አንስታ የተበላበትንና የተጠጣበትን ሰሀንና ብርጭቆ አጣጥባ ተራዋን ወደ መኝታ ቤት ገብታ ልብስ ቀይራ ሳሎን ተቀምጦ የቴሌቪዥን ፕሮግራም የሚከታተለውን መስፍንን ተቀላቀለች :: የወቅቱ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለአዋቂዎች ብቻ የተዘጋጀ በግልፅ የሁለት ፍቅረኛሞችን ግንኙነት የሚገልጽ ትዕይንት ነበር ::

« አሁን ካልጠፋ ነገር ይህን ሙያ ብለው በቴሌቪዥን ያስተላልፋሉ ? » አለች ሕሊና ትዕይንቱን እየተሀየፈች ::

« ኦ ሃኒ ዋት ኢዝ ባድ አባውት ዚስ ? ይኼ እኮ ማንኛውም ጤናማ ሰው የሚያደርገውና የሚፈፅመው ነው :: መሳሳምና መተሻሸት ምን ነውር አለው ? » ሕሊናን በጥያቄ መልክ አያት ::



« ለሁሉም ቦታ አለው :: የሰው ልጅ የሚሠራውና የሚያደርገው ነገር ሁሉ አደባባይ መውጣት አለበት እንዴ ? » በማለት የቴሌቪዥኑ ትዕይንት እስከሚያልፍ ላለማየት ወሰነች ::

« እባክሽ ቁጭ በይ ሃኒ ፣ ፕሮግራሙ ካልጣመሽ እንደዚሁ እናውራ » አለ መስፍን ለመሄድ ስትቃጣ የሌሊት ልብሷን ይዞ እየጎተታት ::

« ስለዚህ ነገር አሁን ማውራት አልፈልግም :: » በእጇ ወደ ቴሌቪዥኑ እያመለከተች « ሌላ ምን ወሬ አለ ? » ጥያቄዋን ሳትጨርስ መስፍን በተጋደመበት ሶፋ ላይ ቁጭ አለች ::

« ጊዜ አግኝተን አልተጫወትንም :: እንዴት ነው አሜሪካን ተስማማሽ ? » ከዓይኖቿ ለማንበብ በመሞከር ዓይን ዓይኗን ተመለከተ ::

« አሜሪካን ጥሩ ሀገር ነው :: በሥልጣኔያቸው በጣም መጥቀው ሄደዋል ፣ ሀብታሞች ናቸው :: መቼም የእኔም ሀገር እንዲህ በሆነልኝ ብሎ ያስመኛል :: ከምግቡ በስተቀር ብዙ ነገር ተስማምቶኛል :: አንተስ ምን ይመስልሃል ? የለመድኩ አይመስልህም ? » ሕሊና መስፍንን ድንገት ጠየቀችው ::

« ሃኒ ኦፍ ኮርስ ኢት ኢዝ ዋን ሀንድረድ ፐርሰንት ሳክሰስ » በማለት ትከሻዋን መታ መታ አደረገ ::

« ለዚህ ሁሉ ስለ አበቃኸኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው :: ከዚህ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ለመግባት እዘጋጃለሁ » አለች ሕሊና ::

« ቴክ ዩር ታይም :: ትምህርት ቤት አሁን ዝግ ስለሆነ ጊዜው ሲደርስ ትመዘገቢያለሽ :: እስከዚያው ሀገሩንና ሰውን መልመድ ነው » አለ ምሥጋናዋን ከተቀበለ በኋላ ::

« ራሄል ቋንቋ ለማስተማር ምዝገባ እየተካሄደ ነው ፣ መጥቼ እወስድሻለሁ እዚሁ ቅርብ ትምህርት አለ ነው ያለችኝ :: ሥሙን እንኳ ጠርታልኝ ነበር » አለች ::

« ኦ ሃኒ ፤ የራሄልን ነገር ሲሪየስ አድርገሽ አትውሰጂ ። እርሷ የምትናገረውን አታውቅም ። ኢግኖር ኢት » በማለት በብስጭት ራሱን በእጆቹ ዳበሰ ።

« ምነው ያማታል እንዴ ? » ሒሊና በመስፍን አባባል ተደናግጣ ጠየቀችው ። እርሷም የጠረጠረችው ነበራት ።

« ኦ ኖ ሃኒ እንደእርሱ ማለቴ ሳይሆን መቼም እዚህ ሀገር የቆየ ሰው ዞር ያላለበት ማን አለ ። ክልቸር ሾክ ያልበታተነውና ያላቆሰለው ጥቂቱን ነው ፤ ማሰቴ ከአደግንበትና ከነበርንበት ወደ አዲስ ባህል ስንገባ ብዙ ውጣ ውረድ ስላለፍን ሳምታይምስ የምንለውን እንኳ አናውቅም ። » መስፍን ከራሄል አልፎ ሁኔታውን በማጠቃለል ተናገረ ።

« ሰውጥ ስትል ባህል ፤ አለባበስ ፤ አበላል ፤ አነጋገር ፤ አኗኗር . . . አልገባኝም ? » ሒሊና በጥሞና መስፍን እንዲያስረዳት ጠየቀች ።

« ያልሽውን ሁሉ ያጠቃልላል ። ሆኖም ከዚያም አልፎ ሌሎች ብዙ ነገሮችን ይመለከታል ። እንደህ በቀላሉ ማስረዳት የምችለው ነገር አይደለም ። እንግዲህ እዚህ ከመጣሽ ለወደፊቱ በየቀኑ አንችንም ያጋጥምሻል ። ያኔ ሁኔታውን ኢንዲቴል እናወራለን:: አሁን በቀላሉ ይኼ ነው ብዬ ባወራልሽ ለወደፊቱ ለሚያጋጥምሽ ሁሉ መልካም አስተሳሰብ አይኖርሽም ። » መስፍን የቴሌቪዥኑን አንቴና አስተካክሎ ተመልሶ ሶፋው ላይ ተቀመጠ ።

« መቼም አሁንም ይኼ ለውጥ የሚባለው እንዴት አድርጎ የሰውን ሁኔታ እንደሚነካ ለማወቅ እፈልጋለሁ ። ብዙ ጊዜ ሀገር ቤት ያሉ ሰዎች ውጪ ደርሰው ሲመለሱ ስለነበሩበት ሀገር ሲያወሩ ከባድ ነው ። ሁሉ ነገር አለ ግን የባህሉ ግጭት ከፍተኛ በመሆኑ መኖር አልቻልንም » ይላሉ ። እስካሁን እንዳየሁት ከሆነ ይህን ያህል



የሚያስመርር አይደለም ። » አለች ሒሊና ጥያቄውን በሀሳብ መልክ ለመስፍን በማካፈል ።

« ሃኒ ዶንት ሃሪ ፤ ትደርሺበታለሽ ። ለካስ ክልቸር ሾክ ማለት ይኼ ነበር ? » በማለት ራስሽ ይገባሻል ። እኔ መቼም አሁን ይኼ ነው ብዬ አልነግርሽም ። እሱን ያለፈ ሰው እዚህ ሀገር የመኖር ዕድሉ ሠፊና ብሩህ ነው ። ከባዱ ያቺን ወቅት በትዕግሥት ለማለፍ መቻል ነው » አለ ድካም በተጫጫነው ድምፅ ። ሒሊና የመስፍንን መዳከም በመገንዘብ የሳሎኑን መብራት አጥፍታ ወደ መኝታ ቤት ገባች ። መስፍን ጥቂት የቴሌቭዥን ዜናዎችን አዳምጦ ሒሊናን ተከተላት ።

ሒሊና ለመጀመሪያ ጊዜ ለብቻዋ ቤት ውስጥ ሥራ በመሥራት ጊዜዋን አሳለፈች ። መስፍን ወደ አዲስ የሥራ ቦታው ሄዶ የሚመለሰው መሸትሸት ሲል ነው ። የቤት ሥራዋን ፈፅማ በሻንጣ ውስጥ የቀሩትን የሀገር ቤት ዕቃዋን ቦታ ቦታ ማስያዝ ጀመረች ። ሁለቱ ትላልቅ ሻንጣዎች ውስጥ የነበሩትን ዕቃዎቿን በታትና ለእርሷ በተመደበላት ቁምሣጥን ስታስቀምጥ ለቤቱ ያመጣችውን ባህል ነክ ጌጦች በየግድግዳው ለጣጠፈች ። በእጅ ቦርሳዋ ውስጥ የነበሩትን ወረቀቶች ስትበታትን ። ከውስጡ በቁም የተነሳችውን ፎቶግራፍ አውጥታ ወደ ደረቷ አስጠግታ አቅፋ ደጋግማ ሳመችው ።

በእርግጥ ፎቶግራፏ የእራሷ በመሆኑ አልነበረም አቅፋ የሳመችው ። ፎቶግራፏ የአባቷ መጥረቢያ ነበረበት ።

« አባዬ ይቅርታ ያወረስከኝን መጥረቢያ ከራሴ ጋር ይዤ ለመምጣት አልቻልኩም ። »

ሒሊና ሀሳቧን ወደ ሀገር ቤት መለሰች ። የአባቷን መጥረቢያ በአደራ የተወችው ለወ/ሮ በላይነሽ ነበር ። የመጥረቢያውን ምስጢር

በወጉ የሚያውቁ እርሳቸውና ያሬድ ብቻ ናቸው ። ወ/ሮ በላይነሽ የእርሷንና የአባቷን ፍቅር በህይወት የተመለከቱ ፣ የተካፈሉ ናቸው።

« እማማ በላይነሽ እናቴ ናቸው ። የእኔ ማለት የራሳቸው ነው » በማለት እራሷን ለማረጋጋት ሞከረች ። ከቦርሳዋ ውስጥ ፓስፖርትና የጋብቻ ወረቀትም ነበር ። በቅጡ ሰብስባ አልጋው አጠገብ ካለው መለስተኛ » ሳጥን አስገብታ ቆለፈች ። በአጋጣሚው የኢትዮጵያ ብር ፣ ሳንቲሞችና ቁርጥራጭ ወረቀቶችን ለየች ።

« ለሕሊና » የሚለውን ፖስታ ለመወርወር ከቃጣች በኋላ ማን እንደሰጣት ለማስታወስ ሞከረች ። ፖስታውን ይዛ ጥቂት አሰላሰለች እና ከፈተችው ። ከውስጡ ሦስት ባለ መቶ ዶላር ኖት ከአንድ ገፅ ደብዳቤ ጋር አወጣች ። በመገረም ስሜት ተውጣ ደብዳቤውን ገልጣ ማንበብ ጀመረች ።

*« ሠላም ሕሊና ! መቼም ይህን ደብዳቤ ስታነቢ ሳይገርምሽ አይቀርም ። መለያየት ካደረግንበት ጊዜ ጀምሮ ጤንነትሽን በእማማ በላይነሽ በኩል ለምቻለሁ ። ይህን ዕድል ማግኘትሽን ስሰማ ከልብ የመነጨ ደስታ ነው የተሰማኝ ። ስለአለፈው ሀይወታችን ሳላነሳ የዘነጋሁበት ቀን በጣም ጥቂት ፣ የተወሰኑ ናቸው ። የተለያየንበትን ቀን እየረገምኩ የምንገናኝበትን ቀን እያለምኩ እስከዛሬ ቆየሁ ። ከሀገር ለቀሽ ለመሄድ መነሳትሽን ስሰማ በእኔ በኩል አንቺን ለማግኘት ያለኝ ተስፋ ቢጨልምም የአንቺ የወደፊት ተስፋ ብሩህ በመሆኑ ደስታዬ ከመጠን ያለፈ ነው ። ሕሊና ! ለአንቺ ያለኝ ፍላጎት ከተገናኘንበት ቀን ጀምሮ እስካሁን እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም ። ባይገርምሽ ያቺ ቀን ለኔ የማትረሳ ናት ምክኒያቱም ሁሌ በደለኛነት ይሰማኛል በወቅቱ ራሴን*



*በጣም ጠልቼው ነበር ። ሕሊ . . የወደዱትን ማጣት የተመኙትን መነፈግ ምን ያህል የከፋ እንደሆነ የደረስበት ነው የሚያውቀው ። መወሰን አቅቶኝ በልንገራት አልንገራት ውስጤ ሲታመስ ፣ ሲንገላታ በስቀቀን የኖርኳቸው ቀናቶች ሲታሰቡኝ ሀዘኔ እጥፍ ነው። ወንድምኔቴን አምነሽ በተቀመጥሽበት ሠአት ባላሰብሽው እና ባልገመትሽው ሁኔታ ፍቅሬን መግለፄ በእርግጥም ጥፋተኛ ነኝ ። ርቀሽኝ ስትሄጂ ይቅርትሽን ሳላገኝ በመሄድሽ ሁሌም ልቤ ይደማል አዝናለሁ ። መቼም ሕሊዬ ይቅርታሽን እንደማትነፍጊኝ ተስፋ አለኝ ። አሁንም እንደ አንቺ ፍላጎት ወንድምነቴን ለመቀበል እራሴን በማስታመም ላይ ነኝ ። አልዋሽም ብዙም አልተራመድኩም ። እስቲ እንግዲህ ጊዜና ርቀት ይሽረው እንደሆን በዚህ ልሞክረው ።*

*« ሕሊና የዚህ ደብደቤ መሠረተ ሀሳብ ይቅርታ ለመጠየቅ ሲሆን ሌላው ደግሞ ለመኖር ማገገሚያ ይሆን ዘንድ ደብዳቤሽ እንዳይለየኝ ለማለት ነው ። ለማንኛውም ለእማማ በላይነሽና ለእማሆይ ብዙም አታስቢ ። እኛው ዘንድ ስለአሉ የተቻለውን ሁሉ ለማድረግ እሞክራለሁ ። አደራ ራስሽን ተንከባከቢ ። በተረፈ ይህችን አነስተኛ ስጦታ አሜሪካን ስትገቢ ለታክሲ ተጠቀሚበት ።*

*ያንቺው ናፋቂ ያሬድ ።*

ሕሊና የአነበበችውን አላመነችም ። ሀዘንና ደስታ የተቀላቀለበት ዕንባዋን አነባች። ደብዳቤውን በሁለት እጆቿ እንደያዘች ተከዘች ። በመጨረሻው ገፁዋ ላይ ያሬድ ለአፍታ ያህል ያደረገውን የርቀት ስንብት በዓይነ ሕሊናዋ ቃኘች ።

« አይ ጋሼ ያሬድ ! አይ ጋሼ ያሬድ ! » ስትል ራሷን ነቀነቀች ። ስለ ደግነቱ ፣ ጨዋነቱ ፣ ግልፅነቱና ለሷ ያለው ስሜት አለመቀዝቀዙ ፣ እራሱን በጥፋተኝነት ስሜት አቅርቦ ይቅርታ በመጠየቁ አዘነች ። በትካዜ ባህር ተውጣ ፣

« ለምን እንደዚህ ይሆናል ? » በማለት ራሷን ጠየቀች ። ለአንድ አፍታ ያሬድን በመስፍን ለውጣ ለማየት ሞከረች ።

« በስመአብ ! » አለች ። ሀሳቧ እውን መስሏት ዘገነናት ። ያሬድን በያሬድነቱ እንዳለ ይዞ መኖሩን መረጠች ። ለደብዳቤው መልስ ለመስጠት ሀሳቧን በማደራጀት ላይ እንዳለች መስፍን በሩን ከፍቶ ገባ ።

* * *

ሕሊና በትሩማን ኮሌጅ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርቷን መከታተል ከጀመረች ሁለት ወራት ሆናት ። እንግሊዘኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ የአሜሪካን ነዋሪዎች የሚሰጠው ይህ ፕሮግራም ለሕሊና አስቸጋሪ አልነበረም ። የሕሊናን የትምህርት ቅልጥፍና የተረዳው ሙሉጌታ ጥረቷን ለማበረታታት ምክሩን ለገሠ ። በየጊዜው ስለ ትምህርት ያላትን ጥያቄ በማብራራት ሳይሰለች ዕድገቷን መከታተል ቀጠለ ። ሙሉጌታ ለሕሊና ትምህርት ብቻ ሳይሆን ሥራንም በሚመለከት እንደመረጃ ማዕከል ሆኖ አገለገላት ።

« እኔ እዚህ ሀገር ስመጣ መምህር ነበርኩ ። ከቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ ዩኒቨርስቲ በጂኦግራፊ ተመርቄ ሀገር ቤት ሦስት ዓመት



ከሰራሁ በኋላ ወደ እዚህ መጣሁ ። ሕሊና አይዞሽ ! መምህር ለነበረ ሰው የዚህ ሀገር ትምህርት ይቀለዋል » በማለት አበረታታት ። ቀጥሎም « . . . እየሠራሽ መማር ትችያለሽ ። ለማንኛውም ሠርትፊኬትሽን ለአፕሬዛል ለምን ለፕሪንግፊልድ አትልኪም ? »

« ጋሼ ሙሉጌታ ይሆናል ብለህ ነው ? » ሕሊና ችሎታዋን በመጠራጠር ሙሉጌታን ጠየቀችው ።

« ከሆነ ይሆናል ። ካልሆነ ደግሞ ምን ታጨያለሽ ? ቢያንስ ቢያንስ ሁኔታውን ለማሟላት የሚያስፈልግሽን ይጠቁምሻል » በማለት የሕሊናን ፍላጎት ለማነሳሳት ሞከረ ።

« እሺ እስቲ እሞክራለሁ ።ግን አድራሻውን ከየት አገኛለሁ?»

« እኔ አመጣልሻለሁ ። ፎርሙን ሞልተሽ ለመስፍን ብትሰጪው ይልክልሻል » በማለት ሙሉጌታ ወደ መስፍን ተመለከተ።

« ኖ ፕሮብሌም እልክልሻለሁ » መስፍን ታላቅ ወንድሙ የተናገረውን ተቀበለ ።

ሕሊና የአሜሪካንን ኑሮ በመታገል ላይ እያለች ከትምህርቱ አልፎ ወደ ሥራ ዓለም መግባቱን በጣም ፈራች ።

« ሥራ ቢሠራስ ምን ዓይነት ሥራ ይገኛል ? እኔ የተማርኩት ማስተማር ፤የሰራሁት በመምህርነት ፤ በእኔ ትምህርትና የሥራ ልምድ መጠን ምን ልሆን እችላለሁ ? » ሕሊና በሀሳቧ ጥያቄዎችን ብታብሰለስልም መልሱን ማግኘት አልቻለችም ።

« ሁኔታውን እንደአመጣጡ መቀበል ነው እንጂ አማራጭ የለኝም » በማለት ነገሮችን በደፈናው ለመተው ሞከረች ።

« ጋሼ እዚህ ሀገር ማስተማር አይከብዳትም ብለህ ነው ? » በማለት መስፍን ወንድሙን ጠየቀ ።

« መክበድ ስትል ? » ሙሉጌታ ጥያቄውን እንዲያብራራ ጠበቀ ።

« ጋሼ ያኔ ስታወራ አንተ የነበርከበት ትምህርት ቤት ተማሪዎቹ አስቸጋሪዎች ናቸው ። እንኳን ለእኛ ሀገር መምህራን ቀርቶ ለሀገሬው መምህራኖችም በጣም ያስቸግራሉ ስትል ነበር » አለ መስፍን ጥያቄውን አብራርቶ ። « መስፍን ! እዚህ ሀገር የማይከብድ ሥራ ምን አለ ? ሁሉም ነገር ከባድና ጥረት የሚጠይቅ ነው ። ዲግሪው ይለያይ እንጂ ሕሊና ከመምህርነት ውጪ ሌላ የሥራ ልምድ የላትም ። ፖርኪንግ ወይም ቤቢ ሲት ካልሆነ ፣ እሱም ቢሆን የራሱ የሆነ ችግር አለው ። »

ሕሊና የሁለቱን ንግግር ለማቋረጥ አልሞከረችም ። መስፍን ያለበችውን ስለጠየቀ በጥሞና የሚናገሩትን ማዳመጥ መረጠች ። ሕሊና የሚያስፈልጋት ወጣ ብላ የሥራውን መስክ ማየትና መለማመድ ነው ። ቀላልና ከባድ ምርጫ የሚመጣው ሁሉንም ስታውቅ መሰለኝ ። » ለሁሉም የመጀመሪያው የት አለ የሚለው አባባል ወቅታዊ መሆኑን በማሰብ ከባዱንም ቀላሉንም ማየቱ ደግሞ ራስን ለማመዛዘንና አካባቢዋን ለመቀበል እንደሚረዳት አብሰሰለች ።

« ጋሼ ያልከው እውነት ነው ። ሌት አስ ሆፕ ፎር ዘ ቤተር»

መስፍን በታላቅ ወንድሙ አባባል ተስማማ ። ሕሊና የወንድማማቾቹ ንግግር እንዲቀጥል ብትፈልግም ሁለቱም ጉዳዩን በማንጠልጠል አቋርጠው ወደ ሌላ አርዕስት ተሸጋገሩ ። ሙሉጌታ ቤት ለለተዘጋጀው ግብዣና ስለተጠሩት እንግዶች ዝርዝር ማውራት ጀመረ ። በዝርዝሩ ውስጥ ሙሉጌታ ራሄልን መጋበዙን ገለፀ ። መስፍን የራሄልን መጋበዝ በደስታ አልተቀበለውም ።

« ጋሼ ደግሞ ዋት ጉድ ካን ሺ ቢ ፣ ለምን ትጠራታለህ » በማለት ስሜቱን ገለፀ ።

« አንተ በቤትህ የምትፈልገውን ጋብዝ ። እኔም በቤቴ የፈለኩትን መጋበዝ ምርጫዬ ነው » አለ ሙሉጌታ በከፊል ቁጣ ቃል።



« ማለቴ እኮ . . . »መስፍን ማለት የፈለገውን አልጨረሰም።

« መስፍን የምትለው ገብቶኛል ። ኢት ኢዝ ኦል ቢሃይንድ፣ ዩ ኒድ ቱ ፎርጌት ኤንደ ፎር ጊቭ » ሙሉጌታ ወደ ሕሊና ተመለከተ። ግራ የተጋባችው ሕሊና ስለምን እንደሚነጋገሩ አላወቀችም ።

« ይቅርታ ነገሩ አንቺን አይመለከትም ። አንቺ በማታውቂው ነገር ፊትሽ ላይ መጨቃጨቃችን አግባብ እንዳልሆነ አውቃለሁ ። »

የሙሉጌታ የይቅርታ ጥያቄ የሕሊናን በሀሳብ መዋጥ ባያስቀረውም ከሁለቱ ወንድማማቾች ክርክር ፣ ቀደም ሲል ካየችው የራሄል ሁኔታና መስፍን ስለ ራሄል ከነገራት ተነስታ ሀሳብ ውስጥ ገባች ።

« ምንድነው ምስጢሩ ፣ መስፍን ራሄል ላይ እንዲህ ዓይነት መጥፎ አመለካከት እንዲኖረው ያደረገው ? ለምን መስፍን ከራሄል ጋር እንዳልገጥም ይከላከላል ? ሙሉጌታስ ለምን ለራሄል አገዘ ? » ስትል አሰበች ። ለጥያቄዋ መልስ ለማግኘት ብትጥርም ብዙ መራመድ አልቻለችም ።

« ጋሼ ደግሞ እኔ ያላሰብኩትን ነው ዝም ብለህ እንዳመጣልህ የምትናገረው ። በል በቃህ እዚህ ላይ እንተወው ። »

መስፍን ንግግሩ እንዲቀጥል አልፈለገም ። ራሱን እያሻሸ ብስጭቱን በማርጎምጎም ገለፀ ።

« ማይ ሚስቴክ ! እሺ ትቼዋለሁ ። . . . « ሌላ ጨዋታ አምጡ ። »

ሙሉጌታ ያደፈረሰውን ሠላም መልሶ ለማምጣት ጥረት ቢያደርግም ሕሊና ሁለቱን ወንድማማቾች ትታ ወደ መኝታ ቤቷ አመራች።

* * *

*« በጣም ለምናፍቃችሁ ውድ እናቴ እማማ በላይነሽ ። ውድ አክስቴ እማሆይ አባይነሽ ። ከተለያየንበት ቀንና ሰዓት ጀምሮ ለጤንነታችሁ እንደምን ሠንብታችኋል ። እኔ እግዚአብሄር ይመስገን በጣሙን ደህና ነኝ ። ባለፈው ጊዜ ለከበቡሽ ስልክ ደውዬ መልዕክት እንድታደርስልኝ ነግሬአት ነበር ። በሠላም መድረሴንም ሳትነግራችሁ እንደማትቀር ተስፋ አለኝ። ውድ ዘመዶቼ ፣ ከእናንተ ተለይቶ ርቆ መኖር በጣም ይከፋል ። ሆኖም እዚህ ብዙ ኢትዮጵያውያን ስላሉ በእነርሱ እፅናናለሁ ።*

*እክስቴ እማሆይ እንዴት ናቸው ? ከህመማቸው እያገገሙ ነው ወይ ? ችግር ካለ ፃፉልኝ ። ስለ እኔ አታስቡ ። ሀገሩ በጣም ተስማምቶኛል ። ትምህርቴንም እየተማርኩ ነው ። ከሰሞኑ ደግሞ ሥራ ሳልጀምር አልቀርም ። መስፍን በሁሉም ነገር ያግዘኛል ፤ በጣም ጥሩ ሰው ነው ።*

*« እማማ በላይነሽ ። ጋሼ ያሬድ ወደ እዚህ ስመጣ አይሮፕላን ማረፊያ መጥቶ ነበር ። ደብዳቤ በሰው በኩል እዚያው ቦሌ እያለሁ ልኮልኛል ። መቼም በጣም ነው የተሰማኝ ። ለማንኛውም ይህን ደብዳቤ ስፅፍ ለእርሱም እፅፍለታለሁ ። በደብዳቤው ላይ እየመጣ እንደሚጠይቃችሁ ነግሮኛል ። እማማ በላይነሽ እደራ ጤንነታችሁን ጠብቁ ። እክስቴም ሀኪም ቤት እንዲሄዱ ምከሯቸው ። ለማንኛውም*



*የገንዘብ ችግር ካጋጠማችሁ ከበቡሽን ጠይቁ ። ደብዳቤ ለመላክ ከፈለጋችሁ ከበቡሽ ስትመጣ ፅፋችሁ ብትሰጧት ትልክልኛለች ። እማማ በላይነሽ በተረፈ በሚቀጥለው ደብዳቤ እስከምንገናኝ አምላክ በሠላም ጠብቆ ያቆየን ። »*

የመጀመሪያውን ደብዳቤ ፅፋ ከጨረሰች በኋላ የሚቀጥለውን ለመፃፍ ራሷን አዘጋጀች ።

« ሠላም ጋሼ ያሬድ ። እንደምን ሠንብተሃል ? . . . » ሒሊና መፃፏን አቁማ ዐረፍተ ነገሩን ለራሷ አነበበች ። አልወደደችውም ። ቀዳ ጣለችው ። ደብዳቤውን እንዴት መጀመር እንዳለባት አሰበች ። በጣም ቀዝቃዛ ደብዳቤ በጣምም ሞቅ ያለ ሠላምታ ለመፃፍ አልፈለገችም ። የመጀመሪያ ደብዳቤዋ እውነተኛ ስሜቷን የሚያንፀባርቅ መሆኑን ተጠራጠረች ። ስለ ራሷ ብዙ ማውራት አልወደደችም ። ሀሳቧን ሳትቋጭ ደብዳቤውን ለመጀመር ብዕሯን አስተካከለች ።

*« በጣም ለምናፍቅህ ወንድሜ ጋሼ ያሬድ ። ለጤናህ እንደምን ሠንብተሃል ? እኔ ይኸው አሜሪካ ገብቼ መኖር ጀምሬአለሁ ። ጋሼ ያሬድ የሰጠኸኝን ፖስታ የተመለከትኩት እዚህ ከደረስኩ በኋላ ነው ። እግዚአብሄር ይስጥልኝ ፣ አመሰግናለሁ ። ቀድሞ ያደረክልኝ ሁሉ አንሶ ይህን ተጨማሪ ውለታ ስትጨምርብኝ በጣም ነው የከበደኝ ። ቁም ነገር አዘል የይቅርታ ደብዳቤህ ደርሶኛል ። የፃፍክልኝን በጥሞና አንብቤዋለሁ ። ጋሽ ያሬድ ለአንተ ይቅርታን የሚነፍግ ልብ የለኝም ። እራስህን ልትወቅሰውና ልትኮንነው ፣ ጥፋተኝነት ሊሰማህ*

አይገባም ። የትላቱን ለትላንት ትተን ዛሬን እንኑራት በኔ በኩል ልቤ ላንተ ይቅርታን ለመስጠት የፀዳች ናት ። መቼም ቢሆን ላንተ ያለኝ ፍቅርና አክብሮት አይለወጥም ። ከምንም እና ከማንም በላይ ይምወድህና የማከብርህ እህትህ ነኝ ። ሀሳብህን ለማስታረቅ የምታደርገው ጥረት አበረታች ነው ። ጋሼ ያሬድ በዚህ ጥረትህ አጠገብህ ሆኜ ብረዳህ ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር ። ሆኖም የእግዚአብሔር ፈቃድ አልሆነም ። የመጣሁ ቀን በርቀት ሳይህ በጣም ነው ደስ ያለኝ ። ምንም ያህል ብንራራቅም የሰጠኸኝ ሠላምታ ከልብ የመነጨ መሆኑን አልጠራጠርም ። ጋሼ ያሬድ ! ሀገሩ በጣም ተስማምቶኛል ።

ባለቤቴም ጥሩ ሰው ነው ። በደግነቱ አንተን ያስታውሰኛል ። ትምህርቴንም ጀምሬአለሁ ። በተረፈ ስለ አደረክልኝ ስጦታ ደግሜ ደጋግሜ አመሰግናለሁ። በሚቀጥለው ደብዳቤ እስከምንገናኝ እግዝአብሔር በሠላም ይጠብቀን ። »

ያንተው እህት ሕሊና።

ሕሊና ለከበቡሽና ለአበራ ደብዳቤ ፃፈች ።

« ከበቡሽ ስለምታደርጊው ታላቅ ዕርዳታ በጣም አመሰግናለሁ ። እግዚአብሄር ውለታሽን ይከፈልሽ ። »

« አበራ መቼም እዚያ እያለሁ የምትለው ነገር ሁሉ አሁን እየገባኝ መጣ ። ያኔ አላመንኩህም ነበር። በአጠቃላይ አጠገቤ ሆነህ ስለሰጠኸኝ ምክርና



ድጋፍ ምን ጊዜም ባለውለታዬ ነህ ። እግዚአብሔር ይስጥልኝ። »

የፃፈችው በተለያየ ወረቀት ቢሆንም ፖስታው ግን አንድ ነበር። ለሁለቱም የወረወረችው ጥያቄም ነበር ።

« ከበቡሽ በአንቺና በአበራ መሀከል ምን አዲስ ነገር አለ ? ለውጥ ካለ አደራ ፃፊልኝ እንድዘጋጅበት ። »

ሕሊና ደብዳቤዋን ከጨረሰች በኋላ ለሚቀጥለው የትምህርት ቀን ራሷን ማዘጋጀት ጀመረች ።

ሕሊና በኢሊኖይዝ ስቴት ውስጥ ለማስተማር ስፕሪንግ ፊልድ የላከችው የፈቃድ ጥያቄ ቅፅ የያዘ ፖስታ መጣላት ። በችኮላ ፖስታውን ከፍታ ስትመለከተው ደብዳቤው ለማስተማር ፈቃድ እንደሚሰጣት ገልጾ ከዚህ ቀደም የሰራችባቸውን ትምህርት ቤቶች ዝርዝርና የትምህርት ውጤት ማስረጃዎቿን እንድትልክ የሚጠይቅ ነበር ። ሕሊና ደግማ ደጋግማ ካነበበች በኋላ ከመስፍን ጋር በመማከር ለሙሉጌታ ስልክ ደወሉለት ። ሙሉጌታ የተጠየቀችውን በፍጥነት እንድትልክ ነገራት ። የሕሊና ችግር ግን ካስተማረችባቸው ትምህርት ቤቶች ምንም ዓይነት ማስረጃ ይዛ አለማምጣቷ ነበር ። ይህንኑ በመጠቆም ሙሉጌታ እንዲረዳት ጠየቀችው ። ከሙሉጌታ ጋር በሚቀጥለው ቅዳሜ ለመገናኘት ተቀጣጥረው የስልኩን ግንኙነት ጨረሱ ።

ሕሊና የእንግሊዘኛ መደበኛ ትምህርቷን አጠናቅቃ ለከፍተኛ ትምህርት ብቁ የሚያደርጋትን ቅድመ ዝግጅት ጀመረች ። ስፕሪንግፊልድ የላከላት ፈቃድ የተወሰኑ የትምህርት ዓይነቶችን በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ እንድታጠናቅቅ ጠቅሶ በተተኪ አስተማሪነት ለመሥራት ብቁ መሆኗን አረጋገጠ ። ከፈቃዱ ጋር ፣ ለመሥራት ፈቃደኛ ከሆነች ወደ አካባቢዋ የትምህርት ዲስትሪክት

እንድትሄድ ጠቁሞ ለወደፊት በመደበኛ አስተማሪነት ለመቀጠል የተጠቀሱትን መረጃዎች ስታሟላ ለቢሮው እንድትፅፍ የሚል ነበር።

ሔሊና እውነተኛው የአሜሪካን ኑሮ ምን እንደሚመስል ለማወቅ እንድትችል ሁኔታዎች ጋበዟት ። ትምህርት ቤቱ በምትኖርበት አካባቢ ስለሆነ ምንም ዓይነት መጓጓዣ አላስፈለጋትም። በመንገድ ላይ የሚሸኮለኮሉት የሰዎች ዓይነት ግን ሠላም ሊሰጣት አልቻለም ። የሰዎቹ አቋማዊ ሁኔታ ፣ አለባበስ ፣ ሀይጅን ፣ አነጋገር፣ ከለመደችው አካባቢ ሰዎች ሁሉ የተለዩ በመሆናቸው በመንገዱ ባለፈች ቁጥር ሠውነቷ ይሳቀቃል ። በአካባቢው የአእምሮ በሽተኞች የሚኖሩበት ሁለት ትላልቅ ህንፃዎች አሉ ።

በእነኚህ ህንፃዎች የሚኖሩት እነዚህ በሽተኞች በመንገድ ላይ፣ በምግብ ቤቶችና በተለያዩ የንግድ መደብሮች ያለገደብ ስለሚዘዋወሩ ለሔሊና የቀን ተቀን የትምህርት ጉዞ ለአንዳንድ የባህል ትውውቅ መድረክ ሆኑ ። ፍርሃት ፣ ርህራሄ ፣ መሸነፍና ተስፋ መቁረጥ በሔሊና ሀሳብ የሚወጣና የሚወርድ የዕለት ተዕለት ክስተት ሆነ ።

ሔሊና የአእምሮ በሽተኛን በመሸሽ ወይንም መንገድ በመልቀቅ ማስተናገድ እንጂ በሽተኛ በመድሃኒት ድጋፍ እንደማንኛውም ጤነኛ ሰው ሊሆን ይችላል ብላ አትገምትም ። በሽተኞቹን ባየች ቁጥር መንገድ መልቀቅ ምርጫዋ ነበር ። ሆኖም የሰው እንቅስቃሴ ለዚህ የሚመች አልነበረም ። ሁኔታው ሰቀቀን ሆነባት ።

መስፍንና ሔሊና በሳሎናቸው ውስጥ ሆነው በመዝናናት ላይ እንዳሉ በአንዱ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ስለ ቤት አልባ ሰዎች የኑሮ ሁኔታ የሚያስረዳ ትዕይንት ተመለከቱ ።

« እንዴት ያሳዝናሉ ? » በማለት መስፍን ስለ አዩት አንድ ቤት አልባ ሽማግሌ ስሜቱን ገለፀ ።

« ከማሳዘን አልፎ ያስፈራል » አለች ። ሔሊና ፊቷን ከቴሌቪዥኑ በማዞር ።



« ምኑ ነው የሚያስፈራው ? ድህነቱ ? » በሔሊና አባባል በመገረም ጠየቃት ።

« ሁሉም ነገር ። አመለካከታቸው ፣ አለባበሳቸው የዚህ ዓይነት ሰዎች ምን እንደሚያደርጉ አይታወቅም ። እነኚህን በሩቁ ነው » አለች ለመስፍን ጥያቄ መልስ ለመስጠት በመሞከር ።

« ሔሊና እዚህ ሀገር ማንኛችንም ብንሆን ዛሬ ያለንን ነገ ልናጣ እንችላለን ። ሆምለስ መሆን እዚህ ሀገር ህገ ወጥ እንድትሆኚ አይገፋፋም እንዲያውም ለብዙ ሰዎች እንደ ኑሮ ምርጫቸው ሊሆን አብዛኛዎቹ ሃርምለስ ናቸው ። »

« እዚህ ሀገር የተትረፈረፈ ሥራ ሠርቶ መብላት እያለ አለመሥራትን መርጦ መቸገርን የሚመርጥ ሰው ጤነኛ ነው ብዬ አላምንም » አለች ሔሊና ።

« እዚህ ሀገር የእያንዳንዱ ሰው የኑሮ ምርጫ በህግ የተከበረ ነው ። የሌላውን ዜጋና ነዋሪ መብት እስካልነኩ ፣ ዘ ሪች ፣ ዘ ፑር፣ ዘ ሆመለስ ህይወታቸውን በየፈርጃቸው እንደፈለጉት መምራት ይችላሉ» በማለት መስፍን ሊያስረዳት ሞከረ ።

« ለዚህ ነው በየቦታው ተለቀው ሰውን መሄጃ ማሳለፊያ ያሳጡት ? » አለች ቆጣ ብላ ።

« ምን አስቆጣሽ ? በግል ጉዳት ያደረሰብሽ ሰው አለ ወይስ ስሜትሽን የጎዳ ? ከአነጋገርሽ በደል የተፈፀመብሽ ነው የምትመስይው » አለ በሔሊና አነጋገር ተደናግጦ ።

ሔሊና ስሜቷን ለመግለፅ ሳትቸኩል በዝምታ በመስኮት በኩል ወደ ውጪ ተመለከተች ። ወደ ትምህርት ቤት የምትሄድበት መንገድ በትይዩ ግልፅ ሆኖ የመንገዱ መብራቶች በርተዋል ።

« ና ተመልከት » በማለት መስፍን ያየችውን እንዲመለከት ጋበዘችው ። በርቀት አንድ ሰው መኪና መንገዱን መልሶ መላልሶ በፍጥነት እያቋረጠ ሠማይ ሠማዩን እያየና እየቃበዘ ለአፍታ ቆም

ራሱን በኃይል እየነቀነቀ መንገድ ማቋረጡን ቀጠለ ። መስፍን ፣ ሕሊና ይህን እንዲመለከት ለምን እንደጋበዘችው አልገባውም ።

« ኤንደ ዘን ዋት » ? በማለት እጁን አወራጨ ። ግራ እንደገባው ለመግለፅ ሞከረ ።

« ተመልከት ያልኩህ የለውዬውን ሁኔታ እንድታይ ነው ። አንተ ምናልባት በመኪና ስለምትመላለስ ፊት ለፊት ላያጋጥሙህ ይችላሉ ። ለእኔ ግን የቀን ተቀን ስቃይ ነው የሆነብኝ ። እነርሱን ባየሁ ቁጥር የምገባበት ይጠፋኛል ። . . . »

ሕሊና ሳግ እያቋረጣት ስሜቷን በንግግር መግለጽ አልቻለችም ። መስፍን ሕሊና የተናገረችውን አብሰለሰለ ። መንገዱ ላይ ያየው የአእምሮ በሽተኛ ሁኔታ እና የእርሷ ፍርሃት ከምን የመነጨ እንደሆነ አልገባውም ። ሁለቱን ሁኔታዎች ለማያያዝ ጥረት በማድረግ « አሁንም የምትይው አልገባኝም ። ዋት ሜክስ ዩ ሶ ሴንስቲብ እና ከአንቺ ትምህርት ቤት መሄድ ጋር ምን አያያዘው ? ሊገባኝ አልቻለም »

« እኔ በጣም ያስፈሩኛል ። ዘለው የሚያንቁኝ ነው የሚመስለኝ ። አንዳንዶቹ ዓይኖቻቸውን አፍጥጠውና አቅልተው አንዳች ነገር እንደገፋቸው በቀጥታ ወደ እኔ ይመጣሉ ። ታዲያ ያለኝ አማራጭ መሸሽ ብቻ ነው ። ጥቂቶቹ ተከታትለው ሲያባርሩኝ ወደ ሱቅ ተጠግቼ ነው የማሳልፋቸው ። »

ሕሊና ፍርሃቷን በማሳነስ ለመስፍን ገለፀችለት ። መስፍን በጥሞና አዳመጠ ። በአድራጎቷ መሳቅ ቢከጅለውም የነገሩን ክብደት በማጤንና ስሜቷን ላለመጉዳት በዝምታው ፀና ። ሆኖም የሕሊና አገላለፅ ፊት ለፊቱ ተደቅኖ ለነበረው ጥያቄ ግማሽ መልስ እንደሆነ ተረዳ ።

« ይህ ለሕሊና ኤ ፓርት ኦፍ ከልቸር ሾክ ነው » አለ ለራሱ ።



« ሕሊና ስሚኝ » መስፍን የሕሊናን ሁለት እጆች ይዞ ሶፋ ላይ እንድትቀመጥ አደረገ ። « እዚህ ሀገር የአእምሮ በሽተኞች በሚገባ ይታከማሉ ። ራሳቸውንና ህብረተሰቡን ጎጂ ሆነው ከተገኙ ወደ ሀኪም ቤት ይወስዳሉ ። ሀኪሙ ጎጂ አይደሉም ብሎ እስከአሳረጋገጠ ድረስ ሆስፒታሉ ውስጥ እየተጠበቁ ህክምና ይደረግላቸዋል ። አሁን በመንገድ ላይ የምታያቸው በሽተኞች ታክመው ሀኪም ሃርምለስ ናቸው ብሎ ሰርቲፋይ ያደረጋቸው ናቸው። »

ለሕሊና የመስፍን አገላለፅ አልተዋጠላትም ። « ከታከሙና ከዳኑ ታዲያ ለምን እንደማገኛቸውም ጤነኛ ሰው አይሆኑም ? »

« አይ ሚን ሃርምለስ ዳዝ ኖት ኢንክሉድ ዘስ ቢይንግ ኪዩርድ ። ሰውን አይተናኮሉም ማለት ነው እንጂ እንደ እኔና እንደ አንቺ ጤነኛ ሆነው የቀን ተቀን ህይወታቸውን አይመሩም ። »

« ከዚህ የበለጠ መተናኮል አይገባኝም ። »

ሕሊና በመስፍን አባባል በአጠቃላይ አለመስማማቷን ገለፀች። መስፍን የሕሊና ጭንቀት ከግል የመነጨ መሆኑን ቢረዳም ሕሊና በውጭ የምታየውን ተቀብላ ከራሷ ልምድ ጋር ለማዋሀድ የግል መለኪያ እንዳላት ገባው ። ይህ መለኪያ ከሰዎች የኑሮ ዘይቤ ፣ ከህብረተሰቡ የጋራ ብሎም ከግለሰቡ ባህላዊና ኤኮኖሚያዊ ህይወት የሚመነጭ ነው ። ሀሳቡን ጥሎ አጠገቡ የተቀመጠችውን ሕሊናን ተመለከተ ። ከአነጋገሯ ንፁህና የዋህ እንደበቷን አደነቀ ። ቢሆንም ተስፋ የቆረጠ መሳይ አመለካከቷ መስፍንን አሳዘነው ። አስተሳሰቧን ቀይሮ ከአካባቢው ጋር ለማመሳሰል የሚያበቃትን ፈጣን ለውጥ እንዲያጋጥማት ተመኘ ። ሆኖም የሰዎች ዓለም እንደግለሰቡ የህይወት ታሪክ የተወሰነ መሆኑን ሲረዳ ምኞቱ በቀላሉና በፍጥነት ሊፈጸም እንደማይችል ገመተ ።

« ዩ ሜይ ቢ ራይት ። መንገድ ላይ ያየሻቸው ሰዎች የአእምሮ በሽተኞች ብቻ አይደሉም ። እዚያ መንገድ ላይ በልዩ ልዩ የአእምሮ አደንዛዥ ዕፅ መርዞች የተበከሉ ሰዎችም ጭምር ይገኛሉ ። ለማንኛውም ከዚህ ትምህርት ቤቱ ድረስ ያለው መንገድ ቅርብ ቢሆንም እኔ አደርስሻለሁ ። ካልሆነም አውቶቡስ ትጠቀሚያለሽ » አለ መስፍን ሕሊናን ከአጋጠማት ችግር ሊረዳት በማሰብ ። ሆኖም ይህ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ እንደማይሆን መስፍን እርግጠኛ ነበር ።

የሕሊና የወደፊት የኑሮ ሁኔታ አሳሰበው ። እርሷ የመንግሥት ትምህርት ቤት ለማስተማር ከርዕሳነ መምህራን ጋር የቃለ መጠይቅ ቀጠሮ በማድረግ ላይ እንደሆነች ያውቃል ። አብዛኞቹ ተተኪ መምህራን የሚያስፈልጉዋቸው ትምህርት ቤቶች ከከተማው በስተደቡብ በኩል የሚገኙ ናቸው ። መስፍን አብዛኛዎቹ ከደቡብ ክፍል የሚመጡ ተማሪዎች ቁጡና ለወንጀል የተጋለጡ መሆናቸውን ከሚሰማውና ከሚያየው መገንዘብ ችሏል ። ሕሊና ወደ እዚህ አካባቢ ስትመላለስ ስለሚያጋጥሟት ሁኔታዎች አሳሰበው ። « የሠፈራቸው ቀለል ያለው ትዕይንት ያስበረገጋት ከበድ ከሚሉት የህይወት ልምዶች ጋር እንዴት መላመድ እንደምትችል መስፍን ግራ ገባው ። ሺ ኒድስ ቱ ጎ ፎር ፕሮፌሽናል ከውንስሊንግ ። » ሀሳቡን ለሕሊና ለማካፈል ወሰነ ።

« ሕሊና ዜር አር ፕሮፌሽናልስ ሁ ካን ሄልፕ ዩ ኢን ዚስ ሪጋርድ » በአባባሉ ሕሊናን እንዳያስቀይም በመጠንቀቅ ጉዳዩን በማጠቃለል ተናገረ ።

« እርዳታ ስትል ምን ዓይነት ? »

« ማለቴ አጀስትመንት ፕሮብሌም ፤ ሀገሩን ለመልመድ ችግር ላለባቸው ሰዎች ፕሮፌሽናል ምክር የሚሰጡ ማለቴ ነው ። »



« አሁንም አልገባኝም ። እኔ ነኝ ችግር ያለብኝ ወይስ መንገድ ላይ የተኮለኮሉት . . . ? » ለማለት የፈለገችውን አልጨረሰችም ከራሷ ጋር ማውራት ጀመረች ።

« የተናገርኩት አንቺን ለማስቀየም አይደለም ። ድንገት ሀገሩን ለመልመድ ችግር ካጋጠመሽ አዋቂዎችን ማማከር አይከፋም በማለት ነው ። አያስፈልገኝም ካልሽ ምርጫው የአንቺ ነው ። »

መስፍን ስለ ጉዳዩ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሕሊና ጋር በመወያየቱ ደስ ስለአለው የእርሷ ቅሬታ አላሳሰበውም ።

« ለምን እቀየማለሁ በእርግጥ አንተ የመሰለህን ብትናገርም ምክርህ ግን አልገባኝም » አለች ። ይበልጥ ለማወቅ ጉጉት እያደረባት።

« የምልሽ ምክር በቀጥታ አይደለም ። ካውንስሊንግ ማለቴ ነው ። እንደሚመስለኝ ዚስ ማይት ሄልፕ ዩ ቱ አጀስት ቱ ዩር ሶሻል ኢንቫይሮመንት ። የዚህ ሀገር ሰዎች ከአቅማቸው በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥማቸው ካውንስሊንግ ። ይስራ አይስራ እኔ አላውቅም ። ሆኖም ላመነበት እንደሚሰራ አልጠራጠርም ። »

* * *

« ታዲያስ ሥራ እንዴት ነው ? » ስትል ሕሊና ራሄልን ከሠላምታ ልውውጥ በኋላ ጠየቀቻት ።

« ኢት ኢዝ ግሬት ! አንቺስ ትምህርቱ እንዴት እያደረገሽ ነው ? መቼም የዚህ ሀገር ትምህርት ማለቂያ የለውም » ራሄል የምትሄድበትን አቅጣጫ እንዳትስት መሪዋን እያስተካከለች ወደ ሕሊና ተመለከተች ።

« ኦ ማይ ጋድ ! ፊትሽን ምን አደረግሽበት ? » የመኪናዋን የፀሀይ መከላከያ ገለጥ አድርጋ ወደመስተዋቱ አመለከተቻት ።

« እይው እስቲ »

« ምን ሆኖለሁ ? » ሕሊና ሁልጊዜ ከምታየው የተለየ ነገር አላየችም ። ወደ ራሄል ተመለከተች ።

« ምን አየሽ ? እኔ ምንም ማየት አልቻልኩም ። »

« ካን ዩ ሲ ዚስ ኤንድ ዚስ ? » ራሄል በጣቷ ወደ ራሷ ፊት እየጠቆመች በምሳሌ ለሕሊና ለማስረዳት ሞከረች ።

« የዚህ ሀገር ዌዘር እንኳን ላልለመደው ለለመደውም በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ መጠንቀቅ አለብሽ ። አይ ወንዶች ፣ መስፍን እንኳን ለሰው ለራሱም ግድ የለውም ። በይ አሁን ሄደን ለፊትሽና ለፀጉርሽ ተስማሚ ቅባት እንገዛለን ። »

« ከሀገር ቤት ያመጣሁት ብዙ የቅባት አይነቶች አሉኝ ። ምን ይሰራልኛል ? »

« እሱን ተይውና አሁን እንሂድ » በማለት ራሄል የተናገረችውን ለማደብዘዝ ሞከረች ። ቀጥላም « ኢት ኢዝ ኦን አወር ዌይ ፣ ደቂቃ አይፈጅም ። ትወጂዋለሽ ፤ ግድ የለሽም » አለቻትና ወደ ቁንጅና ዕቃዎች መደብር ጉዟቸውን ቀጠሉ ።

ሕሊና ለመጀመሪያ ጊዜ ሠፊና የተደራጀ የቁንጅና ዕቃዎች መደብር ውስጥ ገባች ። በውስጡ የተደረደሩት ዕቃዎች ሁሉ ማረኳት ። በሽታውና በቀለሙ ፣ በአንድነትና በብዛት በዋጋ ተለይቶ ማንኛውም ሸማች በግልፅ ሊደርስበትና ሊመለከተው በሚችልበት ቦታ ተቀምጧል ። ለቅምሻ ያህል የተከፈቱ በየዓይነቱ ማዕዛው ጥሩ የሆነ ቅባት ፣ ሽቶ ፣ የጥፍር ቀለምና ሌሎች ዕቃዎችም በየቦታው ተደርድረው የሰውን ሁሉ እይታ በመሻማት ያልገዛን እንዲገዛ ፣ የገዛን እንዲጨምር ይገፋፋሉ ። ምን ያህል መግዛት እንደምትችል ለማወቅ በቦርሳዋ የያዘችውን የገንዘብ ልክ አሰላሰለች ።

« ዕቃው በጣም ውድ ነው ። » ሕሊና ከራሄል ጋር የዕቃ ምርጫ በማድረግ የተሰማትን ተናገረች ።



« መኒ ካምስ ኤንድ ጎስ ። ተመልሶ የማይመጣው ይህ ያለሽ መልክና ዕድሜ ነው ስለሆነ በቅጡ ካልተንከባከብሽው እስከዘላለሙ ታጭዋለሽ ። »

ራሄል የሕሊናን ፍላጎት ሳትጠይቅ የሚመስላትን ሳሙናና ቅባት በያዘችው ቅርጫት ውስጥ ማስቀመጥ ጀመረች ።

« ይህ ሞይስቸራይዘር ነው ። ቆዳሽ እንዳይደርቅና ለስላሳ እንደሆነ እንዲቆይ ይረዳሻል ። በቀን ሁለት ጊዜ ጠዋትና ማታ በዚህ ሳሙና ታጥበሽ ብትቀቢው የቆዳሽ ቀለም እየለመለመ ይመጣል ። »

« እኔ የምልሽ ዕቃዎቹ በጣም ቆንጆዎች ቢሆኑም እኔ ዛሬ ገንዘብ አልያዝኩም ። ለምን ሌላ ቀን ተመልሰን አንመጣም ? » ሕሊና በትህትና መልክ ለማስረዳት ሞከረች ።

« ኦ ጂ ! ስንት ጊዜ ላስረዳሽ ? ገንዘብ ! ገንዘብ ! ዱ ኖት ዎሪ ! እሱን ለእኔ ተይው ። እኔና አንቺ እኮ ዊ ሃቭ ሶ መኒ ቲንግስ ኢን ኮመን ዊ ኒድ ቱ ሄልፕ ኢች አዘር ። » ራሄል በፈገግታ ሕሊናን ተመለከተች ።

ሕሊና የራሄል አባባል ቁምነገር አዘል እንደሆነ ገባት ። ከእርሷ ጋር መስፍን በሌለበት በድብቅ የወጣችበት ምክንያት ሱቅ ለማየት ብቻ አልነበረም ። በበለጠ ስለ አሜሪካን ኑሮ ምስጢር ለማወቅና ከዚያም ካለፈ በራሄልና በመስፍን መሀከል ስላለው ውስጣዊ ቅራኔ ለማወቅ ፍላጎትም ነበራት ።

« ለምን እንደዚያ አልሽ ? ኢትዮጵያውያን ስለሆንን ነው ? » ራሄልን አትኩራ በማየት መልሱን ከፊቷ ለማንበብ ሞከረች ።

« እሱም አንዱ ምክኒያት ነው ። ዋናው ነገር ግን እኔና አንቺ በሥጋና በደም እንደተዋሀድን እህትማማቾች ነን ። ሕሊና ! ሁሉንም ነገር አውቃለሁ ። ሞኝ አልምሰልሽ ። አውጥቼ ባልናገረውም ከመጣሽ ጀምሮ እስከ ዛሬ ብዙ ጊዜ አብረን እንዳንሆን

መስፍን እንደሚከለክልሽ አውቃለሁ ። ያን ሲያደርግ ያለ ምክንያት አይደለም፤ ምክንያት አለው ። ጊዜው ሲደርስ እንነጋገራለን ። »

ራሄል ወደ ገንዘብ መክፈያው ተጠጋች ። ቦርሳዋን ከፍታ የብድር ካርድ አውጥታ ለካሸሯ ሰጠቻት ። ሕሊና ለዕቃው የተከፈለውን ገንዘብ ለማወቅ ጥረት አደረገች ። ለማወቅ ግን አልቻለችም ።

« ይህንን ማን ነገረሽ ? ምክንያቱም መስፍን ስለአንቺ ምንም አላለኝም ። ማን እንደነገረሽ ብትነግሪኝ ጥሩ ነበር ። » አለችና ራሄልን እያየች ስሜቷን ከገፅታዋ ለማንበብ ሞከረች ። የራሄል ገፅታ ግን ትርጉም የለሽ ባዶ ፈገግታ የተላበሰ ነበር ።

« ሕሊና ስቶፕ ኢት ! ለምን እንደዚህ ታይኛለሽ ? እንደህ በጥያቄ መልክ ሲመለከቱኝ በጣም ነው ዲስኮምፎርት የሚሰማኝ » አለች ራሄል ፈገግታዋን ወደ ሳቅ ለውጣ ። « ለነገሩ ስለ መስፍን ማንም ሰው ባይነግረኝም ክበቲ በላይ አውቀዋለሁ ። » በማሾፍ ወደ ሕሊና ተመለከተች ።

« ምን ማለትሽ ነው ? የምፈለገውን ስትይ አልገባኝም ። » ሕሊና ኮስተር ብላ ጠየቀች ።

« ሕሊና ! የነገረኝ መስፍን ይሆናል ። እኔው ለማስረዳት ልሞክር ። እኔና መስፍን ሉንግ ታይም ፍሬንድስ ነበርን ። የእኔና የመስፍን ቤተሰቦች ለረጅም ዓመት አብረው ኖረዋል ። እኔ ወደ እዚህ ሀገር ስመጣ ስፖንሰር ያደረገኝ ጋሼ ሙሉጌታ ነው ። ታዲያ ምን ብዬ ልንገርሽ እኔና መስፍን የልጅ አይሉት አዋቂ - ቦይ ፍሬንድ፣ ገርል ፍሬንድ ስንጫወት ለጥቂት ጊዜ አብረን ቆየን ። ሕሊና አደራሽን ዶንት ቴክ ኢት ሶ ሀርድ ኦን ዩር ሰልፍ ዚስ ኢዝ ኢን አወር ፓስት ። አሁን እኔና መስፍን ጥሩ ወንድምና እህት ነን ። ሁለታችንም ብንሆን በወቅቱ ብዙ አልበሰልንም ነበር ። ያኔ በየቀኑ መጣላት ፣ መፋለስ ነበር ። ጋሼ ሙሉጌታ ታዲያ « የእናንተ አብሮ



መሆን አይታየኝም ። በዚህ ዓይነት ኑሮ አንድ ቀን አንዱ ሌላውን ገድሎ ቤተሰቦቻችንን ደም ታቃባላችሁ ይቅርባችሁ » ብሎ ይመክረን ነበር ። ሁለታችንም በጉዳዩ አሰበንበት ኢት ኢዝ ፎር ዘ ቤተር ብለን ተለያየን ። « ቢሳይድስ እኔና መስፍን አር ኖት ሜድ ፊር ኢች አዘር:: » አለችና አንገቷን ቀስራ ፣ አፏን ከፍታ ፣ ፊቷን አርዝማ ፣ ዓይኖቿን በልጥጣ ወደምታያት ሕሊና ተመለከተች ።

ለሕሊና ይህ መርዶ አዲስ ክስተት ሆነባት ። የራሄል ግልፅ አቀራረብ ቢለማትም አባባሏን በእውነትነት አምና ለመቀበል አዳገታት:: ሕሊና ባላት ልምድ ሴቶች ከወንዶች ጋር ስላላቸው ግንኙነት እምብዛም አይወያዩም ። ከተወያዩም በጓደኝነት ፍጹማዊ ቅርበት ካላቸው ሰዎች ጋር ነው ።

« ባለቤትሽ የእኔ ወንድ ጓደኛ ነበር » ብላ በድፍረት የምታወራ ሴት አጋጥሟት ስለማታውቅ የራሄል አባባል ያልጠበቀችው ዱብ ዕዳ ነበር የሆነባት ሀሳቡን መቀበል አለመቀበሉ ቢያዳግታትም ውይይቱን መቀጠል እንዳለባት ገመተች ። ውስጣዊ ስሜቷን ለመደበቅ በመሞከር « ለመሆኑ አብራችሁ ብዙ ቆያችሁ ? ካነጋገርሽ ለመረዳት እንደቻልኩት ብዙም የተስለቻቻችሁ አይመስልም» አለች ።

« ኦ ! ያ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የዚህ ዓይነት ኮሜንት ሰው ሲሰጥ ሰማሁ ። መሰልቸት ፣ መጣላት ፣ የሚለው እንኳ አልነካካንም ። ዊ ጀስት ሴተልድ አወር ዲፈረንስስ ኢን ኤ ሲቪላይዝድ ዌይ ፤ ግን ሕሊና የእውነቱን ልንገርሽ ፣ ዌን አይ ሲ ሂም ፣ አይ ሄት ሂም ! ሄት ሂም ! ሄት ሂም ! » ራሄል መራር በሆነ ቃል ተናገረች ። የመኪናውን መሪ መታ መታ አደረገች ። ድርጊቷ አነጋገሯን አጋነነው ።

« ለምን ትጠይዋለሽ ? ያለፈ ነገር ያለፈ ነው ብለሽ በእርግጥ የምታምኚ ከሆነ ለምን እርግፍ አድርገሽ አትተይውም » አለቻት ።

ይኸው ኑሮአቸው ተስተካክሎ ይኖራሉ ። ከጋሼ ሙሉጌታ ጋር ሁለት ዓመት ቤታቸው ተቀምጫለሁ ። ለልጆቻቸውም ቤቢ ሲተር ሆኜ አንዳንድ ቀን እረዳቸዋለሁ ። አሁን አሁን ሳስበው ከጋሼ ሙሉጌታ ጋር አብሬ ባልኖር ኑሮ መስፍን አያታልለኝም ነበር ። እኔ ወንድማማቾች ናቸው ፣ ፀባያቸው ያው ተቀራራቢ ይሆናል ብዬ ነበር የተዘናጋሁት ።

« የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው የሚሉት የሀገራችን አባባል እውነት ነው ። . . . ሕሊና ብዙ ጨቀጨኩሽ ። ያሰለቸሁሽ መሰለኝ . . . ኡፎይ » በማለት ራሄል በረጅሙ ተነፈሰች ። ሕሊና የራሄል ወሬ በዚህ እንዲያቋርጥ አልፈለገችም ። ያላወቀችውና ያልዳሰሰችው አዲስ ክስተት በመከፈቱ ለማወቅ ያላት ፍላጎት ጨመረ ።

« ምን ችግር አለ ? እንዲያውም አልፎ አልፎ እንደዚህ ማውራት ጥሩ ነው ። የበለጠ እንድንተዋወቅና እንድንማማር ይረዳናል ። »

« መቼም እርግጠኛ ነኝ ያወራነው በሙሉ በአንቺና በእኔ እንደሚቀር . . . ምስጢር አድርገሽ ያዥው » አለች ራሄል ።

« እርሱን ለእኔ ተይው ። ምን ብዬስ አወራለሁ ? ጉዳዩ የራሴም ጭምር ስለሆነ ሙያ በልብ ነው ። » ሕሊና የመጨረሻውን አባባል ለራሷ በመናገር ጨረሰች ።

* * *

መጠኑ ትንንሽ ሆኖ የተነደፈ ጥጥ መስሎ በስሱ የሚወርደው በረዶ መሬቱ ላይ ተጋግሮ አካባቢውን ነጭ አንሶላ የለበሰ አስመስሎታል ። የቆሙት ዛፎች ቅጠላቸው ረግፎ ፣ ቅርንጫፎቹ ደርቀው ያለምንም እንቅስቃሴ ቆመዋል ። ከመኪና በስተቀር በእግሩ ዝር የሚል ሰውም ሆነ እንስሳ የለም ። ሕሊና መስፍን የገዛላትን ካፖርት ለብሳ ፣ ከዓይኖቿ አካባቢ በስተቀር ፊቷን በተቻላት ሸፍና



ከምትኖርበት ህንፃ ወጣች ። አንድ ዘግናኝ ነገር ፊቷን እንደነካው ሁሉ በእጇ ስትዳስስ ቅዝቃዜው ከልክ አልፎ ዓይኖቿን አቃጠለው ። ፅንባ አኅርቶ የሩቁን ማየት አዳገታት። ባለችበት ቆማ « አይ!ሽ ሕሊና ! የፈረንጅ ሀገር ክረምት ማለት ይህ ነው » ብላ ራሷን አፅናናች ። እንዳትንሸራተት የምትረግጠውን መሬት በጥንቃቄ እየመረጠች መራመዱን ቀጠለች ። ርቃ በሄደች ቁጥር እየቀለላት ሄደ ። ሆኖም ቅዝቃዜው ጫማዋን አልፎ እግሮቿን ሲያደነዝዘው በአካባቢዋ ከሚገኝ ሱቅ ውስጥ ገብታ የእግሮቿ ሙቀት እስኪመለስላት ጠበቀች ። ሆኖም ወደ አሰበችው ቦታ ለመድረስ ባለመቻሏ ቤቷ ተመልሳ ልብሷን አወላልቃ የቤት ውስጥ ሥራዋን ቀጠለች ።

« ምን እግዚአብሄር የተጣላው ሀገር ነው ? ብርዱ ማቆሚያ የለው ፤ ሙቀቱ ሲመጣ ደግሞ ከመጠን ያለፈ ፤ በእንደዚህ ዓይነት አየር ሰውስ እንዴት መኖር ቻለ ? ወይ ህገሬ ! ያለንበት አይታየንም። . . . እንዴ ወጣ ብሎ ለመምጣት ሞቼ ነበር ። » በሠላም ቤት በመድረሷ ደስ አላት ። የቤቱን ሙቀት አመሰገነች ።

« የበረቱት ችግሩን ተቋቁመው ሲወጡ የተሸነፉት ደግሞ ተረተው የባሉቻቸው አገልጋይ ሆነው ቀሩ ። » ራሄል ያለችው ትዝ አላት። ወደ መኝታ ቤት ገብታ መሳቢያውን ከፍታ በጥንቃቄ የተቀመጠውን ፎቶግራፍ አወጣች ። በትከሻዋ እንግባ የተነሳችውን የአባቷን መጥረቢያ አየች ።

« አባዬ ብርታቱን ስጠኝ ። አሁን ደግሞ ይህን የመሰለ የተለየ ፈተና አጋጥሞኛል ። » በማለት ፎቶግራፉን ወደ ደረቷ አስጠግታ አቀፈችው ። ሁሉን ነገር በነበር ትታ ቁም ሳጥኑን ዘግታ ልብሷን መለባበስ ጀመረች ።

ሁለት ወፍራም ካልሲዎች ፣ የብርድ ኮፍያ ፣ ሁለት ሹራብ፣ ጃኬትና ካፖርት በላዩ ላይ ደርባ ቀስ በቀስ በበረዶ ውስጥ

እየተራመደች ወደ ትምህርት ቤቷ አቀናች ። ሒሊና በመሄድ ላይ እንዳለች በረዶው አንሸራቶ ጣላት ።

« ሒሊና በመሄድ ላይ እንዳለች በረዶው አንሸራቶ ጣላት ። «አር ዩ ኦኬ ? » ዞር ብላ አጠገቧ የነበረውን ሰው ተመለከተች ። ለዕርዳታ ለጋሹ ሁለተኛ መጠየቅ አላስፈለገውም ። የሒሊና ሁኔታ ብቻውን ገላጭ በመሆኑ « ኢት ኢዝ ኦኬ » በማለት እጇን ዘረጋችለት ። እያቃለተች በድጋፍ ከወደቀችበት ተነስታ ራሷን እያበረታታች ወደ ትምህርት ቤት እያነከሰች ተራመደች ።

« የግፍ ግፍ በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ። ብርዱ ሳያንሰኝ መውደቄ ደግሞ . . . የተረገመ ሀገር . . . » እያለች ፤ ስለሀገሯ እያሰበች በሀሳብ ጭልጥ አለች ። ከሀሳቧ የተመለሰችው የትምህርት ቤቱን በር ከፍታ እንደገባች ነበር ። የትምህርት ቤቱ ሙቀት ፣ ብርሃንና ድሎት ሥቃዩን ከመቅፅበት እንድትረሳው አደረጋት ።

በክፍሉ ውስጥ የሒሊና መምህር ስለ « ኮምፒዩተር ፖቴንሻል ኢን ኮምኒኬሽን » በሚለው አርዕስት ላይ መግለጫ በመስጠት ላይ ነበር ። ሒሊና የመምህሩን አባባል በቀጥታ ከራሷና ከሀገሯ ጋር በማመሳሰል ምሳሌዎችን ለመጠቀም ሞከረች ።

« አዎ እውነቱን ነው ፣ ኮምፒዩተር የዓለም ሥልጣኔ የደረሰበት የግኝቶች ቁንጮ ነው ። በሠለጠነው ዓለም ኮምፒዩተር ሰዎች የቀን ተቀን ሥራቸውን ለመስራት ስለሚጠቀሙበት ኮምፒዩተር ብዙ ባለሙያዎችን በመተካት ፣ በጥራት እና በብቃት አጥጋቢ ውጤት ይሰጣል ። መዝገብ ቤት ፣ ሂሳብ ክፍል፣ ዲዛይን፣ የመሳሰሉትን ሠፊ ቦታና ብዙ የሰው ኃይል የሚያስፈልገውን ሞያ በአንድ ትንሽ ክፍል ውስጥ ለማከናወን ተችሏል ። »

ሒሊና የመምህሩን ምሳሌያዊ አገላለጽ በተመስጦ ብታዳምጥም ከመጣችበትና ከነበረችበት ልምድ ጋር በማዛመድ በሀሳብ ማዕበል ውስጥ መዋዠቁን ማቆም አልቻለችም ።



« ትምህርት እንደድሎት በሚቆጠርበት . . . በሀገራችን ሥራን ከኮምፒዩተር ጋር እንዴት ለማዛመድ ይቻላል ? » ሒሊና ጥያቄውን ለሀሳቧ እንደ መንደርደሪያ በማድረግ ክፍለ ጊዜውን ጨርሳ ወደ ዕረፍት ወጣች ።

« ሃይ ሄሌ ! ኢሌን ኦ ! ኖ ፣ አይ ኦልዌይስ አይ ሃብ ኤ ዲፊካልት ታይም ኮሊንግ ዩር ኔም ራይት ። ኢዝ ኢት ኦኬ ቱ ኮል ዩ ሄሌ ? »

በእረፍት ጊዜ መቆሚያ ቦታ ሰብሰብ ብለው ከቆሙት የክፍል ተማሪዎች አንዷ ሒሊናን እንድትቀላቀል « ካም ኦን ኤሌን ! ጆይን አስ » ስትል ጋበዘቻት ።

« ዌር አር ዩ ፍሮም ? »

« ኢትዮጵያ ! »

« ዩ ኢትዮጵያንስ አር ሶ ቢውቲፉል ። አይ ዊሽ አይ አም ዋን ኦፍ ዩ ። ዩር አይስ ፣ዩር ሄር ኤንድ ከለር ! ኢት ኪልስ ሚ ።» በሀፍረት አንገቷን የደፋችውን የሒሊናን ፀጉር በማተኮር ጠጋ ብላ ተመለከተች ።

« ዊ ነቨር ሃድ ኤ ቻንስ ቱ ቶክ አይ ዶንት ኖው ማች አባውት ኢትዮጵያ ። ዘ ኦንሊ ቲንግ ዛት አይ ካን ሪኮል ኢዝ ዘ ሆረብል ፋሚን » አለች ጋባዥ አፍሪካ አሜሪካዊት ።

« ሃው ኢዝ ዘ ከንትሪ ናው ? » አብረው ከነበሩት አንደኛው ሒሊናን ጠየቀ ።

« ኢት ኢዝ ኦኬ » ሒሊና ጥያቄውን በማጠቃለል መለሰች ። ሒሊና በሁለቱ ሰዎች የተሰነዘረው አስተያየትና ጥያቄ ስለ ጥሩውና ስለ መጥፎው የሀገሯ ሁኔታ በከፊል እንደሚወክል አሰላሰለች ።

« ቁንጅና የሰዎችን ማንነት አይወክልም ። ቆንጆ እንደ ተመልካቹ ነው ። የቆዳ ቅላትና የፀጉር መለስለስ ተፈጥሮአዊ ክስተት ነው ። ቆንጆ ፣ መጥፎ ከሰዎች አመለካከት የመነጨ ሀሳባዊ ፅንስ

እንጂ የተፈጥሮ ውጤት አይደለም » በማለት የሰማችውን በሀሳቧ ገመገመች ::

ሕሊና በወትር የምትበላጭበት የተለያዩ ሰዎች ለሀገሯ እንደመለያ ምልክት የሚጠቀሙበት ረሃብ እና ችግር ነው :: ስለሀገሯ ሲጠይቋት ባህሉን ፣ ቋንቋውን ፣ የአኗኗር ዘይቤውን ሁሉንም ነገር በጥሞና ታስረዳቸዋለች :: ስለሀገሯ ያላቸውን ግንዛቤ በተቃራኒው ስታስቀምጥላቸው በጣም ይገረማሉ :: ቢሆንም ከስለሀገሯ ድህነት ፣ ጉስቁልና ፣ ኋላቀርነት ጠቆም አርገው የማያልፉበት ቀን ጥቂት ነው:: ሕሊና አብረዋት ካሉት ሰዎች ተለይታ በሀሳብ ርቃ ሄዳለች :: « እውነት ነው ፣ ሀገራችን በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ችግር መንስዔ የደረሰባትን ችግር ለመወጣት አልቻለችም :: ችግሩን ለማስወገድ አቅሙ ጠፋ :: አቅሙ ጠፋ ? ወይስ የተበታተነውን አሰባስቦ ለውጤታማነት ለማብቃት ያለመቻል ? መበታተን ፣ መቃረን ፣ አንዱ የሰራውንና የገነባውን ሌላው ማፍረስ ፣ ከመጥፎ ባህላችን አንዱ ቅሪት ይህ ነው :: »

ሕሊና አብረዋት ከቆሙት የአሜሪካን ተወላጆች ጋር ብዙ ማውራት አልቻለችም :: ሀሳቧን አሰባስባ በአዳማጭነት ተወስና ቀረች::



* * *

« ሃኒ ዩ አር ስፔንዲንግ ቱ ማች ታይም ኦን ዚስ ቲንግ :: ቤቱ ባዶ ነው የሚበላ ነገር የለም » አላት መስፍን ::

መስፍን ቅዳሜ ዕለት አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው በስተቀር ከመኝታው የሚነሳው አርፍዶ ነው :: ሕሊና ሌላ ክፍለ ጊዜ ስለጨመረች ቅዳሜ በጠዋት ወጥታ የምትመለሰው ወደ እኩለ ቀን ነው :: ይህ ለመስፍን ምቾቱን በጥቂቱ አዛባበት :: ቀደም ሲል የቅዳሜውን ክፍለ ጊዜ ወደ ሌላ ቀን እንድትቀይር ለማስገደድ ሞክሮ ነበር :: ሕሊና አጥብቃ በመከራከሯ ሊያሸንፋት አልቻለም :: ሆኖም ደስተኛ አልነበረም ::

« ምን ማለትህ ነው ? አሁን የምወስደው ሰብጀክት እንደከበደኝ ነግሬሃለሁ :: ማክሰኞ ፈተና ስለአለኝ መውደቅ አልፈልግም » አለች መፅሀፏን እየሰበሰበች ::

« ኖ ! ኖ ! አይ ዶንት ሚን ቱ ኦፌንድ ዩ :: ማጥናት ከፈለግሽ ማጥናት ትችያለሽ ሃኒ ! ሌትሊ አብረን የምናሳልፈው ጊዜ እየመነመነ በመምጣቱ ነው መሰለኝ አይ ፊል ጀለስ :: ትምህርቱ አንቺን ከእኔ ቀምቶ የወሰደ ነው የመሰለኝ ::

« ሉክ ! ሉክ ! » መስፍን ሁለቱን እጆቹን ዘርግቶ በየአቅጣጫው ወደተደረደረው መፅሐፍ ፣ በየቦታው ወደ ተቀመጠው ወረቀትና ደብተር እያመለከታት « ቤቱ ወደ ት/ቤት ተለውጧል ነጋ ጠባ ሩጫ ከሆነ ህይወትን መኖር የምንጀምረው መቼ ነው ? »

« ትምህርት እኮ የሰዎች ህይወት አንዱ ክፍል ነው :: ኑሮ እራሱ ያለ ትምህርት የሚሆን ስለአልሆነ ለእኔ መቼም አዲስ ነገሮችን ማወቅ የአእምሮ እርካታን ስለሚሰጠኝ በምንም አለውጠውም :: ትምህርት ያላወከውን ለማወቅ የሚያስችልህ መሣሪያ ነው :: መስፍን ! ብዙ ጊዜ ትምህርትን በጣም አጥላልተህ ታወራለህ :: ምክንያቱን ባውቅ ግን ደስ ይለኛል :: »

ተላቀቅኩ ብዬ በማሰብ አንቺን መረጥኩ ። ታዲያ ልዩነታችን እንደዚህ የሠፋ ይሆናል ብዬ አላሰብኩም ነበር ። »

« ልዩነታችን እንዴት ይሰፋል ? »

« አን ሞስት አፍ ዘ ላይፍ ኢሹስ »

« ለምን ግልፅ አታደርገውም መስፍን ? »

« አጭር ጊዜ የሚበቃን አይመስለኝም ። ለማንኛውም በጥሞና ለመጫወት መኪናውን ላቁም » አለና ፍሬቻውን ወደቀኝ አሳይቶ መውጫው ላይ ወዳለው መናፈሻ ዳር አስይዞ አቆመ ።

« ሕሊና መቼም በዕድሜ ከአንቺ ጠና ያልኩ ሰው ነኝ። ስለዚህ በዚህ ዓለም ላይ ከአንቺ ረዘም ላለ ጊዜ ቆይቻለሁ ። እኔ አንቺን ሳገባ የመጀመሪያው ምኞቴ በህይወቴ ላደርገው ፈልጌ ሳላሟላ ያሳለፍኩትን ሁሉ ለመፈፀም ነበር ። ታዲያ የአንቺ የመጀመሪያ ፍላጎት ደግሞ ልጅ መውለድ ሳይሆን ትምህርት መማር ነው ። ይህ የሁለታችን ፍላጎት ያለመጣጣም በመካከላችን ያለውን ልዩነት እያጋነነና እያሠፋ በተራ ነገሮች ላይ እንኳን ለመስማማት አለመቻላችን ሁልግዜ ያሳስበኛል ። »

« መስፍን ስለ እኔ የትምህርት ፍላጎት ከመጀመሪያ ቀን ግንኙነታችን ጀምሮ እስከዛሬ ያላነሳሁበት ጊዜ አልነበረም ። እውነትህን ነው ፤ ለእኔ ከሁሉም በላይ ትምህርት ነው ። ትምህርት ከወንድ እኩል ለሴት ልጅም ጠቃሚ መሆኑን የምትረዳ ይመስለኛል። እየህ ፤ ለእኔ ትምህርት ለህይወቴ መነሻና መንደርደሪያ አውራጎዳና ነው ። የቤት ልጅ ማለት ሴት ሆና የተፈጠረች ፤ ባለመማሯና ባለማወቋ ምርጫዋ የጠበበ ባሏን ለማርካትና ፍላጎቱን ለማሟላት የተፈጠረች መሆኗን አምና የተቀበለች ማለት እንዳልሆነ ለአንተ ልነግርህ አልችልም » አለችው ኮስተር ብላ ።

« አልገባኝም ። ትዳር ፤ ትምህርትና ልጅ አንድላይ አይሄዱም ያለሽ ማን ነው ? ።



« አይ መስፍን . . . » ሕሊና ሀሳቧን ለማሰባሰብ ሞከረች ።

« ሀሳቤን አልተረዳህኝም ብዬ አልገምትም ። በተለይ እዚህ አገር ልጅ ወልዶ ማሳደግ ቀላል እንዳልሆነ ታውቃለህ እንኳን ከትምህርት ጋር ከሥራም ጋር ይከብዳል ። እየህ ጋብቻውን ፈፅመናል ። ከመውለዴ በፊት ደግሞ መማር ስለምፈልግ የእኔ ትምህርት በአንተ የልጅ መውለድ ፍላጎትህ ላይ እንቅፋት መሆኑን ጠቅሰሃል ። አንዳንድ የሀገራችን ወንዶች የሚሉትም እንደዚሁ ነው። ልጅን እንደተፈጥሮ ፀጋ በመቁጠር ማሳደጉን በጋራ ኃላፊነት እንደመወጣት ፍጹማዊ የሴቶች ኃላፊነት ብቻ ነው ብለው ያምናሉ ። ሌሎቹም ሴትን ማስረገዝና ማስወለድ ሲደፈርስ የተቃረበን ትዳር ማረጋጊያና ሲሞት የተቃረበን ፍቅር ማነቃቂያ አድርገው ይጠቀሙበታል ። ማለቴ በየምክንያቱ ትዳሩ ያልተስማማትን ወይንም በፍቅሩ ያልረካችን ሴት በቁጥጥር ሥር ለማዋል ፤ የሴቶች እርግዝናና ልጅ መውለድ እነኚህ ወንዶች የማይበጠስ ሠንሰለት አድርገው ይወስዱታል ። » ። ሕሊና ለመቀጠል አልፈለገችም ለመናገር የፈለገችውን በእንጥልጥል ተወችው ።

« ኦ ማይ ጋድ . . . » መስፍን የሰማውን አላመነም ።

« እንደዚህ የተበደላችሁ አልመሰለኝም ነበር ። ሁኔታው የተጋነነ ይመስላል ። »

ይህን እኮ ነው የምልህ ! ሴቶች ስለ እኩልነት ሲያወሩና በደላቸውን ሲናገሩ ለምን የተጋነነ ይሆናል ? አንድ ነገር ግልጽ እንዲሆንልህ እፈልጋለሁ ። አንተ እኔ የማስበውን በግድ ተቀበል አልልህም ከአንተም እንደዚሁ እጠብቃለሁ ። ልዩነታችን ሊያሳድገንና ሊያስተምረን ይገባል እንጂ ሊያራርቀንና ሊያናቁረን አይገባም ። ከአንድ ምንጭ የተቀዳ ውሃ እንደ'ንሆንም አንተም አትጠብቅ እኔም አልጠብቅም ።

« አባባልሽ ብዙውን ነገር ያስረዳኝ መሰለኝ ። ታዲያ ተከሊሉ፣ የማረጅ ሰርሞኒው ፣ መሃላው ለምኑ ነው ? እንደአባባልሽ ከሆነ ትዳር የሚለው ቃል ደባል በሚለው ቢለወጥ ተገቢ መሰለኝ ። » መስፍን የሕሊናን አባባል በአጠቃላይ አልተቀበለም ። እውነት ነው የምልህ « እኔነቴን በተፈጠርዬ ዝቅ የሚያደርገኝና ነፃነቴን ለሌላ አሳልፎ የሚሰጥ ባህልም ሆነ ሀይማኖት መሠረት የለውም ፣ በአምላክ ዘንድም ተቀባይነት አያገኝም በማለት ወደ መስፍን ተመለከተች ። መስፍን ሀሳቡን ውጦ ትንሽ አሰላሰለ ።

« እኔ እኮ አንቺን እኩል አይደለሽም ብዬ አላውቅም በማደርገው ሁሉ ክብርሽን ነቅፌ ወይንም ዘንግቼ ያለፍኩበት ጊዜ የለም ታዲያ ምኑ ላይ ነው እኩልነታችን የተዛባው ? »

መስፍን የእኔ አባባል በአጠቃላይ አንዳንዱ ባሕላችን በሴቶች ላይ የሚያደርገውን ተጽእኖ የሚገልጽ ነው ። አንተ ከአካባቢህ ባካበትከው ልምድ እራስህን ሞርደህ የሀገር ቤቱን ዓይን አውጣ ተጽእኖ ስልት በተሞላው ለስላሳ አቀራረብ ሸፋፍነህ ነው ያቀረብከው።

« የእኔ አባባል የገባሽ አልመሰለኝም ። ለእኔ በመጀመሪያ ደረጃ ያለ ልጅ ትዳር ምንም ትርጉም አይሰጠኝም ። ሌላው ከአንቺ ልጅ ለመውለድ የፈለኩበት ምክንያት ለአንቺው ለራስሽም ዕንቆቅልሽ አይደለም ። እወድሻለሁ ። ባለቤቴ ነሽ . . . . አይ ሆፕ ማይ አንሰር ዊል ቬሪ ማች ሳትስፋይ ዩ » ሕሊና የመስፍንን አባባል እያጣጣመች በዓይኗ ገረመመችው ።

« በእውነት . . . በእውነት . . . ትወደኛለህ ? »

« ከዚህ የበለጠ እንዴት ብዬ ልንገርሽ ? እወድሻለሁ ! . . . እወድሻለሁ በቃ ። አደባባይ ወጥቼ አዋጅ እንድለፍፍ ትፈልጊያለሽ ? »



* * *

ራሄልና ሕሊና በጠዋት ተያይዘው ለመውጣት ተዘጋጅተዋል። መስፍን የሁለቱ ግንኙነት እንዲቋረጥ ጥረት ቢያደርግም አልተሳካለትም ። ለእሱ ግልፅ ባልሆነለት ሁኔታ እጅና ጓንት ሆነዋል ። መስፍን ከመኝታው ከመነሳቱ በፊት ራሄል ቤታቸው ደረሰች ።

« ሃኒ ዩ ዲድ ኖት ቴል ሚ ዛት ዩ ሃቭ አን አፖይንትመንት ዊዝ ራሄል ! »

« ጥናት ላይ አምሽቼ ስለተኛሁ ትዝም አላለኝ ። ይቅርታ » አለችው የመለማመጥ በመሰለ አቀራረብ ።

« ቴ ኬር ዩ ቱ ገልስ » ድምፁን ከፍ አድርጐ ተናገረ ። መስፍን በተኛበት ስለራሄልና ስለሕሊና ግንኙነት አሰበ ። ራሄል ከእርሱ ጋር ስለነበራቸውና ስላላቸው ግንኙነት ለሕሊና ትነግራታለች ብሎ ጥርጣሬ ቢገባውም ሀሳቡ እራሱን መልሶ ዘገነነው ።

« ጋሼ ያለውን ምክር ብሰማ ከዚህ ሁሉ እልደርስም ነበር ። አሁንም ለምን ግልፅ አድርጌ እንደማልነግራት አላውቅም ። ምንድን ነው ወደ ኋላ ጎትቶ የያዘኝ ? እውነት ጋሼ እንደሚለው ከራሄል ጋር ፍቅር ይዞኝ ይሆን ? . . . »

ራሄል ፣ ሕሊናን ከአንድ ትልቅ ህንፃ ስር ወደሚገኝ ትልቅ የልብስ መጋዘን ይዛት ገባች ።

« አይዞሽ አትፍሪ ፤ ማናጀሩን በደንብ ስላነጋገርኩት ግድ የለም ብሎኛል » ስትል ሕሊናን አደፋፈረቻት ። የሸቀጡን ክፍል አልፈው ወደ ውስጥ ዘለቁ ። ራሄል ሕሊናን ከአንድ ጥግ አቆይታ ፊት ለፊት የነበረውን በር በዝግታ ከፍታ ገባች ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ፈገግታ ተላብሳ ተመለሰች ።

ሕሊና ለመጀመሪያ ጊዜ በአሜሪካን ምድር ሥራ ዓለም ውስጥ ገባች ። ከራሄል ጋር በአንድ የልብስ መደብር አብረው

መስራት ጀመሩ ። ይህ ሁሉ ሲሆን መስፍን የሚያውቀው ነገር አልነበረም ። በየትኛውም ሁኔታ መስፍን ማወቅ እንዳለበት ብታምንም ማሳወቅ ያለባትን ወቅት መወሰኑ ሳይቻላት ቀየ ። ከዚህ ይልቅ ሥራውን በመለማመድ ላይ ትኩረቷን አደረገች ። ሥራውን በቀላሉ የምትለምደው አልመስልሽ እያላት አለመረጋጋት ፈጥሮባት ነበር ።

« ታዲያስ ቀላል አይደለም ? » ስትል ራሄል ጠየቀቻት በዕረፍት ጊዜአቸው ሠራተኛ ክፍል ውስጥ እንዳሉ ። የሕሊና ለሥራው አዲስ መሆን ይታወቅ ነበር ።

« ሰውየው በጣም ስለሚፈጥን አልፎ አልፎ የሚለው አይገባኝም ። በስተቀረ ደህና ይመስላል ። » ቀና ብላ ወደ ራሄል ተመለከተች ።

« ግን ለምንድን ነው ገበያተኛ ሳይኖር መቀመጥ የማይፈቀደው ? እግሬንና ወገቤን በጣም ነው ያመመኝ ። » አለች ሕሊና ወገቧን በእጆቿ በመዳሰስ ህመሟን እየገለፀች ።

« አይዞሽ ፤ የማይለመድ ነገር የለም ። እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ እንደዚሁ ነበርኩ ። » ራሄል ሕሊናን ለማፅናናት ሞከረች ።

« ማርጀቴ ነው እንዴ ? ድሮ ጠንካራ ነበርኩ ። እንኳንና ለሠዓታት ለቀናትም ብቆም እንደዚህ ጉልበቴ በቀላሉ የሚሸነፍ አይመስለኝም ነበር ። » አለች ሕሊና ቀኝ እጇን ከወገቧ ሳታነሳ ።

« ቤት ስትገቢ እንዳትረሺ ። እግርሽን ለብ ባለ ውሃ ጨው ጨምረሽ ዘፍዝፊው ። ለእግርሽ ጥሩ ነው ፤ ይፍታታልሻል » አለቻት ራሄል በምክር መልክ ።

« እባክሽን ብልሃት ብልሃቱን ንገሪኝ ። እንዲህ በቀላሉ የምወጣው አልመሰለኝም »

« አ ! ማይ ጋድ ! በእኔ ይሁንብሽ ። ህመሙ ፤ ቁርጠቱ ሁሉ ለጥቂት ቀናት ነው የሚቆየው ። ሳታውቂው ይጠፋል ። »



ሕሊና እግሮቿን በሙቅ ውሃ ዘፍዝፋ ቴሌቪዥን ከፍታ መመልከት እንደጀመረች መስፍን በሩን ከፍቶ ገባ ።

« መቼም ይሄ የሀገር ቤት ልማድ አይቀርም ። ለምን ሻወር አትወስጂም ? » በማለት ሕሊናን ከእግር እስከራሷ ቃኘ ።

« የዛሬውስ የልምድ ሳይሆን የመከራ ነው ። ይልቅ ተቀመጥና ስለ ቀኑ ውሎዬ ላጫውትህ » አለችው መስፍን አጠገቧ እንዲቀመጥ እየጋበዘችው ።

« ሥራ ገባሁ ፤ አያስገርምም ? »

« ምን ያስገርማል ፤ ደስ ይላል እንጂ »

« ስለ ደስታው እንኳ አላውቅም ። ለማንኛውም ከራሄል ጋር ነው የምሰራው ። »

« ከራሄል ጋር ? . . . መልካም ነዋ ፤ ምን አለ ! « አላት በቸልታ ። ፊቱን ከፊቷ እያሸሸ ።

* * *

ሕሊና አሜሪካን አገር የገባችበትን አምስተኛ ዓመት አከበረች:: በዚህ የህይወት ጊዜዋ የምታየውን ፣ የምታደርገውን ፣ የምትቀበለውንና የምትጠላውን ሁሉ በቅርብ የምታማክራት ጓደኛዋ ራሄል ብቻ ነበረች :: የሥራ ቅርበታቸው ፣ የፆታ አመለካከት ባህሪቸውና የቅርብና የሩቅ ትዝታቸው እያደገ ፣ እየጠለቀና እየጠበቀ መጣ :: የግል ህይወታቸው እየከሰመ ፣ ለጋራ ሀሳብና ፍላጎት ቦታ እየለቀቀ ፣ አንድነታቸውን አጠናከረ :: ራሄል መኖሪያዋን ለነመስፍን ቅርብ ወደሆነ ቤት ቀየረች :: ይህም ሁለቱ ጓደኛሞች በጋራ የሚሆኑበትን ስለአረዘመው የቀኑ ፣ የሣምንቱ ብሎም የዓመት ዕቅዳቸውን በማጣመር የትምህርት ፣ የሥራና የትርፍ ጊዜአቸውን በማቀናጀት ራሳቸውን ለማሳደግና ከአካባቢው ጋር ለማመሳሰል ሞከሩ::

ራሄል ለመስፍን ያላት ስሜት የቁጭትም የብቀላም ነበር :: ሆኖም ሁኔታውን በብልሃትና በዘዴ ይዛ ለመስፍን የነበራትን ጥላቻ ከሕሊና ጋር በግልፅ ለማውራት ብትችልም ሙሉ በሙሉ ሕሊና ለምትጠይቃት ጥያቄ በቂ መልስ ለመስጠት አልቻለችም :: የሕሊና ጥያቄዎች ያልመረመረችውንና ያልዳሰሰችውን የግል ስሜቷን ደግማ ደጋግማ እንድታስብበት ገፋፉት :: ሆኖም ከመስፍን ጋር ያሳለፉት ጥሩና መጥፎ ጊዜያት ስሜቷን መሻማቱ አልቀረም :: ይህን ግራ የሚያጋባ ስሜቷን ለማሸነፍና ከእራሷ ላይ ለማስወገድ ሌላ ሰው በመውደድ እራሷን ለማባበል ሞከረች :: በዚህ ሃሳቧ ግን አልገፋችበትም :: የመስፍንና የእርሷ ግንኙነት ትርጉም አልባ መሆኑን ውሎ ሲያድር ተረዳች :: ራሄል ይህን የውስጥ ስሜቷን ለሕሊና ገልፃላት አታውቅም :: ሕሊና ግን ከራሄል ንግግርና ድርጊት



ለመስፍን ያላትን ጥልቅ ስሜት ለመረዳት አላዳገታትም :: እያወቀች ያላወቀች በማስመሰል ትዳሯንና ጓደኛዋን ጎን ለጎን ማስታመሙን ቀጠለችበት ::

ፍጹማዊ የሆነው የአባቷ ምክር ነፃ ፍላጎቷን ለማራመድ የሚያስችላት ብቸኛ መፅናኛዋ ነው :: ያሬድ ፣ ሀሰንና መስፍን መልካምና ውጤታማ ለውጥ እንዲኖራት ቢረዷትም ሁሉም የራሳቸው የሆነ የመጨረሻ ግብ እንዳላቸው አውቃለች :: በእርሷና በራሄል መሀከል ያለው አንድነት ከልዩነታቸው በእጥፍ ድርብ ይበልጣል በማለት አሰበች ::

« ለጋሼ ያሬድ ያለኝ ስሜት ትርጉም በሌለው መጀመሪያና መጨረሻ ተንጠልጥሎ ቀረ :: ስለ እርሱ ባሰብኩ ቁጥር ሀሳቤን አሰባስቤ ደግ ነው ክፉ ፣ እወደዋለሁ እጠላዋለሁ ለማለት እንኳ አልቻልኩም :: ከህይወቴ ፍጹም ስርዤ ላወጣውም አልሞክርም ፣ አልችልም :: ጋሼ ያሬድ ከሌሎች ወንዶች ሁሉ የተለየ ነው » በማለት የተምታታ ሀሳቧን ገመገመች :: የእርሷና የራሄል ጓደኝነት መነሻ መስፍን ቢሆንም እያንዳንዳቸው ያሉበት ባህል የፈጠረባቸው ተፅእኖ ቀላል አልነበረም :: « የሰው ባህሪይ በአካባቢው ይጠነሰሳል ፣ ይታነፃል ፣ አካባቢውንም ይመስላል :: » በማለት ሕሊና ከየት ተነስታ የት እንደደረሰች ማሰቧን ቀጠለች ::

« . . . ራሄልን . . . መጀመሪያ እንደአገኘኋት ዘላባጅ እብድ ናት ብዬ ነበር ያሰብኩት :: ከዛ አልፈን በቁምነገር ተሳሰርን :: እኔ ወይስ እርሷ የተለወጥነው ወይንስ እርስ በእርሳችን ተማማርን »

ሕሊና ፣ የራሄልን ጉዳይ ማሰላሰል እንደጀመረች ወደ ኋላ ተመልሳ የከበቡሽን ጓደኝነት አስታወሰች :: ስለ ከበቡሽ እሁን ያላትን ፍቅርና እክብሮት ከራሄል ጋር አመሳሰለች :: « ከልብ የመነጨ ጓደኝነት ዘለዓለማዊ ነው » በማለት ሁለቱም ለህይወቷ ስለ አደረጉት መልካም እስተዋጽኦ አመሰገነች ::

*　　*　　*

ቀኑ አርብ ፣ ወራቱ ፀደይ ነበር ። ፀሐይ በወርቃማ ነፀብራቋ ምድሩን አልብሳ ወደ መጥለቁ ተቃርባለች ። በመንፈስ ላይ ያለው መልካም የፀደይ አየር ለከተማው ልዩ ድምቀት ሰጥቶታል ። ዛፎቹ ለምልመው ፣ ምድሩ አረንጓዴ ሳር ለብሶ ፣ በየመናፈሻውና በየመኖሪያ ቤቱ አካባቢ የተተከሉ አበባዎች ፈክተው አካባቢውን አሸብርቀውታል ። የወራቱን አመቺነት በመሻማት መንገድ ላይ ውር ውር የሚለው የሰው ብዛትና ዓይነት ለአንዳች ህዝባዊ በዓል ዝግጅት የሚያደርግ ይመስል ነበር ። ሕሊና ከሥራዋ እንደወጣች አውቶቡስ ተሳፍራ ወደ ትምህርት ቤት አመራች ። ለመጀመሪያ ክፍለ ጊዜዋ የጽሁፍ ፈተና ዝግጅት የሚረዳ በመሆኑ ለሕሊና ብዙ ጊዜ አልፈጀባትም ። ሁለተኛና ሦስተኛ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ደግሞ ለዕለቱ በመሰረዙ ወደ ቤቷ ከመመለስ ሌላ ምርጫ አልነበራትም ። ጊዜዋን እንዴት እንደምታሳልፍ እያሰላች ወደ ቤቷ አዘገመች ።

« የሳምንቱ ድካም . . . በቀላሉ አይለቀኝም ። እንደገባሁ ሻወር ወስጄ አልጋዬ ላይ እሰፍራለሁ ። » ስትል ፍጹም እረፍት ለማድረግ ራሷን አዘጋጅታ ፣ ቤቷ ለመድረስ እርምጃዋን አፋጠነች።

ሕሊና ቤቷ በር ስትደርስ ኃይለኛ ድካም ውስጥ ነበረች ። በትከሻዋ ያንጠለጠለችውን የደብተር ቦርሳ አሳርፋ የቤቱን በር ቁልፍ አወጣች ። በሩ አልከፈት ስለአላት መልሳ መላልሳ ቁልፎቹን በመለዋወጥ ብትሞክርም የሚከፍተው አልነበረም ። በሩን ደግማ ደጋግማ ብታንኳኳም መልስ የሰጠ የለም ። ጮክ ብላ « መስፍን ! መስፍን ! » ስትል ለረዥም ጊዜ ተጣራች ። ከግራና ከቀኝ የነበሩ



ጎረቤቶቿ በድንጋጤ መንፈስ በሮቻቸውን ከፍተው ብቅ ብቅ አሉ ። ሕሊና መሆኗን እንዳወቁ ተመልሰው ወደ ቤታቸው ገብተው በራቸውን ዘጉ ።

ሕሊና በድንጋጤ ተውጣ የምታደርገው ጠፋት ። ጎረቤቶቿን በመረበሿ ተሰምቷት ቆሞ ወደነበረው ሊፍት ገብታ ወደ አሥረኛው ፎቅ ሄደች ። ራሄል ክፍሏ ውስጥ አልነበረችም ።

« ሰዎቹን ምን ዋጣቸው ? . . . እሺ ራሄል የሆነ ነገር አጋጥሟት ሄደች ይባል መስፍን ወዴት ሄደ ? በሩን ደግሞ ምን አደረገው ? የእኔ ቁልፍ ለምን አልከፈተውም ? ቁልፉ ሁለት ጊዜ ዞሯል ። ታዲያ ለምን አልተከፈተም ? » ሕሊና ለጥያቄዋ መልስ ማግኘት አልቻለችም ። ሀሳቧን በማውጣትና በማውረድ ለጥቂት ጊዜያት ራሄል በር ላይ ቆማ ጠበቀች ። ሊፍቱን አልጠበቀችም ። ወደሁለተኛ ፎቅ ቁልቁል ሮጠች ። እንደገና በሩን ለመክፈት ሞከረች። ኃይሏን ሁሉ የተዘጋው በር ላይ በማሳረፍ ስትገፋው በሩ ተበርግዶ ተከፈተ ።

ከግድግዳ ጋር በመጋጨት የፍንዳታ ያህል ድምፅ አሰማ ። በሩን ለመዝጋት ሳትቸኩል ፈጥና ወደ ሳሎን አመራች ።

« መስፍን ! መስፍን ! » ደጋግማ ተጣራች ። ሳሎን ቤቱን አልፋ ወደ ገበታ ቤት ገባች ። ያየችውን አላመነችም ። ሕሊና ሀሳቧን ለማሰባሰብ ሞከረች ። ከወንበሮቹ በአንዱ ጠረጴዛ ላይ አረፍ አለች ። ጠረጴዛው ላይ የተቀመጡትን የምግብ ሳህኖችና ብርጭቆዎች ተመለከተች ። « ማን ነበር ወይስ እነማን ነበሩ ? » በማለት ራሷን ጠየቀች ። መጀመሪያውኑ በሩ ከውስጥ እንደተቀረቀረ ጥርጣሬው ነበራት ። ሆኖም ማን ለምን እንደቀረቀረው መገመት አልቻለችም ። ወደ ምግብ ጠረጴዛው ደግማ ቀረበች ። ጠረጴዛው ላይ የነበሩት ሳህኖችና ብርጭቆዎች ጥንድ ጥንድ ነበሩ ። በምግቡ ሥነ ሥርአት ላይ ሁለት ሰዎች እንደነበሩ አስተዋለች ። ሀሳቧን

ሳትቋጭ ከፍታ የተወችውን በር ለመዝጋት ወደ ዋናው በር አዘገመች:: በሩን ከዘጋች በኋላ ወደመኝታ ቤቷ ገብታ አልጋዋ ላይ ልትቀመጥ ስትል ዓይኖቿ አንድ ቦታ ላይ ተተክለው ቀሩ :: ያየችውን አላመነችም ቀይ የውስጥ ሱሪ ! በጣቶቿ ጫፍ አንጠልጥላ አገላብጣ ተመለከተችው :: ራሷን በማወዛወዝ በመፀየፍ መልሳ አልጋው ላይ ወረወረችው ከመኝታ ቤቷ በዝግታ በሩን ከፍታ ወጣች:: ብዙም ሳትራመድ መስፍን በበሩ ሲገባ በማየቷ ባለችበት ረግታ ቆመች :: መስፍንን በንዴትና በቁጭት ከላይ እስከ ታች ገላመጠችው ::

« ሃይ ሃኒ ! ኖ ስኩል ቱ ዴይ ? » በማለት መስፍን ሕሊናን ለማቀፍ ሲጠጋ ሕሊና እራሷን አንድ እርምጃ ወደ ኋላ አሸሸች ::

« ምን ሆንሽ ደግሞ ? » አለ በእጁ ይዞ ለማቆም እየሞከረ :: የመኝታ ቤቱን በር በቁጣ ዘግታ ከውስጥ ቆለፈች :: መስፍን በሩን እንድትከፍትለት በልመና መልክ ቢያባብላትም ፍቃደኛ ሳትሆን ቀረች:: ድርጊቱ እንቆቅልሽ ሆነባት ::

ሁሉን ነገር ችላ ብላ ሻወር ወሰደች :: ንዴቷን ከድካሟ ጋር በመታጠብ እራሷን ለማረጋጋት ታገለች :: መስፍን ሳሎን ተቀምጦ ቴሌቪዥን ይመለከት ነበር :: ከሻውር መልስ አጠገቡ በነበረው በአንደኛው ሶፋ ለውነቷን አሳርፋ ጥቂት ጊዜ በዝምታ አሳለፈች:: መስፍን በስርቆሽ ሲመለከታት ዓይን ለዓይን ተያዩ ::

« እስቲ የሆነውን አስረዳኝ :: ለእኔ መቼም ትልቅ ዕንቆቅልሽ ነው የሆነብኝ » ስትል አፈጠጠችበት :: መስፍን ሶፋው ላይ በመገላበጥ ጥቂት ታሸ ::

« ዋት ዱ ዩ ዋንት ሚ ቱ ኤክስፕሌይን » ሕሊና ሊሸሿት ያሉትን የመስፍንን ዓይኖች በዓይኖቿ ተከተለች ::

« ዛሬ የሆነውን ማወቅ እፈልጋለሁ :: »



« ከስራ እንደመጣሁ ምግብ በልቼ ዎክ ለማድረግ ወጣሁ:: አሁን ስመለስ አንቺ እሳት ጎርሰሽ እሳት ለብለሽ ጠበቅሽኝ :: እኔም የሆነውን አላውቅም »

« እኔ በሩን ሳንኳኳ ቤት ውስጥ አልነበርክም ? »

« ዋት አር ዩ ቶኪንግ አባውት ? »

« እኔ ከትምህርት ቤት ስመጣ በሩን ለመክፈት ብሞክር እምቢ አለኝ :: ያስ ዛሬ ይህ በር እንዲህ ሆኖ አያውቅም :: »

« ድንገት ዩ ማይት ሃቭ ሚስድ ዘ ራይት ኪ »

« ኖ አይ አም ሹር ፤ አልተሳሳትኩም :: በተጨማሪም ምሳህን ብቻህን አልበላህም :: » አለችውና ተንደርድራ ወደ ምግብ ቤት ሮጣ በእጇ ጭላጭ የብርትኳን ጭማቂ ያለባቸው ሁለት ብርጭቆዎች ይዛ ተመለሰች ::

« አንደኛው ብርጭቆ ቆሻሻ ነበር :: አይ ዩዝድ አናዘር ዋን :: ወዴት እያመራሽ እንደሆነ አልገባኝም :: » ይሄስ አለችው አንደኛውን ብርጭቆ ወደፊቱ ደቅና በአመልካች ጣቷ ብርጭቆው ጠርዝ ላይ ያለውን ቀይ የሊፒስቲክ ቀለም እያሳየችው ::

የመስፍን አነጋገር የሕሊናን ትዕግሥት ተፈታተነው :: ከተቀመጠችበት ተስፈንጥራ ተነስታ ወደ መኝታ ቤት ገባች :: በቀኝ እጇ ቀይ የውስጥ ሱሪ አንጠልጥላ ተመለሰች :: የያዘችው የውስጥ ሱሪ መስፍንን አስደነገጠው :: ዓይኖቹን ወደ ምድር ተከለ ::

« እኔ ቀይ የውስጥ ሱሪ በህይወቴ ገዝቼ አላውቅም :: ይሄኛውስ ከየት እንደመጣ ልትነግረኝ ፈቃደኛ ነህ ? » አለችው ንዴት በተሞላበትና በተቆራረጠ አነጋገር ::

መስፍን በጎን አሻቅቦ ወደ ሕሊና ተመለከተ :: ፊት ለፊቱ ወደ አለው ሶፋ እየተመለከተ እንድትቀመጥ ጠየቃት :: በእጇ የያዘችውን የውስጥ ሱሪ ወደ ወንበሩ ወርውራ ሶፋው ጫፍ ላይ

እጆቿን ሰብስባ ተቀመጠች ። በመሀከላቸው ለጥቂት ደቂቃዎች ፀጥታ ሠፈነ ። መስፍን ንግግሩን ከየት እንደሚጀምር አሰበ ።

« ሕሊና ፣ ሌት አስ ሊብ ኢት አስ ኢት ኢዝ ። እንደዚሁ እንኑር ። »

« ኖ መስፍን እንደዚህ ዓይነት የድብብቆሽ ኑሮ አልፈልግም። ግልፅልጽ አድርገን ካልተወያየን . . . »

« ኦኬ ! ኦኬ ! ጉደዩ እንደዚህ ነው ። እኔና አንቺ እንደ ባልና ሚስት መኖር ካቆምን ቆይተናል ። እኔ እዚህ ቤት የምኖረው እንደ ደባል ነው ። ዩስ ዊ ሼር ኤ ቤድ ኤንድ ኤ ሃውስ በት ኢት ኢዝ ኖት ዛት ማች ኢምፖርታንት ፣ አይ ዱ ኖት ኖው አይ ፊል አይ ሎስት ዩ ሰም ሃው ። »

« ምን ማለትህ እንደሆነ አልገባኝም ። ባልና ሚስት የሚሰሩትን ሁሉ እንሠራለን የአንተ የጋብቻ ትርጉም ምንን እንደሚጨምር አላውቅም ። »

« ሕሊና የአንቺ ጋብቻ በቤትና በመኝታ ላይ መቆራኘትን ብቻ የሚያጠቃልል ከሆነ ለእኔ እውነተኛ ትዳር አይደለም ። » መስፍን ጥቂት አሰብ አድርጎ « አስታውሺ ፣ መጀመሪያ ሀገር ቤት ገና ስንተዋወቅ ሚስት ሳላገባ የቆየሁበት ምክንያት እውነተኛ የትዳር ጓደኛ እስከማገኝ ድረስ ነው ብዬ ነግሬሽ ነበር ። አንቺን ሳገባሽ ከሚስትነት ባሻገር ጓደኝነትሽን በመፈለግ ጭምር ነበር ። አንቺ ግን በአሜሪካን ሀይወትና በትምህርት ዓለም ስለተጠመድሽ ለጓደኝነታችን ምንም ቦታ አልሰጠሽውም ። ተያየን ፣ ተዋደድን ፣ ተፋቀርን ፣ ትዳር ከመሠረትን ይኸው አምስተኛ ዓመታችን አለፈ ። ከዚህ ሁሉ በኋላ አንድ ፍሬ እንኳ ማፍራት አልቻልንም ። » ሕሊና በቀኝ እጇ ጠረጴዛ ላይ ወደ ተቀመጠው የውስጥ ሉሪ አመለከተች ።

« ታዲያ ይሄን ከምትለው ጋር ምን አገናኘው ? »



« የምለውን አዳምጪ ። እኔና አንቺ ስለትዳር ያለን አመለካከት በጣም የተራራቀ ነው ። ለአንቺ ሀይወት የመጀመሪያውና ትልቁ ቁም ነገር ትምህርት ነው ። ለሚቀጥለው እየተዘጋጀሽ ነው ። አይ ዱ ኖት ኒይድ ኤ ፓርት ታይም ዋይፍ ። ዋት አይ ኒድ ኢዝ ኤ ፉል ታይም ዲቮትድ ዋይፍ ኖ ሌስ ! »

« በጣም ትገርማለህ ! በአጠቃላይ አንተ የምትፈልገው እውነተኛ የትዳር ጓደኛ ሳይሆን ልጅ አሳዳጊ ገረድ ነው ። ለመሆኑ የእኔ መማር ለምን ይኼን ያህል ያንገበግብሃል ? ሠርቼ ፣ ለፍቼ ትዳራችንን ከአንተ እኩል ለመደገፍ ጥረት አደርጋለሁ ። ይሄ ደስ ሊያሰኝህና ሊያኮራህ ይገባ ነበር ። »

« አሁን ንግግራችን የትም አያደርሰንም ። በአጠቃላይ ለምሰራው ነገር ሁሉ አይ ነው ዩ ኖው ዘ ኤክስፕለኔሽን ዛት ኢንክሉድስ ቱ ዴይስ እንሲደንት » አላትና ባለችበት ትቷት ወደ መኝታ ቤት ገባ ።

ሕሊና በተፈፀመው ድርጊትና በመስፍን አነጋገር ክፉኛ ስሜቷ በመደፍረሱ ባልጠበቀችው መንገድ ሀይወቷ ተነካ ። ሀሳቧ ሁሉ ባዶ ሆነባት ።

« ትዳር . . . ድሮም ልጨብጠው እንደማልችል የሚሰማኝ ነገር ነበር . . . ። በአንድ በኩል እም ሀቅ ነው ። ሀይወቴ ኢትዮጵያ ከነበርኩበት ጊዜ ተለውጧል ። እኔ እራሴ አንዳንድ ጊዜ ሳስበው ግራ ይገባኛል ። » በማለት ሕሊና ለጥቂት ጊዜ ሀሳቧን ወደ ሀገር ቤት መለስ አደረገች ። አለላ ከተማ የነበረችበትን ቤት አስታወሰች ። ከሀሰን ጋር የነበራትን ጓደኝነትና መጨረሻ ላይ እንዴት እንደተለያዩ አስታወሰች ። ራሷን « የዋህ » በማለት በዛን ወቅት የነበረችበትን ደረጃ ገመገመች ። ከሀሰን ጋር ለመለያየት ራሷን ምን ያህል እንዳስጨነቀች ትዝ አላት ። ሀሰን እንደ ጓደኛ መስፍንን እንደባል

በመውሰድ በሁለቱ ወንዶች መሀከል የነበራቸውን አንድነትና ልዩነት እያወዳደረች ዝርዝር ሁኔታዎችን ተመለከተች ፡፡

« ወንዶች ፣ የሴቶችን ሀይወትና ምንነት ለማንበብ እንደመቻላቸው ሁሉ በቅምሻ ብቻ እራሰቸውን ያረካሉ ፡፡ ደግሞ ወዲያው ይሰለቻሉ ፡፡ ግን እኮ ሁሉም ወንዶች አንድ አይደሉም ፡፡ » ሕሊና ሀሳቧን አሰባስባ ራቅ ወዳለው ትዝታዋ ራሷን አሸጋገረች ፡፡

« ጋሼ ያሬድ ከእነኚህ ሁሉ የተለየ ነው ፡፡ በሴትነቴ ለመርካት አልቸኮለም ፡፡ በኃይልም ለመጠቀም አልሞከረም ፡፡ አስተዋይነቱና ትዕግስቱ ከሁሉም ልዩ ያደርገዋል ፡፡ ጋሼ ያሬድ እንደ ሀይወቱ ይሳሳልኛል ፡፡ እንደሚወደኝም . . . መውደድ . . . ምነው ዘላበድኩ ! » ሕሊና ሀሳቧን ለመግታት ሞከረች ፡፡ በዕድሏ በጣም አዘነች ፡፡ ሳግ ይዟት ዓይኖቿን ወደ ጣሪያው አቀናች ፡፡ ዕንባዋ እንዳይፈስ ታገለች ፡፡ ካለችበት ተነሥታ ወደ መኝታ ክፍል ገባች ፡፡ ቁምሣጥኗን ከፍታ ዕቃዎቿን አስተካከለች ፡፡ ከሀገር ቤት ያመጣችውን ሻንጣ ከፊት አደረገች ፡፡ የመጥረቢያዋን ፎቶግራፍ አንሥታ ወደ ደረቷ በማስጠጋት ከአንዳች ሰው ጋር እንደሚነጋገር ወደ ጣሪያው ተመለከተች ፡፡

« አባዬ ይኼ ደግሞ ሌላው ክፉ ቀን ነው ፡፡ በል እንግዲህ ከዚህ መዓት ደግሞ እንደለመድከው አውጣኝ ፡፡ » አለችና የያዘችውን ፎቶግራፍ ወደ ሻንጣው አስገባች ፡፡ አልጋ ላይ ተከናንቦ የተኛው መስፍን ድምጽ ሲሰማ መገላበጥ ጀመረ ፡፡

ሕሊና ከመስፍን ጋር ደግማ ላለመነጋገር ሻንጣዋን ዘግታ ፈጥና ከክፍሉ በመውጣት የምትፈልጋቸውን ዕቃዎች ከወዲያ ወዲህ እያለች በማነሳሳት ላይ ነበረች ፡፡ መስፍን የመኝታ ቤቱን በር ከፍቶ ወጣ ፡፡



« የት ለመሄድ ነው የምትጣደፊው ? » አላት ከቆመበት ሳይንቀሳቀስ ፤ « ምን ያስቸኩልሻል ፤ ቢነጋልሽ አይሻልም ? » ሲል ጨመረ ፡፡

« ለምኑ ነው የቀኑን ብርሃን የምጠብቀው ፡፡ ከአሁን በኋላ እኔና አንተ በአንድ ጣሪያ ሥር ልናድር አይገባንም ፡፡ »

« ኢፍ ኢት ኢዝ ኖት ሴክረት ዌር አር ዩ ጎይንግ ? »

« ዩትም ብሄድ የትም ፣ አይ ሲንክ ኢት ኢዝ ነን ኦፍ ዩር ቢዝነስ » መስፍን አንድ እርምጃ ወደ ሕሊና ተራመደ ፡፡

« እኔ አባባሌ ለክፉ ነገር አይደለም ፡፡ ከሀገር ነጥዬ ያመጣሁሽ እኔ ነኝ ፡፡ ድንገት እንኳ አንድ ነገር ቢደርስብሽ በማለት ነው ፡፡ ነገር ግን አሜሪካ ነፃ ሀገር ነው . . . ካልፈለግሽ . . . እንደፈለግሽ ለማንኛውም ኪፕ ኢን ተች ፡፡ »

ሕሊና የምትፈልጋቸውን ነገሮች አሰባስባ ሻንጣዋን እየጎተተች ወጣች ፡፡ የራሄልን በር ስታንኳኳ ያልተዘጋጀችበትን የቀኑን ዜና እንዴት አድርጋ እንደምትገልፅላት እያሰበች ነበር ፡፡ በሩ ግን አልተከፈተም ፡፡ እዚያው ቆማ የት እንደምትሄድ በማሰብ ላይ እያለች ድንገት በሩ ተከፈተ ፡፡ ራሄል ነበረች ፡፡ ሕሊና የራሄልን ሁኔታ የቀኑ ሌላ አጋጣሚ ሆኖ አገኘችው ፡፡ ራሄል በሕሊና መምጣት የተገረመች አልመሰለችም ፡፡

« ወጣሽ » አለች ከፊቷ ላይ ተንጨባሮ የተበተነውን ፀጉሯን በከፊል እያስወገደች ፡፡ ራሄል ደስተኛ ለመምሰል ብትሞክርም ፊቷ ላይ የሚታየው ጉስቁልናዋ ለሕሊና በግልፅ ታይቷት ነበር ፡፡ ሕሊና ራሄልን ተከትላ ወደ ውስጥ ገባች ፡፡ ራሄል ያገኘችው ሶፋ ላይ በቁሟ ወደቀችበት ፡፡ ሕሊና ግን ተክዛ መሀል ሳሎን ላይ ፈዛ ቀረች ፡፡

« ተቀመጪ እባክሽ » አለቻት የቆመችውን ሕሊናን በሀዘኔታ እያየቻት ፡፡ እንደመባነን ብላ « እ . . . እሺ » አለቻት ፡፡ ከሄደችበት

የሀሳብ ጉዞ ተመልሳ ከራሄል ፊት ለፊት ተቀምጣ በእርጋታ የራሄልን ሁኔታ እያጠናች ውስጧ ያቆጠቆጠውን ጥርጣሬ ፈራች ፣ ቀፈፋት። ከአካባቢው መራቅ ፣ መሰወር ተመኘች ። በልውጣ ልቅር ስታመነታ ድንገት በሩ ተንኳኳ ። ሕሊና በሩን ከፍታ ወደ ሳሎን ስትመለስ ከኋላዋ መስፍን ተከትሏት ነበር ።

« እንደምን ዋለሽ ራሄል » አለና ሁለቱን ሴቶች አልፎ ወንበር ፈልጎ ተቀመጠ ። ሕሊና የራሄልን ምላሽ ለመስማት በጉጉት ጠበቀች ። እየተጫወቱባት እንዳይሆን ፈጠረዋን ለመነች ። ራሄል ለመስፍን የሰጠችው የሠላምታ አፀፋ ከዘወትር አባባሏ የተለየ አልነበረም ። መስፍን ራሄልን ይቅርታ ከጠየቀ በኋላ « ይኼውልሽ መጨረሻችን እንዲህ ሆነ » በማለት ወደ ሕሊና ተመለከተ ።

« ይህ መቼም የአንተ መጨረሻህ እንጂ የሕሊና እንኳ መጀመሪያዋ ነው ። ለአንተ ሰዎች ሁሉ ለፍላጎትህና ለስሜትህ ማርኪያ ብቻ የተፈጠሩ ናቸው ።መስፍን ! አትሻሻልም ሼም ኦን ዩ። ስነገሩ ይህ እንደሚሆን እጠብቅ ነበር ። ሆኖም በጣም ፈጠነ ። ነገሩን ቅድም በስልክ ስትነግረኝ አላመንኩም ። ለምን እንደነገርከኝም አላወቅሁም ። በሁኔታው ከአንተ ጋር እንድሆን አስበህ ከሆነ ተሳስተሃል ። » ራሄል ከመቀመጫዋ ተነስታ የሕሊናን ሻንጣ ተቀበለች ።

« በል የምትለውን በልና ውጣልን ። ጊዜው እየመሸ ነው እንተኛበት ። » በማለት ሻንጣውን ጎትታ ወደ ውስጥ ገባች ። ራሄል ሰባልና ሚስቱ የውይይት ቦታ በመልቀቅ ተባበረች ።

« ምን አስቸኩለሽ ? ቤቱ የሁለታችንም ነው ። አሁን ሰው ቤት ከማደር ይልቅ ወደ ቤታችን እንሂድ » አላት መስፍን ።

« የምትናገረውን የምታውቅ አይመስለኝም ። » ሕሊና ከተቀመጠችበት ተነስታ ራሄል ወደ አለችበት አመራች ። መስፍን ብቻውን እንደተቀመጠ ቀረ ።



ራሄል ወደ መኝታ ቤት የገባችውን ሕሊናን አቀፈቻት ። ሕሊና ስቅስቅ ብላ እያለቀሰች ሳግ በተሞላው አባባል « እኔን ፣ እህቴን ፣ ጎዳሽ ! ይሄ አረመኔ ለማንም አይተኛም ። አይዞሽ ! አይዞሽ ! » አለች ። ሕሊና በውስጧ ያመቀችውን ሀዘን ፣ ሀፍረት ፣ ውርደት አምቃ ማስቀረት አልቻለችም ። ያቀፈቻትን አጥብቃ ያዘች እንገት ለአንገት ተጣምረው የቅርብ ዘመድ እንደሞተባቸው ስጥቂት ጊዜ ተላቀሱ ።

« ምግብ ለማብሰል ስል ቤቱ ሄጄ ነበር ። ወደ ውስጥ ለመግባት ስሞክር መስፍን ከለከለኝ ። መጀመሪያ አልገባኝም ። ገፍቼው ስገባ ግን ያየሁትን አላመንኩም ። ድርጊቱ በጣም ስለአናደደኝ የምይዘውና የምጨብጠውን አሳጣኝ ። ይሉኝታ ቢስ እሱ ምንም አልመሰለውም ፣ « ሂ ቶልድ ሚ ቱ ጎ አውት ዶንት ኢቨን ትራይ ቱ ዲስግሬስ ማይ ገስት » አለኝ ። ሕሊና ለአንቺ መቼም ኢት ኢዝ ኤ ብለስንግ » አለች ራሄል ዕንባ የሚተፋትን የሕሊናን ዓይኖች እየተመለከተች ። ሕሊና የተፈፀመባት በደል ከባድ ቢሆንም የፈራችውና የጠረጠረችው ዕውን ባለመሆኑ ደስ አላት ። ለራሄል ያላት ፍቅርና አክብሮት የበለጠ ጎለበተ ። ቀደም ስል የነበራትን ጥርጣሬ ከአሁኑ የራሄል ሁኔታ ጋር አነፃጽራ እራሷን ወቀሰች ። ተስፋ በተሞላው አስተያየት ወደ ራሄል ተመለከተች ። ፍፁም ፍቅር በተሞላበት አባባል « አይዞሽ ምንም አልሆንኩም ። አይ ዊል ቢ ኦኬ » አለቻት ።

« ራሄል ይቅርታ አድርጊልኝና እንዲያው ለነገሩ ማን ነበረች ሴትዬዋ ? » ስትል ሕሊና ጠየቀቻት ። ራሄል ለሕሊና ጥያቄ መልስ ለመስጠት አልቸኮለችም ።

« ምን ታደርግልሻለች ። ይልቁንስ ሳይርብሽ አይቀርም ፣ ነይ ምግብ እንብላ » ብላ ወደ ኩሽና መራመድ ጀመረች ።

« ትናደዳለች ብለሽ አትፍሪ ። በእኔና በመስፍን መሀከል ከአሁን በኋላ ግንኙነት ይኖራል ብለሽ አታስቢ » አለች እጇን ይዛ ።

« ስሟን አላውቀውም ። ማን ብዬ ብነግርሽ ማንን ታውቂያለሽ ? »

« በእናትሽ አሜሪካዊት ናት ? » አለች ለማወቅ መጓጓቷ እያስታወቀባት ።

« አዎ አሜሪካዊት ናት ። በሀገሩ አባባል አፍሪካን አሜሪካን ነች ። ጥቁር ሆነች ነጭ አሜሪካዊት ኢትዮጵያዊት ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ጉዳዩ የእርሱ ነው ። እርሱ ይቸገርበት ። » ተያይዘው ወደ ኩሽና ገቡ ።

* * *

የመስፍንና የሒሊናን መለያየት ዘመድ አዝማዱ እንደሰሙ የቅርቡ በስልክ እና በግንባር የሩቁ ደግሞ ደብዳቤ በመፃፍ ተስማምተው አብረው እንዲኖሩ ተማፀኑ ። መስፍንም በተቻለው መጠን ሒሊናን ለማግባባት ሞከረ ። ሆኖም ሒሊና በመለያየታቸው በመፅናቷ ምክሩና ልመናው ሊበግራት አልቻለም ።

አበራና ከበቡሽ ፣ እንዲሁም ወ/ሮ በላይነሽ « በሰው ሀገር እንዳትንከራተቺ ትዳርሽን አትፍቺ » በማለት የመቆርቆር ስሜታቸውን ቢገልጹላትም ሒሊና ግን ልትለወጥ አልቻለችም ። ሒሊና ከመስፍን ከተለየችበት ዕለት አንስቶ ለሁለት ወራት ያህል ከራሄል ጋር በአንድ ቤት ተዳብለው መኖር ጀመሩ ። ራሄል ለሒሊና ብቸኛና የቅርብ ሰው በመሆኗ ሒሊና ጉዳቷን ፣ ደስታዋን እያዋየቻት ጊዜዋን አሳለፈች ።

ሙሉጌታ የወንድሙን ፀባይ አስቀድሞ ስለሚያውቀው በሁለቱ መለያየት ብዙም አልተገረመም ። ሒሊና በመለያየቱ



መፅናቷን ካረጋገጠ በኋላ በእርሱ በኩል ምንም ዓይነት ቅሬታ እንዳይሰማት ገልጾ በቸገራት ጊዜ ሁሉ ከጎኗ እንደሚሆን ነገራት ።

« ሒሊና እኛና አንቺ ቤተሰቦች ነን ። መወለድ ቋንቋ ነው ። የእኛን ቤተሰብ ታሪክ ተካፍለሻል ። በአንቺና በመስፍን መሀከል ስለተፈጠረው ያለመግባባት በጣም አዝናለሁ ። ቢሆንም ለመለያየት ያደረግሽውን ውሳኔ እከብረዋለሁ ። »

አበራና ከበቡሽ የፍቺው ወሬ እንደደረሳቸው የማበረታቻና የማፅናኛ ደብዳቤ ፃፉላት ።

*« ታስታውሺ እንደሆን ገና በፊት ግንኙነታችሁ ሲጠነሰስ አስጠንቅቄሽ ነበር ። ዋናው ነገር ግን ለመማር ያለሽን ጉጉት ስለማውቅ ከአሜሪካን እንድትቀሪ አልገፋፋሁሽም ።*

*የመስፍን ጋብቻ የአንቺን በአሜሪካ የመማር ዕድል ያጣመረ ስለነበር ነጥሎ ማየትና መቀበል አልተቻለም ። ስለመስፍን ፀባይ በደፈናው ለአንቺ መገምገምና ማስረዳት አልፈለኩም ። አስተዋይ በመሆንሽ በቅርቡ ትደርሺበታለሽ ብዬ ገምቼ ነበር ።*

*« እህቴ ሒሊና ከመስፍን በመለየትሽ ብዙ እንደማትቆጪ ተስፋ አለኝ ። መስፍን በአስተሳሰቡ አንቺን አይመጥንም ። የሁለታችሁም አስተዳደግ ለየቅል ነው ያም የራሱ የሆነ ተፅእኖ ይኖረዋል ። አንቺን የሚመኙ ብዙ ናቸው ። ቁም ነገሩ በጣም የምትጓጊለትን ትምህርት ዳር አድርሺ . . . » በአጠቃላይ የደረሰብሽን ችግር በቀላሉ እንደምትወጪ አልጠራጠርም ። ያለፍሽባቸው የህይወት ጉዳናዎች ቀላል አይደሉም ። ባንቺነትሽ በአሸናፊነት*

*ስለተወጣሽው ለኔ ሕሊና ያለምንም መደለያ ቃል ፣ እንዳንቺ ጠንካራ ፣ አስተዋይ፣ ታታሪና ቆራጥ ሴት በህይወቴ አጋጥሞኝ አያውቅም አንቺ የመጀመሪያዋ ነሽ ።*

*በዓይነ ሀሊናዬ የተነሳሽበትንና የደረስሽበትን ሳሰላስል ፣ ድንቅ ሥራ ፣ በጠበበት የተመራ አንዳች የምርመራ ውጤት ይመስላል ። ይህ ረቂቅ መርህ እንደሚቀጥልና የደረሰብሽ ችግር ትዕግስትሽን እንደማይፈታተነው እርግጠኛ ነኝ ። ለዚህ እምነቴ ሌላ ምንም ምክንያት የለኝም ውስጥሽ ከማየው ጥንካሬሽ በስተቀር ። አንቺ ለኔ የሴቶች ሁሉ ቁንጮ እንደንብ ታታሪ፣ ሥራሽ በምሣሌነት ሊጠቀስ የሚገባ ሰብአዊ ንብ ነሽ ።*

የአበራ ደብዳቤ ለሕሊና ምንም አዲስ ነገር ባይጨምርም አባባሉ የእምነቷ መሠረት ከሆነው ከአባቷ ምክር ጋር የተያያዘ በመሆኑ ደጋግማ አነበበችው ። ደብዳቤው ያዘለው መልዕክት አፅናኝና ጥንካሬ እንዲኖራት የሚያበረታታ መሆኑን አሰበች ።

« እስቲ እነማን ናቸው ከእኔ ጋር ለመሆን ምኞት ያላቸው?» በማለት ያለፈ ህይወቷን ለማስታወስ ስትሞክር በደግና በደስታ ትዝታ ሀሳቧን የተሻማው አንድ ሰው ብቻ ነበር ። « አይ ጋሼ ያሬድ ለምን መልሼ መላልሼ በሀሳቤ ውስጥ እንደምሰነቅረው አይገባኝም » በማለት ሀሳቧን ለማሰባሰብ ሞከረች ። ሆኖም የሀገር ቤት ወሬ በተነሳና ደብዳቤ በደረሳት ቁጥር የያሬድ ትዝታ ሀሳቧን መሻማቱ አልቀረም ። ከራሄል ጋር አብራ በመኖር ላይ እያለች ነበር በቅርቡ የፃፈላት ደብዳቤ የደረሳት ።

*« እማሆይ ደብረ ሊባኖስ ከገቡ ቆዩ ። ከተማ ለመኖር ፈቃደኛ አልሆኑም ። « ከምትኩም ዘመድ*



*እንዳይቀብረኝ ለቅሶም እንዳይለቀስልኝ » በማለት ያላቸውን ንብረት በእኔ አደራነት ለአንቺ አውርሰው ሄደዋል ። ደብረ ሊባኖስ ያደረስኳቸው እኔ ነኝ ። አሁን ከአንዲት መነኩሲት ጋር ተዳብለው ነው የሚኖሩት ። ከእርጅናቸው በስተቀር ለጤናቸው ደህና ናቸው ። እማማ በላይነሽም ብቻቸውን መኖር ባለመቻላቸው ከእኔ ጋር መኖር ጀምረዋል ። አልፎ አልፎ ከበቡሽ እየመጣች ትጠይቀናለች ። »*

በማለት ስለ ቤተሰቡ ገለጸ ስለ ራሱ ብዙም አላወራም ። « በጣም ደህና ነኝ » የሚል ቃል ከመጨመር በስተቀር ። ከቤተሰቡ ዜና ቀጥሎ ፣

*« ሕሊና የደረሰብሽን ችግር ባለፈው ጊዜ ከበቡሽ ነገረችኝ ። በአንቺና በባለቤትሽ መሀከል የተፈጠረውን መለያየት ሰምቼ በጣም ነው ያዘንኩት:: ልዩነታችሁን አስወግዳችሁ በሠላም አብራችሁ ለመኖር እንደምትበቁ ተስፋ አደርጋለሁ ። ለማንኛውም በዚህ ቀውጢ ቀን አጠገብሽ ሆኜ በሃሳብ ልረዳሽ ባለመቻሌ በጣም አዝናለሁ ። ሆኖም በደብዳቤና በስልክ የተቻለኝን ለማድረግ እሞክራለሁ ። » በማለት የተሰማውን ገለፀ ።*

የያሬድ አባባል አዲስ አልሆነባትም ። ሆኖም የማይለወጠው ፀባዩና ደግነቱ በመሀከላቸው ተፈጥሮ የነበረውን አለመግባባት አልፎ ለእርሷ እርዳታና ድጋፍ ለመስጠት በመፈለጉ የበለጠ እንድትወደውና እንድታከብረው ጋበዛት ። በፊትም እንደዚሁ ያደርግ ነበር:: ህይወቱን ሰውቶ ለእርሷ ደስታና ደህንነት ብዙ ለፍቷል ። ሳላችለት:: እርሱን በአካል እንድታይ የሆነ ነገር ጎተጎታት ።

« የሰዎች ሁሉ ፍፁም ነው » ብላ አመነች ። ከአባቷ ቀጥሎ ያላትን አክብሮትና መውደድ ለያሬድ ሠጠች ። ናፍቆቷ ስላየለባት በፀጥታ እንባዋን አነባች ።

« ራሄል ከመታጠቢያ ክፍል ስትወጣ በምታየው ነገር ተደናግጣ ምን ሆነሻል ? ማን ሞተ ? » ስትል ጠየቀች ። ሕሊና በእጇ ይዛ የነበረውን ደብዳቤ ሰጠቻት ። ራሄል የደበዳቤውን መልዕክት ደጋግማ ብታነበውም የሕሊና የለቅሶ ምንጭ ግን ሊታያት አልቻለም ።

« ታዲያ ምን ተፈጠረ ? » አለችና መልሱን ከሕሊና ጠበቀች።

« ምን ብዬ ልግለፅልሽ ? እንዴት አድርጌ . . . » ሕሊና ሀሳቧን ለመግለፅ ከራሷ ጋር ታገለች ።

« ጋሼ ያሬድን ታውቂዋለሽ ? ማለቴ ከዚህ በፊት ነግሬሻለሁ ? . . . » ራሄል አለማወቋን አንገቷን በማወዛወዝ ገለፀችላት ። የሚቀጥለውን አረፍተነገር ለመናገር ጥቂት ካመነታች በኋላ ይኼውልሽ ጋሽ ያሬድን ከማንም በላይ የምወደው ወንድሜ ነው። ብላ ከመነሻው እስከመጨረሻው የነበረውን ታሪክ ነገረቻት ። ታዲያ ይኼውልሽ ፧ « ክብሩን እንደዚያ ዝቅ ከአደረኩ በኋላ አሁንም አልተለወጠም ። ከእኔ አልፎ ተርፎ የምወዳቸውንና የምሳሳላቸውን ሰዎች ህይወት እየተንከባከበ ነው ። ውለታው በጣም ከበደኝ ። አሁን ያለሁበትን ህይወት ሳየው በእርሱ ላይ ያደረኩት ሁሉ ፀፀተኝ ። በእሁኗ ሠዓት አጠገቤ እንዲሆን ተመኘሁ ። ግን ምኞቴ እውን ቢሆን ምን እንደማደርግ አላውቅም » አለች ሕሊና ደብዳቤውን እንደገና ለማንበብ እየሞከረች ።

« እንዲያው በደፈናው ናፈቅሁኝ አትይም » አለች ራሄል ሁኔታውን በማቃለል ።



« መናፈቅ ! . . . መናፈቅ . . . እኔ እንጃ የተሰማኝ ግን ከመናፈቅ በላይ ነው ። ምን ብዬ ልንገርሽ ? » ሕሊና ስሜቷን ለመግለጽ አልቻለችም ቃላት አጠራት በረጅሙ ተንፍሳ ወደ ራሄል ተመለከተች ። ዓይኖቿ ከራሄል እርዳታ ሻቱ ።

*　　*　　*

የራሄልና የሕሊና የድበላ ኑሮ ፍጹም ደስታና ፍቅር የተሞላው ቢመስልም አልፎ አልፎ ጥርጣሬ የሚነፍስበት በመሆኑ ሁለቱም የየግል ምስጢራቸውን በማፈን የህሊና ድንበራቸውን አጠበቡ ። በጓደኝነት የሚካፈሉአቸው ቁምነገሮች በብዛት በጠቅላላ ሁኔታዎች ላይ የሚያተኩሩ ሆኑ ። አብረው ከሚያሳልፉት ጊዜያት ይልቅ በግልና በተናጠል የሚያሳልፉት እያመዘነ መጣ ። ይህ ሁኔታ ሕሊናን እንደ ማዕበል ሳታውቀውና ሳትወድ በግድ ወደማትፈልገው አቅጣጫ እንድታተኩር ገፋፋት ።

ራሄል ውጭ ማደር ከጀመረች ሠነበተች ። ይህ የራሄል ፀባይ አዲስ ባይሆንም በአዳር ማግስት የሚኖራት ፀባይ ፈፅሞ ሊገባት አልቻለም ። ውጪ አድራ በተገናኙ ቁጥር ራሄል ከሕሊና ጋር ከማውራት ትቆጠባለች ። ካወራችም ንግግሯን በአጭር በአጭሩ በማድረግ ራሷን ታገላለች ። ብዙ አብረው በኖሩ ቁጥር ራሄል ድብቅ ተፈጥሮ እንዳላት መረዳት ቻለች ።

በሕሊና ግምገማ ራሄል ድብቅ ብቻ አልነበረችም ። ስልት አዋቂና ውስጣዊ ስሜትዋን በቀላሉ በውጪ ገፅታዋ የምትሸፍን ብልህና ብልጥ ሰው እንደሆነች ተገነዘበች ። ጊዜው እያለፈና እየጨመረ በሄደ ቁጥር ይህ የሕሊና ጥርጣሬ እየጎለበተና ፈር እየያዘ

መጣ ። ስለአዳሯ እና ስለምታወጣቸው ወንዶች ጠረጠረች። ራሄልን ልታውቃት አልቻለችም ። ስለምታወጣቸው ወንዶች አልፎ አልፎ ቆንጠር አድርጋ የምትነግራትን ገጣጥማ ራሄልን ለመተርጎም በፈለገች ቁጥር ፣ . . . ባወቀቻት ቁጥር . . . ውስጧ ይረበሻል ።

ቀኑ ቅዳሜ አመሻሹ ላይ ነበር ። ራሄል ያሰወትሮዋ ቤት ውስጥ ዋለች ። ሕሊና በቅዳሜ ምድር ቀኑን አብሯት የሚያሳልፍ ሰው ከብዙ ቅዳሜዎች በኋላ በማግኘቷ ደስታ ተሰምቷት ነበር ። በዚሁ ስሜት ውስጥ ሆና እራት ለማዘጋጀት ምግብ ቤት ጉድ ጉድ በማለት ላይ እንዳለች በመካከል የሆነ የጭንቀት ጥሪ ከመኝታ ክፍል ተሰማት ። ደንግጣ መኝታ ቤት ስትገባ ያየችውን ለማመን ተቸገረች። ራሄል ወለሉ ላይ ተንበርክካ ሽቅብ ከሚላት ሁኔታ ጋር ትንቅንቅ ገጥማለች ።

« ምነው እኔን ! እኔን ! እመመሽ ? » ሕሊና አጠገቧ ተንበርክካ ራሄልን ለማገዝ ሞከረች ።

« አይዞሽ በይው ይውጣልሽ » ያስጨነቃትን እንድታስወግድ ገፋፋቻት ። ከግማሽ ሰዓት የግቢ ነፍስ ውጪ ነፍስ ትግል በኋላ የራሄል ነፍስ ተመለሰ ። በሕሊና እገዛ ከተንበረከከችበት ወለል ተነስታ ወደ መታጠቢያ ቤት ገባች ። ሕሊና ወለሉ ላይ የተዝረከረከውን ቆሻሻ ጠራርጋ መስኮቱን ከፍታ ቤቱን አናፈሰች። ሕሊና የቅያሪ ልብስ ለማዘጋጀት ወደ ራሄል ክፍል ገብታ የራሄልን ቁምሳጥን ከፈተች መሳቢያ ውስጥ ያየችው ነገር ትኩረቷን ሳበው ።

ምንም እንኳ አንድ ቤት በደባልነት ቢኖሩም ሕሊና የራሄልን የግል ዕቃዎች ነክታ አታውቅም ነበር ። ለመጀመሪያ ጊዜ የራሄልን ሳጥን ከፍታ ስትመለከት መሳቢያው ውስጥ ማስታወሻ ደብተር ፣ ጌጣጌጦች ፣ የውስጥ ልብስና ቀበቶዎች እንዲሁም መስፍንና ራሄል በግልና በጋራ የተነሷቸው ፎቶግራፎች ነበሩ ። ከቀበቶዎቹ አንደኛውን አንስታ አገላብጣ ተመለከተች ። የመጀመሪያ ደመወዝዋን



እንደተቀበለች ለመስፍን ማስታወሻ የገዛችው ስጦታ ነበር። ከረባቶቹንም ለመለየት ጊዜ አልፈጀባትም ። የቀድሞ ባሏ የመስፍን የግል ዕቃዎች በራሄል ምስጢራዊ ሳጥን ውስጥ እንዴት ሊገቡ እንደቻሉ ማወቅ አልቻለችም ። ሁለተኛውን መሳቢያ ከፈተች። የውስጥ ሱሪ ! አገላብጣ ተመለከተችው ። ሰውነቷ ተንቀጠቀጠ ። ስሜቷ ተረበሸ ። ያየችውን ላለመቀበል ፣ ከሀሳቧ ጋር ለመቃረን ሞከረች ። በእጇ የያዘችውን ቀይ የውስጥ ሱሪ በጥላቻ ወደአልጋው በኃይል ወርውራ ከመኝታ ቤቱ ተንደርድራ ወጣች ።

ሕሊና በውስጧ የነደደውን ስሜቷን ሳታረጋጋ የራሄልን የስቃይ ድምጽ ስትሰማ ክፍሉን ለቃ ወጣች ። ብቻዋን ሆና ራሷን ለማረጋጋት ቀጥታ ወደ ኩሽና ገባች ። ሕሊና ዓይኗን ሞልታ ራሄልን ለማየት አልፈለገችም ። ለመስራት ያሰበችውን መቀጠል አልቻለችም ። ክስተቱ የምታደርገውን ሁሉ አጨልሞ አመሰካከቷን አዛባው ። ህይወቷን አማረረች ። የቀረበቻቸውን ሰዎች ሁሉ ልታምናቸውና ልትወዳቸው መቻሏን ጠረጠረች ። ግን አልገፋችበትም ።

« ለጨለማ ብርሃን ፣ ለክፋም ደግ አለ ። » ሀሳቧን አሻግራ ወደ አገር ቤት ወረወረች ። ያሬድን አስታወሰች ። አንድም ቀን መጥፎ ሰው ሆኖባት አያውቅም ። እራስዋን አፅናናች ። በያሬድ ውስጥ ደግ ሰዎችን ፈለገች ። እማማ በላይነሽን ፣ ከበቡሽን . . . በሀገር ቤት ለደስታዋና ለተስፋዋ ምክንያት የሆኑ ሰዎችን አስታወሰች። እንደገና ብሩህ ተስፋ ፤ እንደገና አዲስ ህይወት . . . በህይወት ከኖሩ መልካም ነገር አለ . . . ።

ሕሊና እራሷን ገዝታ ምንም እንዳልተፈጠረ እንደቀድሞዋ ወደ ራሄል ተመለሰች ። ራሄልን አረጋግታ ደግፋ መኝታ ቤቷ አስገብታ አስተኛቻት ።

ራሄል ጀርባዋን ለሒሊና ሰጥታ እንቅልፍ እንዲወስዳት በማሰብ ዓይኖቿን ከደነቻቸው ። ሒሊና ለአፍታ በትዝብት ተመልከታት እንገቷን ሰብራ ክፍሉን ለቃ ወጣች ።

* * *

ራሄል የምግብ ፍላጎቷ ቀንሷል ። ሒሊና ያቀረበችላትን ምግብ አፏ ላይ እየተንቀዋለለ መዋጥ ስለአቃታት እንደነገሩ ቀማምሳ ምንም ሳይነካ መልሳዋለች ። ከታመመች አንስቶ የምትበላው ምግብ አይስማማትም በተደጋጋሚ ያስመልሳታል ።

« አንቺ ልጅ ምን ሆነሻል ? ድካም ፣ ማስመለስና የምግብ ሽታ ማስጠላት ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ ? » አለች ሒሊና መብላቱን አቁማ ወደ ራሄል ሙሉ በሙሉ እየተመለከተች ።

« እንደገባኝ የፀነስሽ ይመስለኛል » ስትል አከለች ሒሊና ። ራሄል የሒሊና አመለካከት እንደ ጦር ሲወጋት አንገቷን ሰብራ ራሷን በአምንታ አነቃነቀች ።

« ለመሆኑ ስንት ወሩ ነው ? » ሒሊና ጠየቀች ። ራሄል አራቱን የቀኝ ጣቶችዋን በማውጣት አራት ወር እንደሆነው አስረዳች። ሒሊና ጥቂት አሰበች ። ከመስፍን ቤት ከወጣች አራት ወራት አለፉ ። ፈራች ።

« ይቅርታ አድርጊልኝና . . . ግን ራሄል . . . ከማን እንዳረገዝሽ . . . » አቋረጠች ።

ራሄል ሀሳቧ ቢገባትም ለማደናገር ሞከረች ። ከተቀመጠችበት ተነስታ መኝታ ክፍሏ ገብታ በሩን ጠረቀመች ። ሒሊና ፈራች ። ፍራቻዋ ለራሷ ብቻ አልነበረም ።

ራሄል በፈፀመችው ድርጊት ተፀፅታ በራሷ ላይ ወይም በፅንሱ ላይ ጉዳት እንዳታደርስ ነበር ። ያለወትሮዋ ተከተለቻት ።



የመኝታ በሩን አንኳኳች ። መልስ አልነበረም ። ቢለለቻት ራሷ በሩን ከፍታ ወደ ውስጥ ዘለቀች ። ራሄል አልጋዋ ላይ በደረቷ ተደፍታ ታለቅስ ነበር ። ሒሊና አልጋው ጠርዝ ላይ አረፍ ብላ ራሄልን ከአንገቷ ቀና አድርጋ ፣ ጭኗ ላይ አሳርፋ ፣ ፀጉሯን እያሻሸች ልታረጋጋት ሞከረች ። ለቅሶውና ማባበሉ ለጥቂት ጊዜ ቀጠለ ።

ከቆይታ በኋላ ራሄል በኃይል ተንፍሳ « በመሀከላችን ሌላ ሽማግሌ ሳያስፈልግ የዘላለም ጭንቀቴን ልነግርሽ ብዙ ጊዜ ሞክሬ አቃተኝ » አለቻት ፣ ፀጉሯን እያሻሸች እንደእናት ወደምታባብላት ሒሊና እየተመለከተች ።

« ሽማግሌ ሀገራችን ቀረ . . . » አለች ሒሊና የሆነ ነገር እየተናነቃት ።

ራሄል ራሷን እያጠናከረች ፣ እንባዋን በእጆችዋ እያደራረቀች ከሒሊና ጭን ተነስታ ፊቷን ከሒሊና አዙራ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀመጠች ።

« . . . የምነግርሽን ሳልጨርስ እንዳታቋርጪኝ ። መቼም የምነግርሽ እንደሚያስገርምሽና እንደሚያስቆጣሽ አውቃለሁ ። ብትቆጪም አልፈርድብሽም ። ሒሊና በጣም የምወድሽና የማከብርሽ ጓደኛዬ ነሽ ። ስለዚህም ነው ዛሬ ይህን ታላቅ ምስጢር የምገልፅልሽ . . . » ሁለቱም ባሉበት በዝምታ ለጥቂት ጊዜያት ቆዩ ።

« ለምን እንዲህ ሆነ ? ለምን ዛሬ ገለፅሽው ብለሽ ብትጠይቂኝ መልሱን አላውቅም ። ሒሊና ! እኔና አንቺ በህይወታችን አንድ ሰው ተካፍለናል . . . » ራሄል መናገሩን አልቀጠለችም ። ካለችበት ተነስታ ወደ መስኮቱ ተጠጋች ። የተዘጋውን መስኮት ከፍታ ወደ ውጪ ተመለከተች ። በመስኮቱ በኩል የሚገባውን አየር በኃይል እየተነፈሰች ካለችበት የምድሩን ርቀት ገመተች ።

« ያደረግኩት ትክክል እንዳልሆነ አውቃለሁ ። ነገር ግን ከቁጥጥሬ በላይ ነው ። ስለበደልኩሽ ትልቅ ይቅርታ እጠይቃለሁ ። ከዚህ በኋላ የእኔ መኖር ትርጉም የለውም ። አንቺ የዋህና ደግ ሰው በመሆንሽ እግዜር ከክፋ ነገር ይጠብቅሻል ። » ራሄል ንግግሯን በሳል ጨረሰች ። ሕሊና የሆነ ነገር ጠረጠረች ።

« ምን ነካሽ ? » በማለት ካለችበት ዘላ የራሄልን ቀሚስና እጅ ይዛ ታገለች ።

« ሕሊና እባክሽን ተይኝ ። አይ ዱ ኖት ዲዘርቭ ቱ ሊቭ » በማለት ግማሽ ሰውነቷን በመስኮቱ በኩል አውጥታ ስትታገል ሕሊና ሃይሏን ጨምራ ስትጎትታት ተያይዘው ወለሉ ላይ ወደቁ ።

« ለማን ብለሽ ነው ህይወትሽን የምታጠፊው ? ለእኔ እህቴ ነሽ ። በርግጥ ስለተፈጸመው ሁኔታ ባዝንም ጉዳትሽን አልሻም ። » ራሄል ባለችበት እንደ ህፃን ልጅ እየተወራጨች ፣ ፀጉሯን እየነጨች « እኔ ወራዳ ነኝ ፤ እኔ ልክስክስ ነኝ ፤ መኖር አይገባኝም ! » አለች።

ሕሊና የራሄልን ትከሻ በሁለት እጆቿ ግጥም አድርጋ ይዛ እየወዘወዘቻት « ራሄል ከጥፋትሽ ለማምለጥ ሞትን ምርጫሽ ማድረግ የዋህነት ወይም አላዋቂነት ነው ። ከበደልሽ ለመንፃት የግድ ወደ ሞት ጎዳና ሽሽት ገብተሽ መሆን አለበት ? ሞት ምንድን ነው ? ተስፋ ሲቆርጡ ፣ እንዲህ እንደ አንቺ በጸጸት አለንጋ ሲገረፉ እንዲሁም የተለያዩ ፈተናዎችን መጋፈጥ ሲያቅት የሞት ጨዋታ መጫወት ። ይሄ ማለት ምንድን ነው ? በሞት ድል ላይገኝ ከሞት ጋር ግብግብ በመግጠም ማሸነፍ አይገኝ ። ሊያም አንቺ ህይወትሽን ስለሰዋሽ ከበደል አይነፃም . . . ይልቅስ በህይወት ኖረሽ ካለፈው ስህተትሽ ተምረሽ ሰው ለመሆን መጣር ይሻላል ። መኖር በራሱ ብዙ ያስተምራል በሞትሽ በሽንፈት ላይ ሽንፈትን ደርበሽ ቁልቁል ወደ መቃብርሽ ተምዘግዝገሽ ስትወርጂ ዝም ብዬ አላይሽም » አለቻት ትንፋሿን በረጅሙ ለቃ ።



« ያልሽውን ብትይ እኔ እወድሻለሁ ። በአንቺና በመስፍን መካከል የነበረውን ግንኙነት ማለቴ ጓደኞች እንደነበራችሁ እስከነገርሽኝ ሠዓት በሁለታችሁ መካከል የማያቸውና የምሰማቸው ነገሮች እንዲሁም መስፍን ላንቺ ያለው አመለካከት ጥሩ ይሁን መጥፎ . . . ብቻ. . ብቻ ሁሉም ነገር ግራ ያጋባኝ ነበር አለቻት እጆቿን እያወናጨፈች ።

አየሽ ራሄል ባለማወቅ በሁለታችሁ መሀል ተሰንቅሬ በመግባቴና ህይወትሽን በመበጥበጤ በጣም አዝናለሁ ። በርግጥ ያደረግሽው ባህላችን የማይቀበለውና የሚያወግዘው ድርጊት ቢሆንም በእኔ በኩል እውነተኛና ፍላጎትሽን የሚገልፅ ነው ። » ለማረጋጋት እና ለማፅናናት ለፈለፈች ። ሁኔታው መቀዝቀዝ እንደጀመረ ሕሊና ራሄልን ከመሬት አስነስታ አልጋ ላይ እንድትቀመጥ አደረገች ።

« ራሄል ቀደምሽኝ እንጂ እኔ ነበርኩ ይቅርታ መጠየቅ የነበረብኝ ። ባለማወቅ ህይወትሽን መጥፎ ሁኔታ ላይ ጥየብሻለሁ ። አየሽ የእኔና የመስፍን ትውውቅ እንዴት እንደተጀመረ ፣ በምን እንዳለቀ ለአንቺ እንግዳ አይደለም ። ከመጀሪያውም መስፍንና እኔ ስለ ህይወት ያለን አመለካከት የተለያየ ነው ። ሁኔታዎች ገፋፍተው ለጋብቻ አበቁኝ እንጂ ትዳራችን በፍቅርና በሙሉ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ አልነበረም ። . . . ከመስፍን ጋር ከተገናኘንበት ቀን ጀምሮ አንቀቅልሽ ለነበረው ግንኙነቴ ተጨባጭ ፍች በማግኘቴ በጣም ደስታ ይሰማኛል . . . »

ሕሊና ፊቷን ከራሄል አዙራ ወደ መስኮቱ ተመለከተች ። አንዳች ቅዝቃዜ እንደገባው ሰውነቷን አንቀጠቀጣት ።

« ዛሬ የሞከርሽውን ብትፈፅሚ ኖሮ እስከ ህይወቴ መጨረሻ ፀፀት ላይ ጥለሽኝ ነበር » አለች እየዘገነናት ።

« እ . . እኔ በዚህ መልኩ አገኝሻለሁ ብዬ አልጠበኩም ነበር . . . » አለች ራሄል ዓይኖቿ ዳግም በፀፀት ዕንባ እየተሞሉ . . . . ::



* * *

ሕሊና ሆድ ብሷት ነበር :: ተነስታ አልጋዋ ላይ ጋደም አለች:: እንደድንገት እጇን ስትዘረጋ ኮሜዲኖዋ ላይ አረፈ :: የሆነ ፖስታ ይዞ ተመለሰ :: በቅርቡ ከአገር ቤት የደረሳት ነበር :: ሕሊና ማንበብ ጀመረች ::

*« . . .የአባትሽ መጥረቢያ አንድ ነገር ቢሆን በማለት እማማ በላይነሽ አደራ ብለው አስረክበውኛል ::መጥረቢያውን ባየሁ ቁጥር ትዝታሽ ይቀለቀስብኛል :: ሕሊና ይቅርታ አድርጊልኝና ያልኩትን ከመናገር ለመቆጠብ አልቻልኩም :: ያለ አንቺ የእኔ ህይወት ሙሉ ሊሆን አልቻለም :: በቅን መንፈስና በጥሩ ስሜት ለአንቺ ያለኝን ስሜት ፣ ለአንቺ ያለኝን ፍቅር ለማደብዘዝና ለመርሳት በፅኑ ሞከርኩ :: ሆኖም ሙከራዬ ውጤት አልባ ሆነ :: . . . ሕሊና መጥረቢያሽን በማግኘቴ ባለሁበት በትዝታሽ ለመፅናናት ረድቶኛል:: . . . አንቺም ባለሽበት ፣ እኔም ባለሁበት ሀሳባችንን ለማረጋጋት እግዚአብሄር ይርዳን :: . . . »*

« ያሬድ ከዚህ ሁሉ በኋላ እንኳ ሊረሳኝ አልቻለም » አለች እንባዋን እየጠራረገች :: ደብዳቤውን አንብባ የጨረሰችው በለቅሶ ነበር፣ የደስታና የሀዘን ድብልቅ የሆነ ለቅሶ :: ያሬድ ለእርሷ መቼም ቀን ክፋዋ ሆኖ አያውቅም :: በእርግጥም ገንዘቡን ፣ ጊዜውን ብቻ ሳይሆን ህይወቱንም ሰውቶላት ኖሯል :: ባነነች :: እንደበደለችው ፣ ግፍ እንደዋለችበት . . . ዘልቆ ተሰማት እና በሀሳብ አገር ቤት ዘለቀች:: አድባሯ ተቀበለቻት :: . . . ያሬድ የፅጌረዳ አበባ ይሏል ::

- ተፈፀመ -